# ስለ ስልጣን

በመስከረም አበራ

(2007)

© መስከረም አበራ፣ 2007 ዓ.ም

# ማውጫ


ስብሐት ለደጋጎች ፱

መግቢያ ፲

**ምዕራፍ አንድ፡ የብሄር ፖለቲካችን** 1

1.1 የብሄር ፖለቲካ ስንክሳር 1

1.2 በሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ የገነነው የብሄር ፖለቲካችን 7

1.3 የዘር ፖለቲካ እና ማህበራዊ ኑሯችን 12

1.4 የብሄረሰቦች ቀን በዓል፡ የብሄር ፖለቲካችን «ስንኩት» 14

1.5 ሉላዊነት፣ አለማቀፍ ዜግነት እና የብሄር ፖለቲካችን 19

**ምዕራፍ ሁለት፡ የሲቪክ ማህበራት ምንነትና ፋይዳ** 26

2.1 የሲቪክ ማህበራት ተፈጥሮ 26

2.2 የሲቪክ ማህበራት ሚና 28

2.3 የሲቪክ ማህበራት በኢትዮጵያ 30

**ምዕራፍ ሶስት፡ የአቶ መለስ ትዝታዎች** 44

3.1 የመለስ ውበቶች! 44

3.2 ፋኖው መለስ 46

3.3 በምስራቅ - ምዕራብ መስህብ መዋተት 47

3.4 የሚኒው እና ኩፎሚው መለስ 48

3.5 ፕሬዚደንት መለስ 51

# ስብሐት ለደጋጎች

የምበላውን ብቻ ሳይሆን የማነበውንም እያቀረባችሁ ላሳደጋችሁኝ ወላጆቼ አቶ አበራ አየለ እና ወ/ሮ ሙሉ ከበደ የሆንኩትን አይነት ሰው እንድሆን ስላደረጋችሁኝ ምስጋናዬ እጅግ ነው።

የመልካምነትህ ብዛት የምናገረውን ለማያሳጣኝ፣ አንተን ለማመስገን ስነሳ ቃላት አቅመቢስ፤ እንደብት ኮልታፋ ለሚሆንብኝ ወንድሜም፣ ሚስጠረኛ ጓደኛዬም፣ ባለቤቴም ለሆንከው ፍፁም ገ/ሚካኤል ስለ አንተ ምን የልቤን ሊገልፅ ምን ልበል? ሁልጊዜ በመልካምነትህ እንደምታሸንፈኝ፣ ሳትከራከር እንደምትረታኝ ግን ልንገርህ...

እነዚህ ፅሁፎች አስተማሪነት አያጣቸውምና ወደ መፅሃፍነት ቢቀየሩ የሚለውን ሃሳብ ከማንሳት ጀምሮ የእኔን የአይሆንም ክርክር ተቋቁሞ እስከ ማሸነፍ የደረስከው ወንድሜ ደረጀ ዘርጋው ምን ቃላት በቅተውኝ እንደማመሰግን አላውቅም። በህይወት ስንክሳር ውስጥ ለሚገጥሙኝ ወጣ ገባዎችስ የአንተ አለኝታነት በምን ይወከላል? ኑርልኝ - ደሬ

ጉዳዩን ሁሉ ጉዳይህ አድርገህ ለስኬቴ የምትለፋልኝ፣ ሁሌ እድገቴን የምታስብልኝ ወንድሜ ዳንኤል አዝምት ወረታህን ፈጣሪ እጥፍ ድርብ አድርጎ ይክፈልልኝ።

እጅግ የማከብርህ እና ብዙም የምማርብህ ወዳጄ ኃ/ኢየሱስ ባላ ከአንተ ጋር ትንሽ ስቀመጥ ብዙ የምማረው ሳያንስ የእኔን ትቂቱን ጅማሬዬን እንደትልቅ ቆጥረህ በርች ስትለኝ ዘወትር ትህትናህን እና መልካምነትህን አይለሁ እንጅ እኔማ አቅሜን አውቀዋለሁ። ስለሁሉ ምስጋናዬ ትልቅ ነው።

ይህ መፅሃፍ እውን እንዲሆን በብዙ የሞገትከኝ፣ አካሄዱ ሁሉ ከአደጋ እንዲጠበቅ የምትመክረኝ (አንዳንዴ ተግሳፅም አለ) መልካም ጓደኛዬ ሙሉቀን ተስፋው ለአንተ ምስጋና ምን አላት።

ገናድሮ አማርኛ መተየብ ሳልችል በፊት በወረቀት ላይ የሞነጨርኩትን ፅሁፍ አሁንኑ ፅፊህ ካላመጣህ የሚለውን ዘወትር አርብ አርብ ጨኽቴን (አርብ አርብ ይሸበራል ብለነው ነበር ይህን ነገር) ችለህ ብዙ የረዳኸኝ፣ ገና ሳልናገር ሃሳቤን ሁሉ የምትረዳኝ እጅግ ምቹ ጓደኛዬ አብርሃም ገ/ኪዳን እስኪ ዛሬ እንኳን ላመስግንህ።

ፅሁፎቼን አንብበህ የምታብረታታኝ፣ የስደት እና እስር ዜና ስትሰማ ደግሞ አብዝተህ የምትጨነቅልኝ አብሮ አደግ ወንድሜ እና ጓደኛዬ አትክልት (እዮብ)መልካሙ ለበዛው መጠንቀቅህና ርቀት ላልበገረው መልካም ጓደኝነትህ ምስጋና ያንሳል።

ባህር ማዶ ሆናችሁ ይጠቅማታል ያላችሁትን የሚነበብ ነገር ሁሉ የምትልኩልኝ ጓደኞቼ ጥበበ ሲራክ፣ ሂሩት ጌታሁን እና አላቸው ሽታሁን እንዲሁም ጳውሎስ ሚኪያስ ውለታችሁ እናንተ እንደምትሉት ትቂት እንዳይመስላችሁ።

ሃሳብ ፅሁፍ እንደሚሆን አበክረህ ነግረኸኝ ወደ ፕሬስ እንድቀላቀልም ለረዳኸኝ ጋዜጠኛ አናንያ ሶሪ ብዙ ምስጋና አለኝ።

በየሳምንቱ ፅሁፎቼን እያነበባችሁ ገንቢ ሂስ ላልነፈጋችሁኝ መልካም ወዳጆቼ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ፣ ገጣሚ ውዳሴ ፈረደ፣ አቶ ብዕአተ ተረፈ፣ አስተዋይ ሳሙኤል፣ ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ፣ የቀድሞ የፓርላማ አባል አቶ መሃመድ አሊ፣ መልካምሰው አባተ፣ መምህር ጌታነህ አበበ፣ ሂሩት አመሃ፣ መሰረት ባየ፣ ሳሙኤል አበበ፣ ከበቡሽ አለሙ፣ ሰለሞን ተስፋዬ፣ ሄኖክ ባየ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

የኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ እና የፋክት መፅሄት ዝግጅት ክፍሎች ፅሁፎቼን ስላስተናገዳችሁልኝ አመሰግናለሁ።

# መታሰቢያነቱ

ይህ መፅሃፍ መታሰቢያነቱ መሞቱን መቀበል ለሚከብደኝ አመለ ሸጋው ወዳጄ ሚች ጋዜጠኛ ሚሊዮን ሹርቤ ይሁንልኝ።



# መግቢያ

«ፖለቲካ ማለት ለሃገር ማሰብ ነው» እንዲል አዳም ረታ ስለሃገር ፖለቲካዊ ጉዳዮች ማንበብ፣ ማሰላሰል፣ መፃፍ የዜግነትን ማበርከት ነው። እኔም ይህ እጣ ወድቆብኝ ስለ ሃገሬ ፖለቲካ በማንበብ እና በመከታተል ትቂት ጊዜያትን ካሳለፍኩ በኋላ በዚህች መፅሃፍ የተሰበሰቡ ፅሁፎችን ለማበርከት ቻልኩ።

በዚህ መፅሃፍ የተካተቱ ፅሁፎች በብዛት በኢትዮ-ምህዳር አለያም በፋክት መፅሄት የተስተናገዱ ናቸው። ፅሁፎቹን ወደ መፅሃፍነት ለመቀየር ያስፈለገበት ምክንያት አንድም በፋክት መፅሄት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ፅሁፎቹን ያነበቡ አንባቢን ከዚህ በፊት የፃፍኳቸውን ፅሁፎቹን ቢያገኙ እንደሚወዱ ስለነገሩኝ፣ ሁለትም ብዙ ወዳጆች ፅሁፎቹ የተወሰነ አስተማሪነት አያጣቸውምና ወደ መፅሃፍነት ቢያድጉ የሚል ሃሳብ ስላቀረቡልኝ ሶስትም ፅሁፎቹ የዘመናችንን የፖለቲካ ትርታ በከፊል የያዙ በመሆናቸው ይህን ለመረዳት የሚፈልግ የኋለኛ ትውልድ በአንድ ላይ ቢያገኛቸው ደግ ነው ብዬ ስላመንኩ ነው።

ፅሁፎቹ በተለያየ ወቅት እንደመፃፋቸው በምዕራፍ ለማስቀመጥ የመንፈስ መቀራረባቸውን መሰረት አድርጌያለሁ። የጭብጥ መራራቅ ያላቸውን ነገር ግን ከመታተም እድል እንዳይጎድሉ ያልኳቸውን ፅሁፎች «ቅይጥ ፖለቲካዊ ጉዳዮች» በሚል ምዕራፍ ስር ተካተዋል።

ረዥም ርቀት በአንድ እርምጃ ይጀመራልና ቀጣይ ስራዬ ወጥ መፅሃፍ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። እንደ ሃሳቤ ቢሆን ወጥ ስራዬ ቢቀድም በወደድኩ ነገር ግን ሌሎች የኑሮ ዱብዱቦች ጊዜዬንም ቀልቤንም ስለሰረቁት ይህ ስብስብ ስራ እንዲቀድም ሆነ። ብዙ ባልራቀ ጊዜ ወጥ ስራ ይገፍ ብቅ እንደምል ቃል ገብቼ መግቢያዬን ልደምድም።

ይሁን እንጅ የብሄር ፖለቲካ የብሄር ጭቆናን የማስቀረትም ሆነ ዲሞክራሲን የመገንባት አቅም እንደሌለው ይገልፃሉ ፕሮፌሰር መሳይ።

## በሽታ በሽታን አይፈውስም!

ብሄርንም ሆነ ማንኛውንም የሰው ልጅ ማንነት መሰረት ያደረገ ጭቆና መፈታት ያለበት የሃገር ችግር ነው። ችግሩን ለማፍታት የምናደርገው እርምጃም ግን ሌላ ችግር ይዞ እንዳይመጣ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው። በሃገራችን በዘውዳዊው ዘመንም ሆነ በወታደራዊው አስተዳደር የሃገራችን ችግር ዘርን ማዕከል ያደረገ ጭቆና ነበር ወይስ አይደለም? የሚለው ነገር አከራካሪ ቢሆንም ዘርን ያማከለ ብሄራዊ ጭቆና ደርሶብናል ያሉ ወገኖች በብሄረሰባቸው ተቧድነው እየታገሉ ነው። ፕሮፌሰር መሳይ ግን ብሄርን መሰረት ያደረገ ጭቆና ብሄርን መሰረት ባደረገ ትግል እንደማይፈታ ሲገልፁ «በሽታ እንዴት በሽታን ለማዳን መፍትሄ ሊሆን ይችላል?» ሲሉ ይጠይቃሉ።

የፕሮፌሰር መሳይን ክርክር ወደ ሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስናመጣው በአሁኑ ጊዜ አንድ ብሄርን ነፃ እናወጣለን ብለው በብረትም ሆነ በምርጫ ለማሸነፍ ከሚታገሉት ፓርቲዎች አንዱ ስልጣን ላይ ቢወጣ ቆሜለታለሁ የሚለውን ብሄር ሁለመና በሌሎች ላይ ለማንገስ፣ ጭላፊ የብሄሩን ተወላጆች ቆንጥሮ አውጥቶ ባለሃብት እና ባለስልጣን ለማድረግ እንደሚጣደፍ እሙን ነው። ይህ ደግሞ በፊት ተጨቁኛለሁ ብሎ ያስብ የነበረን ከአንድ ብሄር የሆነ የተወሰነ ቡድን ወደ ጨቋኝነት ይቀይር ይሆናል እንጅ ጭቆናን አያጠፋም። ምክንያቱም ዛሬ ባለስልጣን የሆነው ብሄር ትናንት ይጨቁነኝ ነበር ብሎ የሚያምነውን ብሄር በተራው መጨቆኑ አይቀርም፤ በማንም ላይ ቢሆን ጭቆና ካለ ደግሞ ነፃነት አለ ማለት አይቻልም። ትናንት ጨቁኖኛል ብሎ ያሰበውን በተራው ሊጨቁን የሚነሳ ቡድንም በቀለኛ እንጂ ነፃ አውጭ ሊሆን አይችልም። ነፃነት ማንኛውንም ጭቆና በእኩልነት እና ነፃነት የሚተካ እንጂ የጨቋኝን እና ተጨቋኝን ቦታ የሚቀያይር ማለት አይደለም።

የብሄራቸውን ነፃነት ብቻ ትኩረት አድርገው የሚነሱ ነፃ አውጭዎች ደግሞ ሃገር የመምራት ስልጣን ይዘውም ቢሆን ለሁሉም ዜጋ ነፃነት እና እኩልነት እንዳይቆሙ ቀድሞ ያደቆናቸው ሴጣን በጆ አይላቸውም። እነዚህ ወገኖች በተለይ ስልጣን ላይ ከተቆናጠጡ በኋላ ቆምንለት የሚሉትን ብሄርም ከሌላው ለይተው የሚያደርጉለት ጉልህ ነገር የለም። ለብሄር ፖለቲካ ታጋዮች



ቆምንልህ የሚሉት ብሄር ህዝብ አስፈላጊነቱ በትግል ወቅት ወደ ስልጣን ደጀሰላም እንዲያደርስ እንጅ ከስልጣን በኋላ እንደ አጠቃይ ብሄር ረብ ያለው ነገር የማግኘት እድሉ ዝቅ ያለ ነው። ለዚህም ነው የብሄር ፖለቲካ የስልጣን ጥመኞች ጎሬ ነው የሚባለው።

በብሄር ስም ወደ ስልጣን የሚመጡ ቡድኖች ቆምንለት የሚሉትን ህዝብ ችግር ላይ የሚጥሉበት ሁኔታም ይኖራል። በዚህ ረገድ ለትግራይ ህዝብ ቆሜያለሁ የሚለውን ህወሃት እና ለኦሮሞ ህዝብ ቆሜያለሁ የሚለውን ኦነግ ሁኔታ ማንሳት ይቻላል። ህወሃት የትግራይን ህዝብ በሁለት መንገድ ጎድቶታል። አንዱ በትጥቅ ትግሉ ወቅት በግድም በውድም ልጆቹን እንዲገብር፣ ሳይተርፈው የህወሃትን ወፈ-ሰማይ ወታደር እንዲያበላ፣ ጦርነት ከሞት ባሻገር የሚያመጣቸውን መፈናቀል እና ርሃብ የመሰሉ ሰቆቃዎችን እንዲያስተናግድ ሆኖ ኖሯል። ከድል በኋላ ህወሃት መራሹ መንግስት በአምቻ እና በጋብቻ የተጣመሩትን ትግራዋይ ዜጎች ባለፀጋ እና ባለስልጣን ስላደረገ ትግሬ ሁሉ ያለፈለት የሚመስለው ኢትዮጵያዊ ቀላል አይደለም። እናም ህወሃት ቀን ዞሮበት ከስልጣን ቢወርድ ሌላው ኢትዮጵያዊ ክፉ ሊያደርግብኝ ይችላል እያለ ብዙው የትግራይ ተወላጅ ያልበላው እዳ የሚያስበረግገው ሆኗል። በዚህ መንገድ ለነፃነትህ ቆምኩልህ ያለው ህወሃት የትግራይን ህዝብ በሸማቂነቱም በመንግስትነቱም ዘመን ጎድቶታል። በተመሳሳይ ለኦሮሞ ህዝብ ቆሜያለሁ የሚለው ብረት አንጋቹ ኦነግ በስሙ ጦስ የኦሮሞን ወጣት ለእስር ቤት ደንበኝነት፣ ለማእከላዊ እስር ቤት እንግልት ዳረገው እንጅ የፈየደለት ነገር የለም። በብዙ መፍገምገም እልፍ አመታትን የገፋው ኦነግ ለህወሃት የቀናው በለስ ቀንቶት ስልጣን ቢይዝ ኖሮ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ሊኖረው የሚችለው ግንኙነት እንደ ባለስልጣኑ ህወሃት እና የትግራይ ህዝብ እንደማይሆን እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

ህወሃትን ጨምሮ የብሄር ነፃ አውጭዎች ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ነፃ እናወጣዋለን ብለው የታገሉለትን ብሄር መጥቀም የማይችሉት ለምንድን ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ከመጀመሪያው በአንድ ሃገር ከሚኖሩ ህዝቦች ውስጥ አንዱን ለይቶ ለብቻው ተጠቃሚ ማድረግ ወይም ነፃ ማውጣት ቀቢፀ-ተስፋ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባለ በሁሉም ማዕዘን ያለው የሃገሪቱ ዜጋ ሁሉ በተቀራረቢ ድህነት ያደላበት፣ ነፃነት የጠፋበት ኑሮ በሚገፋበት ሃገር አንድ ብሄር ብቻ የተለየ ጉዳት የደረሰበት ሌላው ደግሞ

ዘመናት ነጎዱ። ኢህአዴግ ከደርግ እንደሚሻል ሚከራከርበት ዋነኛ ማስረጃም ይሄው ለብሄረሰቦች ሰጠሁት የሚለው መገንጠልን የጨመረ መብት ነው። ኢህአዴግ ይህን ይበል እንጅ የዘረጋው የብሄር ፖለቲካ ከአንዳድ የዲሞክራሲ መርሆዎች ጋርም ሆነ ከዓለም አቀፍ ሰብዐዊ መብት ድንጋጌዎች ጋር አይገጥምም።

በዲሞክራሲዊ አስተዳደር የብዙሃኑ አስተሳሰብ ገዥ ህግ ይሆናል። እዚህ ላይ ልብ መባል ያለበት ወሳኙ አብላጫ ድምፅ ያገኘው ሃሳብ እንጂ የብዙ ቁጥር ባለቤት የሆነው ዘር ወይም ቋንቋ አይደለም። የዲሞክራሲ መሰረታዊ መርህ ትኩረቱን የሚያደርገው በሰዎች ሃሳብ መመሳሰል እንጅ የቋንቋ መመሳሰል፣ የጎጥ መዋሰን ላይ አይደለም። ዲሞክራሲያዊ አሰራር ሰዎች ተመሳሳይ ቋንቋ ስለተናገሩ ወይም ከአንድ ብሄር ስለወጡ ብቻ ተመሳሳይ ሃሳብ እና ፍላጎት አላቸው ብሎ አያምንምና የብሄሮችን የቁጥር ብልጫ ሳይሆን የሃሳብ በላይነትን ይዞ ይጓዛል። የእንትን ብሄረሰብ አባላት ምን ያስባሉ ሳይሆን አንድ ሃሳብ በስንት ሰዎች ተደገፈ በስንቶቹስ ውድቅ ተደረገ ሲል በብሄራቸው ሳይሆን በግላቸው የወሰኑ ሰዎችን ድምፅ ቁጥር ብዙሃኑ የደገፈውን ሃሳብ ገዥ ያደርጋል። በሌላ አባባል ዲሞክራሲያዊ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ በጣም አስፈላጊው የግለሰቦች ግላዊ ውሳኔ ነው። ለዚህ ነው የቡድን መብትን እና ፍላጎት የሚያስቀድመው ብሄር ፖለቲካ ዲሞክራሲን መገንባት አቅም የለውም የሚባል ክርክር የሚነሳው።

የቡድን መብትን የሚያስቀድመው የብሄር ፖለቲካ ከዲሞክራሲ መርሆዎች የሚጋጭበት አጋጣሚ ብዙ ነው። የዲሞክራሲ እምብርት የሆነው ምርጫ ሲካሄድ ዜጎች መሪዎቻቸውን ለመምረጥ የሚወስኑት በግላቸው ነው። በግል መረጡትን መንግስት ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም ህብረት የሚያደርጉት በሃሳብ ከሚመስሏቸው እንጅ በቋንቋ ከሚጋሯቸው ጋር አይደለም። ምናልባት ቋንቋን ከሚጋሯቸው ጋር ህብረት የሚያደርጉት ባህላቸውን ለተመለከተ ጥያቄ ሊሆን ይችላል። በዚህ በኩልም ቢሆን የዲሞክራሲ ባህል በተገነባበት ሃገር የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ዜጎችም በሃሳቡ ስለሚስማሙ ጥያቄያቸውን ሊስተጋቡላቸው ይችላሉ። ይህ የሚያስረዳው ደሞክራሲን ለመገንባት ቅድሚያ ሊሰጠው ሚገባው የግለሰቦች የሃሳብ እንጅ ብሄር መመሳሰል አለመሆኑ ሲሆን በተቃራኒው የብሄር መመሳሰልን ዋና አድርጎ ዲሞክራሲን ለመገንባት መታተር ከንቱ ልፋት መሆኑን ነው። በተጨማሪም የዲሞክራሲ



መሰረት የሆነው ነፃነት ከግለሰብ ካልጀመረ ዲሞክራሲን ለመገንባት በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነፃ ማህበረሰብ መፍጠር ያዳግታል። በተቃራኒው ኢህአዴግ በሚያራምደው የዘር ፖለቲካ ታሳቢ የሚያደርገው ግለሰቦች ነፃነታቸውን የሚያገኙት ለብሄራቸው በጅምላ ከሚሰጠው ነፃነት ነው። ይህን የኢህአዴግ እሳቤ ከፈረሱ ጋሪውን ያስቀደመ ነው የሚሉት ፕሮፌሰር መሳይ ነፃ ግለሰቦች ሲሰባሰቡ ነፃ ቡድንን ይፈጥራሉ እንጅ ቀድመው ግለሰባዊ መብታቸውን ባላረጋገጡ ሰዎች የተፈጠረ የብሄርም ሆነ የሌላ ቡድን ስብስብ ዲሞክራሲን ለመገንባት የሚበቃ ነፃነት ሊኖረው አይችልም ይላሉ።

የኢህአዴግ ብሄርን ማእከል ያደረገ የቡድን መብትን የማቀንቀን ዘይቤ ዘርን ማእከል አድርጎ በፈጠረው የብሄር ፌደራሊዝም ይታገዛል። በመሆኑም ዜጎች ለወጡበት ብሄር ከተከለለው ክልልም ሆነ ዞን ወጥተው ሲኖሩ ብዙ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን እንዲያስተናግዱ ሆኗል። ይህ ግን ለኢህአዴግ ችግር መስሎት አያውቅም። እንዴውም ከቡድን መብት ይልቅ የለግሰቦች መብት ይቅደም የሚሉ ምሁራንን የተስፋፊ አማሮችን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚወተውቱ ሲል ይሞግታል። እንደ ኢህአዴግ እሳቤ የአማራ ብሄረሰብ ተወላጆች በቀድሞዎቹ መንግስታት ረዳትነት በመላ ሃገሪቱ የመስፈር እድል ተጠቃሚዎች ናቸው። ይህ ማለት በሃገሪቱ ከክልላቸው ውጭ ከሚኖሩ ህዝቦች ውስጥ የአማራ ብሄር ተወላጆች አብላጫውን ቁጥር ይይዛልና ኢህአዴግ የሰጠው ብሄርን ማእከል ያደረገው የቡድን መብት ለክልሉ ተወላጆች ብቻ የሚሰጠው የፖለቲካ ስልጣን የመያዝ እና ሌሎች መብቶች የ«መጤ» አማሮችን የቀድሞ የበላይነት የሚያዳክም ነው። ውጤቱም ኢህአዴግ ሲያወራለት የነበረውን የነፍጠኛውን ስርአት የማንኮታኮት ህልም ያሳካል ተብሎ ይታሰባል። በተቃራኒው ለግለሰቦች መብት ቅድሚያ ቢሰጥ ከክልላቸው ውጭ በተለይ በከተሞች በብዛት የሰፈሩት አማሮች በሃገሪቱ የፖለቲካ አውድ ላይ ብቅብቅ ሊሉ ይችላሉ ብሎ ያስባል። በመሆኑም ኢህአዴግ ዘርን ማዕከል ያደረገውን የቡድን መብትን የማቀንቀን ዘይቤውን ይቀይራል ብሎ ማሰብ በመሬት ባለቤትነት ላይ ያለውን አቋም ይቀይራል ብሎ እንደማሰብ ነው፤ ለዚህ የኢህአዴግ መልስ ያው በመቃብሬ ላይ ነው የሚል አቋሜን ከምቀይር ብሞት ይሻለኛል የሚለውን አቋሙን በሾርኔ ሚገልፅበት ክርክር መሆኑ ይታወቃል።

ብሄር ስም በጅምላ ያነሳሱ ይሆናል እንጂ ዜጎቹ በተናጠልም ሆነ በቡድን የሚደርስባቸው የሰብዐዊ መብት ጥሰቶች እንደማያሳስቧቸው በርካቶች በስመ አማራ ከቤት ንብረታቸው ሲፈናቀሉ ጆሮው ላይ የተኛው ብአዴን፣ የጋምቤላ ህዝቦች ለአረብ እና ለህንድ ቱጃሮች ሲባል ቀያቸውን ለወቀው ሲጉላሉ ድምፁን ያጠፋው ጋህዴድ አብነቶች ናቸው።

## 1.3 የዘር ፖለቲካ እና ማህበራዊ ኑሯችን

የአንድ ሃገር ፖለቲካዊ ስርአት በሃገሪቱን ሁለመና ላይ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅሙ ከፍ ያለ ነው። ሃገር እያስተዳደረ ያለ የፖለቲካ ዘይቤ ነፀብራቁ በማህበራዊ ኑሮ ላይ ሲታይ ጊዜ አይወስድም። እንደ ኢትዮጵያችን ግላዊነት በማህበራዊነት ላይ መግነን ባልቻለበት ሃገር በተለይ ፖለቲካዊ ድባቡ በማህበራዊ መስተጋብሩ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ በጎ መሆን ካልቻለ ጉዳቱ ብዙ ይሆናል። ዘርን እና ቋንቋን ብቻ ማዕከል ያደረገው የፌደራል ስርአታችን በማህበራዊ ኑሯችን እና የእለት ተዕለት መስተጋብራችን ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አሳርፏል። ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በመጣ ሰሞን ብዙ ዘመናትን የኖረው በእድር እና ዕቁብ ስር ህብረት የማድረጋችን ባህል ከጉርብትና እና ትውውቅ ይልቅ ዘር ተቋጥሮ፣ ሃረግ ተማዞ የሚደረግ አብሮነት ወደ መሆን አድልቶ ነበር። የእድር እና መሰል መረዳጃ ማህበራት ስሜያዎች እንደ ሃገራችን ክልሎች የዘር ወይ የቋንቋ ስም ተሰጥቷቸው ነበር። እድር እቁቦቹን የዘረኝነት ካባ ለማላበስ የተሮጠበት ፍጥነት እንደአጀማመሩ ባለመቀጠሉ አሁን በተሻለ ሁኔታ ላይ ቢሆንም ቀርቷል ማለት ግን አይቻልም።

ለእቁብ እድሩ ያልደረሱ ወጣቶች ደግሞ ወዳጅ ጓደኝነታቸው በአመዛኙ ከወንዛቸው ልጆች የሚሆንበት አጋጣሚ ይበዛል። የወንዝን ልጅ ፈልጎ መወዳጀቱ በራሱ ጎጅ አይደለም። ችግሩ የወንዝ ልጆች ሲገናኙ ሌሎችን ጎሪጥ ማየት ሊከተል መቻሉ ነው። የራሳችንን ብሄር መውደድ ማክበራችን ሌሎች በመጥላት፣ በመፍራት እና በመጠራጠር ካልታጀበ ልክ አልመሰለን ብሏል። ይህ ሁሉ ሲዳመር ባዕዳንን ሲያስቀና የነበረው ኢትዮጵያዊ የመከባበር እና የመረዳዳት ልምዳችን ደስ በማያሰኝ የመጠባበቅ፣ የመጠራጠር እና የመፈራራት ድባብ ውስጥ ወድቋል።



### ምን ይሻላል?

አሁን ያለንበት የብሄር ፖለቲካ የፈጠረብን ማህበረ-ፖለቲካዊ ድባብ ካለማው ያጠፋው ይብሳል። በማይካድ መልኩ ስርዓቱ ከቀደሙት ስርዓቶች በተሻለ ሁኔታ በሃገሪቱ ያሉ ህዝቦች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ፣ ባህላቸውን እንዲያሳድጉ አድርጓል። በመከባበር ላይ የተመሰረተ አገራዊ አንድነት በመፍጠሩ ረገድ ግን ኢህአዴግ የፈጠረው ፖለቲካዊ ከባቢ ስኬታማ አይደለም። የዚህ ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ለዘር ፖለቲካ የተሰጠው አላስፈላጊ ግዙፍ ቦታ ነው። ሁሉን ነገር በብሄር መነፅር ሚመለከተው ኢህአዴግ ሃገሪቱን የተበተቧትን ችግሮች ሁሉ ለመፍታት የብሄር ጉዳይን ቀዳሚ ያደርጋል ይህ ደግሞ ከብዙዎቹ የዲሞክራሲ መርሆዎች ጋር እየተጋጨ የዲሞክራሲን ባህል መፍጠር አልተቻለም። ዲሞክራሲ ባላደገበት ሁኔታ ደግሞ ሁሉንም እንደማንነቱ ማስተናገድ የሚችል የሰለጠነ ፖለቲካዊ አስተዳደር መፍጠር የማይታሰብ ነው። በመሆኑም የሃገራችንን ብዙ ትናንሽ ችግሮችን ለመፍታት ትልቁ ፖለቲካዊ ክበብ በዲሞክራሲዊ አስተሳሰብ መቃኘት አለበት። ዘር ቋንቋው ምንም ይሁን ምን እያንዳንዱ ዜጋ ለዲሞክራሲ ወሳኝ የሆነውን ነፃነት መናፈቅ አለበት። ይህን ሲያደርግ ደግሞ የብሄሩን ነፃነት ሳይሆን አገራዊ ነፃነትን፣ የጎጡን ተጋሪዎች ብቻ ሳይሆን የዜጎችን ሁሉ ሰብአዊ መብት መከበር ታሳቢ ማድረግ አለበት። ምክንያቱም አንድ ሰፈርን ቀንብቦ ነፃ ማውጣት አይቻልም፤ ቢሞከር እንኳን ውጤቱ ምን እንደሆነ ኢህአዴግ ከፈጠረው አስተዳደር ያየነው ነው። ነፃነትን መሻት ዲሞክራሲዊ አስተዳደርን ለማምጣት ወሳኝ ምዕራፍ ነው። ዲሞራሲ የሚሰፍነው ደግሞ ነፃነትን እና እኩልነትን የሚሹ ዜጎች በሚያደርጉት የሃሳብ ምስስሎሽ የፈጠረው ህብረት እንጂ በዘር ተቧድኖ ጎሪጥ በመተያየት አይደለም። ዲሞክራሲን የመሻቱ የጋራ ግንዛቤ በሚፈጥረው ህብረት ሚደረግ ትግል ሁሉንም አይነት ጭቆና፣ አድሎ፣ ብልሹ አሰራሮች የመዋጋት አቅም ይኖረዋል እና ጉዟችን ለሁሉም ዜጋ እኩል ነፃነት ወደሚያመጣው መንገድ መሆን አለበት። ይህን በማስመልከት ታላቁ የነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ ተናገሩት ንግግር ከላይ የተነሳንበትን ሃሳብ ያጠናክራል "freedom is indivisible .....To be free is not merely to cast off one›s chains, but to live in a way that respects and enhances the freedom of others".

## አለማቀፍ ዜግነት ምንድን ነው?

አለማቀፍ ዜግነት የትውልድ እድገት ቦታን፣ ቋንቋ ዘር ባህልን ትኩረት ባላደረገ መልኩ ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ሰብአዊ መብት መከበር በመቆም፣ የሰው ልጆችን ልዩነት እና እኩልነት አምኖ የሁሉንም ማንነት በማክበር፣ ሰብአዊ ፍጡርን ሁሉ ለመርዳት በመዘጋጀት፣ ስለፍትህ በመሞገት፣ ግጭትን በሰላም ለመፍታት ባለ ዝግጅት፣ አገራዊ እና አለማቀፋዊ ሁነቶች በመከታተል ወዘተ እንደሚገለፅ "People in Need" የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት "why Global Citizenship?" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ፅሁፍ ያብራራል። ፅሁፉ አለማቀፋዊ ዜግነትን ከበጎ አስተሳሰብ እና መልካም ስብዕና ጋር ያያይዘዋል። ሰብአዊ ፍጡርን ሁሉ እኩል ማየት፣ ለመርዳት መዘጋጀት፣ ስለ ፍትህ መንደል መቆጨት፣ ወ.ዘ.ተ ባህሪያት የሰው ልጅ ለራሱ ወይም ለቋንቋ፣ ባህል፣ ግዛት ተጋሪዎቹ ብቻ ከማሰብ ከፍ ወዳለው የሰብአዊነት ማማ መመንደግን ያሳያል። oxfam የተባለው ድርጅት "cool planet" በሚል ርዕስ ባሰራጨው ፅሁፍ እንደሚገልፀው የዚህ አይነት ስብዕና ባለቤቶች በየትኛውም የአለም ዳርቻ የሚከሰት የሰብአዊ ፍጡራን ችግር ያሳስባቸዋል። ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ በወለዳቸው ችግሮች ላይ ያሉ ሰብአዊ ፍጡራንን ለመርዳት የተጎጅዎቹ ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው። ይህ አይነቱን በጎ አስተሳሰብ ወደ ገቢራዊነት ለመቀየር የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማት እና ማህበራት ይቋቋማሉ። ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በተለይ አለም አቀፍ ተቋማትን መስርቶ ስለ አለም ህዝብ ሁለንተናዊ ችግሮች ተቋማዊነት ባለው ሁኔታ መሞገቱ ፈለግ እየተስፋፋ ነው።

የአለም አቀፍ ዜግነት አስተሳሰብ የበለጠ የሚጠቅመው በብዙ ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ ሚገኙትን ሶስተኛው አለም ሃገራት ነው። እነዚህ ሃገራት ዲሞክራሲ ያላደገባቸው በመሆናቸው አለመግባባቶች ወደ ጦርነት የሚያድጉበት እድል ሰፊ ነው። ጦርነቱ ደግሞ ስደት፣ መፈናቀል፣ የህይወት መጥፋት አይነት ችግሮችን ይዞ ይመጣል። በእነዚህ ሃገራት የሚኖሩ ዜጎች ግልፅ ጦርነት በሌለበት ሁኔታም በገዛ መንግስቶቻቸው ዲሞክራሲ የራቀው አስተዳደር ፍትህ የሚያጡበት፣ ሰብአዊ መብታቸው የሚረገጥበት አጋጣሚ ይበዛል። ይህን ከመሰለው ሰው ሰራሽ አደጋ በተጨማሪ ተፈጥሯዊ አደጋዎች ሲከሰቱ በታዳጊ ሃገሮች ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከአደጉት ሃገሮች ላቅ ይላል።



በዚህ ሁኔታ ላሉ ሃገሮች አፋጣኝ የነፍስ አድን ስራ የሚሰራው የአለም አቀፍ ዜግነት አስተሳሰብ የተነሳ ነው። ለዚህ ደግሞ ከዘር፣ ከባህል፣ ከመንደረኝነት አስተሳሰብ መዋጀትን ይጠይቃል። ከዘመኑ ጋር ለመራመድም ወደዚህ አይነት አስተሳሰብ መግባት ወሳኝ እንደሆነ Oxfam የተባለው ድርጅት "Qualities of Global citizenship" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው መጣጥፍ ይገልፃል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመጣው ሉላዊነት ፈለግ ጋር አካሄድን ማስተካከል ከሃገርም ሆነ ከግለሰቦች የሚጠበቅ የውዴታ ግዴታ እየሆነ ነው። በሃገር ደረጃ ሃገራቱ ሉአላዊነታቸው እንደተጠበቀ አለማቀፍ ህግጋትን ማክበር ይጠበቅባቸውል። ዲሞክራሲ የዳበረባቸውን ሃገራት የሚመሩ መሪዎች ከሞላ ጎደል መሰረታዊ ዓለማቀፍ የሰብዐዊ መብትን የተመለከቱ አለማቀፍ ህግጋትን ስለሚያከብሩ ስለሰብአዊ መብት ከሚሞግቱ ተቋማት የከፋ ስሞታ ሲቀርብባቸው አይሰተዋልም።

## የአለም አቀፍ ዜግነት ፋይዳ

የአለም አቀፍ ዜግነት አስተሳሰብ ስለሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን መብት መከበር እና ስለፍትህ የሚሞግቱ ተቋማት እንዲመሰረቱ ረድቷል። በመሆኑም በአምባገነን መንግስት አገዛዝ ሰብአዊ መብታቸው ለሚረገጥ፣ በተፈጥሮ አደጋ ለሚጎዱ ወገኖች ዘር፣ ድንበር ሳይወስነው ጩኸታቸው እንዲሰማ፣ ችግራቸው መፍትሄ እንዲፈለግለት እየተደረገ ይገኛል። ሂውማ ራይትስ ዎች የተባለው ዓለም አቀፍ ስለ ሰብዊ መብት ሞጋች ተቋም የሃገራችንን መንግስት ጨምሮ የራሳቸውን ህዝብ ሰብዐዊ መብት አክብረው የማያስከብሩ መንግስታትን በየጊዜው የሚሞግቱት ዓለም አቀፍ ዜግነት ባመጣው የሰብአዊነት ትስስር ነው። ጦርነት መፈናቀልን አስከትሎ ደጋግሞ በሚጎበኛት አፍሪካ የሚኖሩ ዜጎች ሲፈናቀሉ ልብስ እና ጉርስ የሚያቀርቡ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ተጎጅዎችን እንዲረዱ የሚያደርጋቸው ዓለማቀፍ ዜግነት ባመጣው ከመንደር አስተሳሰብ አለፍ ያለ የሰብአዊነት ስሜት ነው። በቅርቡ ለሃገራቸው ህዝቦች ያቀቱ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎችን እና የጦር አበጋዞችን በሰብአዊ መብት ጥሰት እና የጦር ወንጀለኝነት እየከሰሰ ያለው ዓለም አቀፍ ፍርድቤት መቋቋም ሁሉ የአለም አቀፍ ዜግነት አስተሳሰብ ውጤት ነው።

# ምዕራፍ ሁለት፡ የሲቪክ ማህበራት ምንነትና ፋይዳ

## 2.1 የሲቪክ ማህበራት ተፈጥሮ

የሲቪክ ማህበራት ዋና መለያ መንግስታዊ ያለመሆናቸውነው። ይህ ማለት ግን ከመንግስት ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም ማለት አይደለም። ማህበራቱ በአንድ ሃገር ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸውን ፈቃድ ከመስጠት/መከልከል ጀምሮ የማህበራቱን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ መከታተል የመንግስት ስልጣን እና ሃላፊነት ነው። በተጨማሪመ ማህበራቱ የትኩረት አቅጣጫ አድርገው የሚሰሩት ስራ ከመንግስት ፖሊሲዎች የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር ስምም መሆን አለባቸው። እነዚህ ሁኔታዎች ከተሟሉ በኋላ ግን ማህበራቱ ሚሰሩትን ስራ ያለ መንግስት ቀጥተኛ ጣልቃገብነት እና ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይችላሉ። መንግስታዊ ያልሆኑ የሚያስብላቸው ዋነኛ ምክንያትም ይህ ነው።

የማህበራቱ መንግስታዊ ያለመሆን ተፈጥሮ በብዙ መንገድ የሚገለፅ ሲሆን የበጀት ምንጫቸው ከመንግስት ያለመሆኑ አንዱ ነው። የሲቪክ ማህበራት የበጀት ምንጭ ለጋሽ ተቋማት/ግለሰቦች ወይም የአባላት መዋጮ ሊሆን ይችላል። የማህበራቱ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ መተዳደሪያ ደንብ በቀጥታ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለመሆኑም ሌላው ማኅበራቱን መንግስታዊ ያልሆኑ የሚያስብላቸው ገፅታቸው ነው። ዲሞክራሲ ባደገባቸው ሃገራት በሲቪክ ማህበራት ላይ የመንግስት ቀንበር ልዝብ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ፈቃድ ከመስጠት፣ ማደስ፣ ተጨባጭ አካሄዳቸው ከአላማቸው ጋር ካልሄደ ደግሞ ፈቃዳቸውን እንደአስፈላጊነቱ ማገድ ወይ መከልከል፣ የኦዲት ሪፖርታቸውን ከመከታተል ባለፈ ህልውናቸውንም ሆነ የቀን ተቀን እቅስቃሴያቸውን የሚያስተጓጉል ነገር ከመንግስት በኩል አይደረግም።

ለትርፍ ያልተቋቋሙ መሆናቸውም ሌላው የሲቪክ ማህበራት መለያ ነው። የማበራቱ ዋና አላማ ትርፋማነት ሳይሆን የሰፊውን ህዝብ የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ ግንዛቤውን ማሳደግ፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችን መስጠት አይነት





በጎ አድራጎት የሚያደላበት ሥራ ይሠራሉ። አመሠራረታቸውም በአባላት በጎ ፈቃድ ላይ የሚመረኮዝ ነው።

ሶስተኛው እና ለብዙ ክርክር ተጋላጭ የሆነው ተፈጥሯቸው ከፖለቲካ አቋም ገለልተኛ የመሆናቸው ነገር ነው። የሲቪክ ማህበራት ከፖለቲካ አቋም ገለልተኛ መሆን አለባቸው የሚለው ሃሳብ ትክክለኛ ትርጉም ማህበራቱ በምርጫ ተወዳድረው የመንግስት ስልጣን የመያዝ አላማ የላቸውም፣ በሃገራዊ ምርጫ ወቅት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች መሃል የተወሰነውን ለይተው የተለየ ወገንተኝነት አያሳዩም፣ እንደ ፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ፕሮግራም አይኖራቸውም ለማለት እንጂ ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ የተገለሉ ናቸው ማለት አይደለም። ከተጠቀሱት ፖለቲካዊ አውዶች በመለስ ባሉት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ ይችላሉ። በሰለጠነው አለም ሲቪክ ማህበራት በአንድ ሃገር ፖለቲካ ውስጥ ያላቸው ሚና ላቅ ያለ ነው። በምዕራቡ አለም እንደ ፀረ-የቀለም መድሎ፣ የፆታ እኩልነት ወዘተ አይነት የሲቪል መብት እንቅስቃሴዎች በሲቪክ ማህበራት ጠንካራ ድጋፍ የተከናወኑ እና ስኬት ያገኙ ናቸው። በነዚህ ሃገራት የሲቪክ ማህበራት ህዝባዊ መግባባትን ከማምጣት፣ ጠቃሚ ማህበራዊ እሴቶችን ከመገንባት፣ ህዝባዊ ትስስርን ከመፍጠር አልፈው የመንግስት ለውጥን ከማገዝ አንፃር ትልቅ ሚና አላቸው። የቅርቡን ሁነት እንደ አስረጅ ብንወስድ እንኳን ትቂት አመታትን ቀደም ብሎ ተፋፍሞ የነበረው የዐረብ ሃገራት አብዮት በከፍተኛ ሁኔታ የሲቪክ ማህበራት ድጋፍ ነበረው።

ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና መለያዎች ያሏቸው የሲቪክ ማህበራት ብዙውን ጊዜ አላማቸውን መሰረት በማድረግ ራስ አገዝ (Self-help Civic Organizations)፣ ምግባረ ሰናይ (Charity Civic Organizations) እና የማህበረሰብን ንቃትን ለማሳደግ የተቋቋሙ (Advocacy Civic Organizations) ተብለው በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። ራስ አገዝ የሚባሉት የሲቪክ ማህበራት ተመሳሳይ ማኅበራዊ ማንነት ያላቸው ሰዎች አብሮ ለማደግ እና ተመሳሳይ ችግሮቻቸውን ለማስወገድ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩባቸው ማህበራት ሲሆኑ ሙያን፣ ጾታን፣ እድሜን፣ ወዘተ ያማከሉ ማህበራት ናቸው። እቁብ፣ እድር፣ ደቦ፣ ማህበር የመሳሰሉ የሃገራችን የቆዩ የመተጋገዣ ማኅበራት ከዚህኛው ወገን ይመደባሉ።

ምግባረ-ሰናይ የሚባሉት ደግሞ **የማህበረሰቡን** ችግር የሚያቃልሉ አገልግሎቶች የሚሰጡ እና የተቸገሩ **የህብረተሰብ ክፍሎችን** የሚረዱ ናቸው። የማኅበራዊ አገልግሎት እጥረት ባለባቸው ቦታዎች የትምህርት፣ የጤና፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት አቅርቦት፣ የምግብ እህል እርዳታ የሚያቀርቡ ተቋማት ምድባቸው ከዚህኛው አይነት ነው። ሶስተኛው እና በአምባገነን መንግስታት ዘንድ በአንክሮ የሚታው የሲቪክ ማህበራት አይነት የማህበረሰቡን ማህበረ-ፖለቲካዊ ንቃት በማሳደግ እና ዲሞክራሲን ለማስፈን በሚያግዙ ክንዋኔዎች ላይ የሚሰራው ነው።

## 2.2 የሲቪክ ማህበራት ሚና

የሲቪክ ማህበራት በተቋቋሙለት አላማ መሰረት የተለያየ ሚና ይኖራቸዋል። የሙያ ማህበራት እና ሌሎች ራስ አገዝ ማህበራት የአባሎቻቸው ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እንዲሻሻል ይሰራሉ። እነዚህ ማህበራት የመንግስት ፖሊሲዎች ለአባሎቻቸው ኑሮ መሻሻል እንዲመቹ ሆነው እንዲወጡላቸው ይወተውተውታሉ፣ የአባላቱ መብት የሚከበርበትን መንገድ ያመቻቻሉ። ይህ በማይሆንበት ሰዓት ፍላጎታቸው ይሟላ ዘንድ መንግስትን አጠንክረው ይሞግታሉ። በመሆኑም በማህበር ካልታቀፉ ባለሙያዎች፣ ሰራተኞች ወይም ሌላ የህብረተሰብ ክፍሎች ይልቅ በጠንካራ ማህበር ጥላ ስር ያሉቱ በተሻለ ሁኔታ መብታቸውን የማስከበር አቅም እና ተሰሚነት አላቸው። መንግስት ሰምቶ ለችግራቸው ተገቢውን መልስ የማይሰጥበት አጋጣሚ ከተፈጠረም በማህበራቸው አማካይነት እንደ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የአቋም መግለጫ፣ የስራ ማቆም አድማ አይነት ሰላማዊ መንገዶችን ተጠቅመው የመንግስትን ትኩረት ለማግኘት ይችላሉ። ማህበራት በዚህ መንገድ የአባላቶቻቸውን መብት ሲያስከብሩ እግረ-መንገዳቸውን በሃገራቸው ዲሞክራሲ እንዲያድግ የሚያደርገውን መብትን የማወቅ እና የማስከበር ሚና እየተወጡ ነው። ለዚህ ነው የጠንካራ ማህበራት መኖር በአንድ ሃገር ውስጥ ዲሞክራሲን ለማሳደግ ለሚደረገው ጥረት ትልቅ ሚና አለው የሚባለው።

ማህበረሰብን የማንቃት ዋና አላማ ይዘው የሚሰሩ የሲቪክ ማህበራት (Advocacy Civic organizations) ከራስ አገዝ ማህበራት ላቅ ባለሁኔታ ዲሞክራሲን ከማስፈን አንፃር ትልቅ ሚና አላቸው። ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ራስ አገዝ የሲቪክ ማህበራት ዋነኛ ግባቸው የአባላቶቻቸውን ህይወት ማሻሻል



ስለሆነ በዋናነት ትኩረት የሚያደርጉት በአባሎቻቸው ዲሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶች መከበር እና የኑሮ መሻሻል ላይ ነው። ይህ ማለት ግን በሃገራቸው በሚደረገው ፖለቲካዊ ሁነት ላይ የድጋፍ ወይም የተቃውሞ ድምፅ ማሰማት አይችሉም ማለት አይደለም። መንግስት የሰፊውን ህዝብ መብቶች የጣሰ በመሰላቸው ጊዜ ወይም መንግስት ህገ-መንግስቱን ጨምሮ ሌሎችን ህጎችን እንዳላከበረ በታያቸው ሰዓት ማህበራቱ ተቃውሟቸውን ይገልፃሉ። እንዲሁም መንግስት አበጀህ የሚያስብል ተግባር በሰራ ጊዜ ድጋፋቸውን የመግለፅ መብት አላቸው። ይህ ተግባራቸው የዲሞክራሲን ባህል ከማጎልበት አንፃር ጉልህ ሚና የሚጫወት ቢሆን ህብረተሰብን የማንቃትን ስራ ዋነኛ አላማቸው አድርገው የሚሰሩ የሲቪክ ማህበራት የዲሞክራሲን ባህል ከማሳደግ አንፃር ከራስ አገዝ የሲቪክ ማህበራት ላቅ ያለ ድርሻ አላቸው።

ማህበረሰባዊ ንቃትን እና ዲሞክራታይዜሽንን ለማስፋፋት ከሚሰሩ የሲቪክ ማህበራት ወገን የሆኑ ተቋማት በተለያየ ማህበራዊ ዳራ ውስጥ ላሉ ህዝቦች መብታቸውን ያውቁ ዘንድ፣ አውቀውም የማስከበር ድፍረት እንዲያሳድጉ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን ይሰጣሉ። በተለያየ ምክንያት ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች (ህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች....)ደግሞ መብታቸውን ያስከብሩ ዘንድ የገንዘብ እና የሙያ ድጋፍ ደርጋሉ። ይህን መሰሉ የተቋማቱ ተግባር ህፃናትን ጨምሮ በአንድ ሃገር ውስጥ የሚኖሩ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መብታቸውን እንዲያውቁ ያደርጋልና ዜጎችም መብታቸውን ለማስከበር ንቁ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ መንግስትን ጨምሮ የዜጎችን መብት ለመሸራረፍ ለሚሞክሩ ክፍሎች ታላቅ ተግዳሮት ነው። አምባገነን መንግስታት በተለይ ግንዛቤ በማስጨበጥ ስራ ላይ ከተሰማሩ የሲቪክ ማህበራት ጋር ከከባቸው የማይገጥመውም ለዚሁ ነው።

ለሰፊው ህዝብ መብቱን ከማሳወቁ ጎን ለጎን ማህበራቱ ዲሞክራሲን ከማስፈን እና የዜጎችን መብት አክብሮ ከማስከበር አንፃር የመንግስት አካሄድ እና ቁርጠኝነት ምን እንደሚመስል ተከታትለው ጉድለት ያለ ሲመስላቸው መንግስት አካሄዱን እንዲያስተካክል ያሳስባሉ፣ ይተቻሉ። ሃገራዊ ምርጫ ሲኖርም የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት ተከታትለው ይታዘባሉ፣ ሪፖርትም ያደርጋሉ። በተጨማሪም የምርጫ ክርክሮች እና መሰል የውይይት መድረኮችን

እስከ ቀበሌ በመውረድ ያስተምር ነበር። በዚሁ እንቅስቃሴው ተማሪዎች፣ የማህበረሰብ መሪዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ ፖሊሶች፣ የህግ ባለሙያዎች፣ የእስር ቤት ሰራተኞች፣ የመንግስት ባለስጣናት እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በሰብዊ መብቶች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ድርጅቱ ብዙ ስራዎችን ሰርቷል። በተጨማሪም በሃዋሳ እና በባህርዳር ቤተመፅሃፍትን ከፍቶ በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ አካላት የማጣቀሻ መፃህፍትን እና ሌሎች መዛግብት ሲያቀርብ ቆይቷል።

ዲሞክራሲዊ ስርዓት ባልተገነባበት ሃገር ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር አዳጋች በመሆኑ ኢሰመጉ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዋና የሆነውን የምርጫ ስርዓት በመታዘብ እና ሪፖርቶችን በማጠናቀር ተግባር ላይ ትልቅ ተሳትፎ ሲያደርግ ቆይቷል። በተጨማሪም በሃገሪቱ የምርጫ ህግ ዙሪያ ለመራጮች፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ ጋዜጠኞች እና የሲቪክ ማህበራት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናሮች ያዘጋጅ ነበር። ለዚሁ ስራ የሚውል የገንዘብ አቅም ከባህር ማዶ በሰፊው ያገኝ የነበረው ኢሰመጉ ቅርንጫፍ መስሪቤቶቹን እያደር በማስፋፋት በ2001ዓ.ም ወደ 12 አድርሶ በስሩ 58 ባለሙያዎችን ቀጥሮ ያሰራ ነበር። ከሰራተኞቹ ውስጥ 16ቱ የሰብአዊ መብት ጉዳዮች ምርመራ ባለሙያች ነበሩ። ሰመጉ በአርባምንጭ፣ አሰላ፣ ባህርዳር፣ ደሴ፣ ድሬዳዋ፣ ጋምቤላ፣ ጎንደር፣ ሃዋሳ፣ ጅማ፣ ጂጂጋ፣ መቀሌ እና ነቀምት ቅርንጫፍ መስሪያቤቶች የነበሩት ሲሆን ከተሞቹ የተመረጡት በአንፃራዊነት የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚበረክትባቸው ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ነበር ሲል ከላይ በተገለፀው ድርሳኑ ያስረዳል። አዲስ አበባ በሚገኘው ዋና መስሪያቤቱም ሆነ በቅርንጫፍ ቢሮዎች አማካይነት በ9000 ሰብአዊ መብት ጥሰቶች ጉዳች ላይ ክትትል አድርጎ ሪፖርቶችን ይፋ አድርጓል፣ 34 ቋሚ እና 17 ልዩ ሪፖርቶችንም አውጥቷል። ሪፖርቶቹም ለሃገር አቀፍም ሆነ ለአም አቀፍ ድርጅቶች ዋቢ ሆነው እንዳገለገሉ የኢሰመጉ ሪፖርቶች ያመለክታሉ።

በዚህ ሁሉ ጉዞው ውስጥ ድርጅቱ ገለልተኛ ለመሆን አብዝቶ ቢጥርም ከመንግስት በኩል በድጋፍ ፋንታ ማስፈራራት እና ወከባ እንደሚያስተናግድ የኢሰመጉ አባላት ሰርክ የሚናገሩት ነው። ድርጅቱ ምርጫን እና ሌሎች ሃገራዊ ሁነቶችን ተከትሎ የሚያወጣቸው ሪፖርቶች ከመንግስት ጋር ያለውን ግንኙነት የባሰ የሚያሻክር ሆኗል። ኢሰመጉ ገለልተኛ ለመሆን እንደሚጥር አባላቱ ይናገሩ እንጅ መንግስት በበኩሉ ሪፖርቶቹን ከመቀበል ይልቅ በድርጅቱ የተፈበረኩ ሃሰተኛ ድርሰቶች ናቸው ማለቱ ይቀናዋል።



## አምሳስ ህግ ወጀብ?!

በ1999 ዓ.ም በሃገራችን ወደ 127 የሚጠጉ በመብት ላይ የነበሩ የሲቪክ ማህራት እንደ ነበሩ ኢሰመጉ ከሁለት አመት በፊት ባወጣው ሰነድ ያስረዳል። በ2000ዓም የሰቨክ ማህበራት ህግ ከወጣ በኋላ በሰብአዊ እና ዲሞክራሲዊ መብቶች፣ በህፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች መብቶች እና እኩልነት፣ በግጭት አፈታት እና እርቅን ማስፋፋት፣ በህግ የበላይነት ዙሪያ የሚሰሩ ማህራት በስራቸው እንቀጥላለን ካሉ 90 የበጀት ምንጫቸውን ከሃገር ውስጥ ማድረግ አለያም የትኩረት አቅጣጫቸውን በልማት ዙሪያ ብቻ እንዲያደርጉ የሚል አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ። ከ127ቱ ድርጅቶች ውስጥ በመብት ዙሪያ በመስራቱ እንደሚቀጥል አስታውቆ በበጀት እጥረት ድቀት ውስጥ ሆኖም ቢሆን ከፋኙ ህግ መውጣት በኋላም ህልውናውን ጠብቆ የቆየው ኢሰመጉ ብቻ ነው።

ሆኖም በ2000 ዓ.ም የወጣውን የሲቪክ ማህበራት ህግ ተከትሎ ኢሰመጉ በበጀት ድርቅ በመኖር እና ባለመኖር መሃል እየተላጋ ይገኛል። በበጀት እጥረቱ ሳቢያ በሃገሪቱ አብዛኛ ክልሎች ከነበሩት 12 ቅርንጫፍ መስሪቤቶች ወደ 3 አሽቆልቁለዋል። ከአዋጁ አንድ አመት በፊት የነበሩትን 58 ባለሙያዎችን ደሞዝ ከፍሎ ማሰራት ስለተሳነው ቀንሶ ወደ 12 አድርሷቸዋል። የባለሙያዎቹ መቀነስ የድርጅቱን ዋና ዋና ዲፓርትመንቶች መታጠፍን አስከትሏል። የቅርንጫፍ ቢሮዎችን ማስፋፋት እና አባላት ምልመላ ዲፓርትመንት፣ የውጭ ግንኙነት እና ኮሚኒኬሽን ክፍል፣ የሰብአዊ መብት ትምህርት እና ማስከበር ዩኒት፣ ተጎጅዎችን በህግ አገልግሎት በኩል የመደገፊያ ዩኒት፣ የዕቅድ እና ፕሮጀክት ዝግጅት ክፍል ከታጠፉት ክፍሎች ውስጥ ናቸው። አንድ በሰብአዊ መብቶች ዙሪ የሚሰራ ተቋም እነዚህን ክፍሎች ከዘጋ እንዴት የተቋቋመለትን ዋነኛ ግብ መምታት ይቻለዋል? ቅርንጫፍ መስሪቤቶች ከ12 ወደ 3 ማነስም ሌላው ጉዳት ሲሆን የድርጅቱን ስም ከኢሰመጉ ወደ ሰመጉ የቀየረውም ይሄው ነው። (በ ሲቪክ ማህበራት ህጉ መሰረት ከአምስት ክልሎች በታች የሚሰራ ድርጅት የኢትዮጵያ የሚለውን ቅጥያ መያዝ አይችልም)። ሰመጉ ወደሚል መጠሪያ ያነሰው ኢሰመጉ ያከበትን አደጋ የሚያሳየው በበጀት እጥረት ምክንያት የድርጅቱ ሸራተኞች በቀን ከ 30 ደቂቃ በላይ ኢንተርኔት መጠቀም አይችሉም። የድርጅቱ ወርሃዊ የስልክ ባጀትም ወደ 120 ብር ወርዷል። ድርጅቱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመመርመር የሰብአዊ መብት

ጥሰቱ የተደረገበት ቦታ በአካል ከመገኘት በተጨማሪ የጉዳቱ ሰለባዎችን ለማግኘት ድህረገፆችን እና የስልክ ግንኙነቶችን በብዛትከመጠቀሙ አኳያ ይህ አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

በሲቪክ ማህበራት ህግ የተቀመጠው የበጀት አደላደሉ በ90/10 ብቻ አያበቃም። ሌላ 70/30 የሚባል የበጀት ክፍፍልም አለ። የበጀታቸውን 90 ከሃገር ውጭም ሆነ ከሃገርቤት ያደረጉ ማህበራት ያገኙትን በጀት 70 እና በላይ ለስራ ካፒታል ባጀት መመደብ ሲኖርባቸው ቀሪውን 30 እና በታች ደግሞ የሰራተኛ ደሞዝን ጨምሮ ለሌሎች የስራ መስኬጃ ተግባራት እንዲያውሉ ያስገድዳል። ለአስተዳዳደራዊ ተግባራት የተመደበው ባጀት ማነስ ማህበራቱ ተጨማሪ ቅርንጫፎችን ከፍተው፣ ባስፈላጊው መጠን ባለሙያወችን ቀጥረው ከመስራት ያግዳል።

የትኩረት አቅጣጫውን ከሰብአዊ መብቶች ወደ ልማት መቀየርን ያልወደደው ኢሰመጉ ከሃገር ውስጥ ለጋሾች በጀት የማፈላለጉ ነገር እንዳይሳካለት የሲቪክ ማህበራት ህጉ ሌላ ተግዳሮት አስቀምጦለታል። ይህም ከሃገር ውስጥ ማህበሩን የሚያግዙ ግለሰቦችንም ሆነ ድርጅቶችን ሙሉ ማንነት መግለፅ እንደሚጠበቅበት ህጉ ይደነግጋል። ማህበሩ ከመንግስት ጋር ባለው የሻከረ ግንኙነት ሳቢያ የለጋሾቹን ደህንነት አደጋ ላይ ላለመጣል ማንነታቸውን ከመግለፅ ከዘገየ ደግሞ ከ20000-50000 ብር የሚደርስ ቅጣት እንደሚጠብቀው ይሄው ህግ ያዛል። ይህን መሰሉ የመንግስት ቁጥጥር ባይኖር እንኳን የሲቪክ ማህበራትን ጥቅም በቅጡ አውቆ የመደገፉ ልምድ እምብዛም ባልደገበት በሃገራችን ሁኔታ በድፍረት ማህበሩን ለመርዳት የሚዘረጋ እጅ መጠበቅ ቀቢፀ ተስፋ ነው። በመሆኑም ሃገራችን በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ በመስራት ፋና ወጊ የሆነው እና በታላቁ የአደባባይ ምሁር ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ከፍተኛ ጥረት ተመስርቶ ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎች በጎ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየው ኢሰመጉ አሁን በመጥፋት ስጋት ላይ ይገኛል።

የገንዘብ እጥረቱ ያመጣውን ችግር ለማወገድ እና መንግስት ያወጣው የ10/90 ህግ በኢሰመጉ ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሰመጉ በ1991 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ያወጣውን መግለጫ በመጥቀስ መንግስትን ለማሳመን ጥረት ማድረጉን ድርጅቱ በ2000 ዓም ባወጣው የማሻሻያ ሃሳቦችን በያዘው ጥራዝ ያስነበባል። እንደ ጠቅላላ ጉባኤው መግለጫ ማንኛውም ሰው በግል



ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ሰብአዊ መብቶችን ለማስፋፋት እና ለማስከበር በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ ከማንኛውም ወገን ገንዘብ የመጠየቅ፣ የመቀበልና ስራ ላይ የማዋል መብት አለው። ይህ መግለጫ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በገንዘብ እጥረት ምክንያት ብቻ ስለሰብአዊ መብቶች ከማስተማር፣ ሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን ከመከታተል እና ከመሳሰሉ ለማህበረሰብ እድገት እና ለዲሞክራሲ ግንባታ የሚስፈልጉ እንቅስቃሴዎች እንዳይገቱ ለማድረግ የተደረገ እርምጃ ነው።

## የኢህአዴግ መንግስት አቋም

የተባበሩት መንግስታት መስራች እና አባል የሆነችው ሃገራችን መንግስት በበጀት ድርቅ ማህበራቱን የሚያንገላታውን የሲቪክ ማህበራት ህግ አለማቀፋዊ ተቀባይነት ያለው እና በሃገሪቱ ፖለቲካዊ ክበብ ውስጥ የውጭ ጣልቃገብነትን የሚያስቀር በማለት ትክክለኛነቱን አበክሮ ይገልፃል። በ2001 መስከረም-ጥቅምት በወጣው የመንግስት ልሳን በሆነው አዲስ ራዕይ መፅሄት ቅፅ 2 እትሙ ገፅ 27 ስለ ህጉ የበጀት ድልድል ትክክለኝነት የሚከተለውን ያስነበባል «በየትኛውም ዲሞክራሲያዊ ሃገር እንደ አሜሪካ ባሉት ሃገራት ጭምር የፖለቲካ ፓርቲዎች ዜሮ አምስት ሳንቲም ከውጭ ዜጎች ከተቀበሉ በህግ የሚቀጡበት ምክንያት ገንዘቡ ከየትም ይምጣ ከየት ፓርቲው የአሜሪካ ዜጎች እስከፈጠሩት እና እስከመሩት ድረስ አሜሪካ ነው ተብሎ መደምደም ስለማይቻል ነው። ፓርቲዎች በውጭ ገንዘብ መንቀሳቀስ አይችሉም የሚባልበት ምክንያት የእያንዳንዱ ሃገር ፖለቲካ ከውጭ ተፅዕኖ ነፃ መሆን ስላለበት ነው። የብዙሃን ማህበራትም በሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ ከፓርቲዎች የማይተናነስ እጅግ ቁልፍ የሆነ ድርሻ አላቸው። ስለሆነም እንደ ማንኛውም የፖለቲካ ተዋናይ ሁሉ ከውጭ ገንዘብ እና ከውጭ ተፅዕኖ ነፃ መውጣት አለባቸው። »

ይህ የመንግስት አባባል በማወቅም ይሆን ባለማወቅ ፖለቲካን እና የፓርቲ ፖለቲካን አንድ እና ያው አድርጎ ለማየት ይቃጣዋል። ከፍ ብሎ የተገለፀው የመንግስት ሙግት ዲሞክራሲን ለመገንባት እና የዜጎችን መብቶች ለማስከበር ሲሆን ብቻ የፖለቲካ ስራ የሚሰሩ የሲቪክ ማህበረትን መንግስታዊ ስልጣን ለመያዝ ከሚንቀሳቀሱ እና የፓርቲ ፖለቲካን ከሚያራምዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተገቢ ባልሆነ መንገድ ያዳብላል። ለፓርቲዎቹ የተከለከለውን

## 3.2 ፋኖው መለስ

አቶ መለስ በጫካ ትግል ቆይታቸው በጦር ሜዳ ጀብዱ በመስራት ብዙ አይታወቁም። እንደውም የጫካው ህወሃት ሂሳብ ሹም የነበሩት አቶ እየሩሳሌም ጌታቸው «ነፍሱን በጨርቅ መቋጠር የሚቀረው» ሲሉ ከመሞት መሰንበት ባይ፣ ነፍሳቸውን ወዳድ እንደ ነበሩ «የሀገር ልጅ» ለተሰኘው የኢሳት ፕሮግራም በአንድ ወቅት ገልፀዋል። አቶ ኢየሩሳሌም በተቃራኒው ወ/ሮ አዜብን «በተፋፋመ ጦርነት ለመማገድ የማትፈራ ጀግና ነበረች፣ ዘወትር በጦርነቱ ለመሳተፍ ስትፈልግ እሱ ነበር እየለመነ የሚያስቀራት፤ አንዳንዴ ግን እምቢ እያለችው ትሄድ ነበር» ይላሉ። አቶ መለስ ራሳቸውም በትግሉ መጀመሪያ አመታት በተወሰኑ ግንባሮች ተሳትፌያለሁ ይሉነበር እንጂ በትግሉ ዘመን ሁሉ ከጠላት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቄ ተዋግቻለሁ፣ በጥይት በሳንጃ ጠላት አርበደብድ ነበር ብለው አያውቁም።

አቶ መለስ ብዙውን የጫካ ህይወታቸውን በፖለቲካው ኮሚሳርያት ክፍል ነበር ያገለገሉት። ሁሉም ሰው ጦር ሜዳ ወርዶ መዋጋት ላይኖርባቸው ይችላልና አቶ መለስ መድፍ ማገላበጡ ባይሳካላቸው መፅሃፍ አገላብጠው፣ ሀልዮት ባይፈጥሩም የነማርክስን ሃልዮት እንደሚመች ደውረው ሰራዊቱን ለአላማ በመፅናት ስም ነፍስን ከምንም እስካለመቁጠር በዘለቀ መሰጠት ህወሃት/ኢህአዴግን አዲስ አበባ እንዲያደርስ አድርገዋል። ይህ ለህወሃት ትልቅ አበርክቶት ነው።

መትረይስ ከማናገር መውዜር ከመታጠቁ ሰራዊቱን በምስራቃዊ ርእዮት አለም ወደ ማስታጠቁ መዞራቸው ለአቶ መለስ በግልም ብዙ ጠቅሟቸዋል። ብዙጊዜያቸውን በማንበብ እንዲያሳልፉ አድርጓቸዋል። ማንበባቸው የርእዮት አለም ትጥቃቸውን ከማጥበቁ ባሻገር ማለት የፈለጉትን ንባብ በሳለው ርቱዕ አንደበት አሳምረው እንዲናገሩ፣ ተናግረውም እንዲሰሙ፣ በሰራዊቱ ዘንድም ወደር የለሽ ምጡቅ፣ አዋቂ ተደርገው እንዲታሰቡ ረድቷቸዋል። በሰራዊቱ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት እያደር እያደገ መምጣቱ በእድሜም፣ በችሎታም ላቅ የሚሉዋቸውን እንደነ አረጋይ በርሄ እና ግደይ ዘርአፅዮን አይነት ቀደምት ታጋዮችን አስወግዶ ፊት ለመሆን ትግላቸው ክንዳቸውን አበርቶላቸዋል።

በጫካ ትግሉ ወቅት የወታደሩ ክንፍ በፖለቲካ ኮሚሳሪያቱ ስር ስለነበር የፖለቲካ ኮሚሳርያቱን ቁንጮነት የተቆናጠጡት መለስ በተለይ በኋለኞቹ



የትግል ዘመናት የህወሃት ዋና ሰው እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። በጦር ሜዳ ከጦሩ ጋር ወድቀው ተነስተ ከታገሉት የጦሩ ፊትአውራሪዎች በላይ በስልጠና፣ ፕሮፖጋንዳ እና ርእዮተአለም ስርፀት ስራ የተካኑት ተናጋሪው መለስ ተፅእኖ መፍጠር ችለው እንደነበር የህወሃትን ትግል የሚዘክሩ ከቅርብ አመታት ወዲህ በብዛት እየታተሙ ያሉ ድርሳናት ይጠቁማሉ።

## 3.3 በምስራቅ - ምዕራብ መስህብ መዋተት

እንደሃገራችን አቆጣጠር በ 1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ በሃገራችን የነበረው የፖለቲካ ንፋስ በማርክሲስት ሌኒኒዝም ርዕዮት የተቃኘ ስለነበር በዚሁ ዘመን ትግል የጀመረው ህወሃትም ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን መመሪያው እንዳደረገ በ1968ቱ ማኒፌስቶው ላይ እንዲህ ሰፍሯል፡ «ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስ የላብ አደር ርዕዮተ-አለም መሆኑን በማመን በአሁኑ ጊዜ የሚካሄደውን አብዮት ከግቡ ሊደርስ የሚችለው ይህንን መመሪያ በማድረግ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ ...ወዝ አደሩንና ደሃ ገበሬውን ለማደራጀት በቅድሚያ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የሆነ የፖለቲካ ማህበር ያስፈልጋል።» (ገፅ. IX-X) ወደ ሰባዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ አካባቢ ደግሞ ትግራይን ነፃ ካወጣሁ በኋላ የአልባኒን አይነት ሶሻሊዝም በነፃይት ትግራይ እመሰርታለሁ ሲል ማሌሊት መመሪያየ ነው እንዳለ እና ማሌሊትን በማቀንቀኑ በኩል ደግሞ አቶ መለስ ቀዳሚ እንደነበሩ «ከሃገር በስተጀርባ» የሚለው የአስራት አብርሃም መፅሃፍ ያስነብባል።

በዚህ ሁኔታ አብዛኛውን የጫካ ቆይታቸውን በምስራቃዊ ፖለቲካ ዘይቤ አድርገው የቆዩት አቶ መለስ አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ሲታያቸው እና የምስራቃዊው ርዕዮት ሲንኮታኮት አንድ ሆነ። አዋጭው መንገድ እየነጋለት ካለው ምዕራባዊነት ጋር መመሳሰል መሆኑ የተከሰተላቸው አቶ መለስ እንደፈረጆቹ አቆጣጠር በ1990 ወደ ምእራባዊኑ አውራ ሃገር አሜሪካ ገሰገሱ። የጉዞዋቸው ዋና አላማ ደርግን ጥለው ለሚመሰርቱት መንግስት ግልፅ የሆነ የአሜሪካ እዳታ ስለሚያስፈልጋቸውና ያንን ለማስተማመን መሆኑን በወቅቱ የአሜሪካ ፀጥታ ምክርቤት ባልደረባ ለነበሩት እና በቅርቡ በሞት የተለዩት ወዳጃቸው ፖል ሄንዝ ባደረጉላቸው ቃለ ምልልስ ገልፀዋል።

በቃለ-ምልልሱ ሄንዝ ለአቶ መለስ ወሳኝ ጥያቄዎችን አቅርቦ ነበር። የቃለ-ምልልሱ ሙሉ ቃልም ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ ትኩረት በሚያደርጉ ድህረገፆች

ላይ ይገኛል። በሶስት ዙር በተደረገው ቃለ-ምልልስ ሄንዝ የአቶ መለስን እና የድርጅታቸው ህወሃትን ምስራቃዊ የፖለቲካ ማንነት ሲጠይቃቸው «ድርጅታችን ምስራቃዊነትን አያውቅም፣ ማርክሲስት ሌኒኒስትነትን የሚገልፅ አንዳችም ቅጥያ በድርጅታችን ስም ላይ የለም፤ ምናልባት እኛ በግል ማርክሲዝምን እናምን ይሆናል እንጂ» ሲሉ ነበር እንመሰርተዋለን ሲሉት የኖሩትን ማሌሊትን ዶሮ ሳይጮህ እንደ ጴጥሮስ ደጋግመው የካዱት። ነገሩ ያልጣመው ሄንዝ «ደጋግማችሁ ማርክሲስት ነን ትሉ ነበር፣ እንደውም የአልባኒያን ሶሻሊዝም አርአያ ትግራይ ላይ እንደግማለን ትሉ ነበር» ሲል ሲሞግታቸው አቶ መለስ «እኛ የቻይናንም ሆነ የራሽያን አለያም የአልባኒያን ሶሻሊዝም በህዝባችን ላይ የመጫን እቅድ የለንም» ብለው ከእውነታው የማይገጥመውን ሶሻሊስት አይደለንም ሚለውን አቋማቸውን አጠናክረዋል።

ቃለምልልሱ ከተደረገ ከአንድ አመት በኋላ አዲስ አበባ የገባው ኢህአዴግ ልማታዊ መንግስት ሆነክ እስካለበት ድህረ ምርጫ 1997 ድረስ ነጭ ካፒታሊዝምን እንደሚከተል አቶ መለስ ደጋግመው ይናገሩ እንደነበር «ዳንዲ» በሚለው መፅሃፍ ላይ ዶ/ር ነጋሶ ገልፀዋል። ካፒታዝምን መከተሉ የምእራባዊያንን ዲሞክራሲ ማስፈንን፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በመንግስት መዳፍ ከመዘወር ለገበያው ሁኔታ መተውን ስለሚጠይቅ እና ይሄ ደግሞ ውስጠ-ማርክሲስት ለሆነው ኢህአዴግ በቀላሉ የማይለመድ መሆኑ ኢህአዴግ አይኑን ሙሉ በሙሉ ከምእራባዊያን ላይ ባያነሳም ቀደምት ምስራቃዊነቱ ከልቡም ስቦት በቅርቡ ወደ ቻይና ጠጋ ጠጋ ማለት ጀመረ። መሪው አቶ መለስም ቻይናን ከኢትዮጵያ አልፋ ከአፍሪካ ጋር ወዳጅነቷን እንድታጠብቅ በአፍሪካ መድረክ በመወትወት አፍሪካ-ቻይና ወዳጅነትን እውን አደረጉ። የወዳጅነቱ ሁኔታ ቻይናን አንዷን ሀገር አግዘፎ አህጉር ከሆነው ከአፍሪካ ጋር መሳ ያደረገ ያጋደለ ወዳጅነት ነው።

## 3.4 የጫካው እና ከተሜው መለስ

አስራ ሰባት አመታትን በጫካ ትግል ያሳለፈው ህወሃት/ኢህአዴግ አዲስ አበባ ከገባ በኋላም የሚያሳየው የአመራር ዘይቤ ከጫካው አመራር ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ አቶ አስገደን ጨምሮ ከድል በኋላ ኢህአዴግን የተለዩ የቀድሞ ታጋዮች በፅሁፍም ሆነ በሚሰጧቸው ቃለ-ምልልሶች ይገልፃሉ። ይህ መመሳሰል በትጥቅ ትግሉ ወቅት በተለይ በመጨረሻዎቹ ዘመናት የፖለቲካው ክንፍ ዘዋሪ የነበሩት አቶ መለስ ከድል በኋላም በመሪነቱ በመሰንበታቸው ይሆናል።



የጫካው መለስ ሁልጊዜ አሸናፊነትን ብቻ ስንቀው የሚነሱ፣ ከእሳቸው ሃሳብ በተቃራኒ የቆመን ሁሉ ተጨባጭ በሆነም ባልሆነም ፍረጃ ከጨዋታ ውጭ እንደሚያደርጉ፣ የተቀናቃኛቸውን ግበአተመሬት ለመፋጠን ዋና ዋና መርሆችን እንኳን ከመጣስ እንደማይመለሱ የቀድሞ የትግል አጋራቸው እና የዚህኛው የአቶ መለስ ስብእና ሰለባ የሆኑት አቶ አረጋይ በርሄ አቶ መለስ ባረፉ ሰሞን ለቪኦኤ በሰጡት ሰፊ ቃለምልልስ ገልፀዋል። አቶ ግደይ ዘርአፅዮንንም አቶ መለስ ‹ህወሃት ገላ ላይ የበቀለ ጋንግሪን ስለሆነ እሱ ካልተቆረጠ ህወሃት በህይወት አትኖርም› ብለው እንዳሰናበቷቸው በትግሉ ዙሪያ የተፃፉ መዛግብት ያትታሉ። ይሄ የአቶ ግደይ እና የአቶ አረጋይ እጣ በብዙ ለምን ባይ ታጋዮች ላይም ወድቆ እንደ እስራኤሉ ሙሴ የመሩት ትግል ወደተሰፋ ምድራቸው አዲስ አበባ ሳይደርስ ከመሃል መንገድ እንዲቀሩ አድርጓቸዋል።

የትግሉ ዘመን ገንዘብ ቤት የነበሩት አቶ እየሩስአሌም ጌታቸውም በተመሳሳይ አቶ መለስን ጠላታቸውን ለመወንጀል ራሳቸው ማያደርጉትን ሳይቀር እንደወንጀል ጠቅሰው የሚከሱ ሲሉ የሃገር ልጅ ለተሰኘው የኢሳት ፕሮግራም ገልፀዋል። በራሳቸው ላይ የደረሰውን እንደማስረጃ ሲገልፁም «ከ1977 በፊት በነበረው የትግሉ ወቅት ከተቃራኒ ጾታ ጋር የፍቅር ግንኙነት መጀመር ክልክል ቢሆንም እኔ በስህተት የጀመርኩትን ግንኙነት ደርሶበት ከሶ አስቀጥቶኝ ነበር። ይህንን ያደረገው ከእኔ ጋር አለመግባባቶች ስለነበሩ እንጂ ህጉን ለማስከበር አልነበረም ምክንያቱም በኋላ አዜብ ራሷ እንደነገረችኝ መለስ እና እሷ ከ1971 ጀምሮ ድብቅ የፍቅር ግንኙነት ነበራቸው» ይላሉ።

ከላይ ስለአቶመለስ የጫካ ስብዕና አፈንግጠው ከወጡት የቀድሞ የትግል አጋሮቻቸው ከሚሰማው በተቃራኒ ስለጫካው መለስ ትህትና፣ ተራማይሌ ሃሳብ አስተናጋጅነት፣ የሁሉን ሃሳብ አድማጭነት፣ ሃሳብን እንጂ ሰውን በክፉ የማያዩ እና ሚዛናዊ ውሳኔ ሰጭ መሪነት የሚመሰክሩ ፀሀፍትም ሆኑ የአይን ምስክሮች ሞልተዋል፡፡ የአቶ መለስን ፖለቲካዊ ስብዕና በተመለከተ በሁለት ተቃራኒ ጫፍ ላይ የቆሙ መረዳቶችን ለማመሳከር የከተሜውን መለስ አመራር ማጤኑ አማራጭ መንገድ ነው።

በግሌ የአቶ መለስን ጉራማይሌ ሃሳብ አስተናጋጅነት ትዕግስት እጠራጠራለሁ። ምናልባት እስከተወሰነ፣ የእሳቸውን ዋናነትእስካተፈታተነ ድረስ የተለየ ሃሳብን የሚቀበሉ ዲሞክራት መሪ ለመምሰል ይሞክሩ ይሆናል እንጂ ለሃሳብ የበላይነት እጃቸውን ሲሰጡ አልተስተዋለም። ይሄን ለማረጋገጥ ደግሞ በራሳቸው አንደበት ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች «ማሰሪያቸው ሲረዝም የተፈቱ ይመስላቸዋል» ሲሉ የገለጹትን እንደአስረጂ ማንሳት ይቻላል።

ጠቅለል ብሎ ሲታይ አቶ መለስን በተመለከተ ዘላቂ ወዳጆቻቸው ከሚያነሱት ፖለቲካዊ ማንነታቸው ይልቅ በነ አቶ አረጋይ የተገለፀው የጫካ ማንነታቸው በከተሜው መለስ ላይ ጎልቶ ይታያል። እንደ ግላዊ መረዳቱ አቶ አረጋይ ‹አቶ መለስ ባለጋራውን ለማጥቃት ማንኛውንም መርህ ሊጥስ ይችላል› ሳሉት ነገር እውነትነት በ1997 አቶ መለስ ስልጣናቸውን ለማትረፍ ሲያደርጉት የነበረው ዲሞክራሲያዊ መርሆችን የመጣስ የደመነፍስ ጉዞ ምስክር ነው።

በወቅቱ የተቃውሞው ጎራ መሪዎችን ከያሉበት እየለቀመ (ሲስፈልግም ቦክስ እየሰነዘረ) እስርቤት የሚያጉረው ፖሊስ በቀጥታ የሚታዘዘው በእሳቸው ነበር። የመንግስታቸው አካሄድ የህዝብ ቁጣ ሊቀሰቅስ እንደሚችል የተረዱት ነገር አዋቂው መለስ የዲሞክራሲ መርሆዎች አንዱ የሆነውን የመሰብሰብ መብት በገዛ አንደበታቸው ላልተወሰነ ጊዜ ብለው ለስምንት አመት እንደ እናት ጡት እንድንረሳው አደረጉ። ጋዜጠኞችን ለቃቅመው ሲያስሩም ከዲሞክራሲያዊ መርሆዎች አንዱ የሆነው ሚዛናዊ መረጃ የማግኘት መብት እየተጣሰነበር።

ከዘጠና ሰባት አለፍ እንበል ከተባለ ደግሞ ለኢህአዴግ ጆሮ የማይመቹ መረጃዎችን የሚያቀርቡ መገናኛ ብዙሃንን ስንት ሃብት አፍስሶ በሞገድ ከማፈን ጀምሮ እስከ ማተሚያ ቤት ድረስ ገስግሶ የውሃሽታ የማድረጉ እርምጃ ዲሞክራሲያዊ መርህ መጣሱ እንደ ቀጠለ ያመላክታል። ህገመንግስታዊ መርሆች ሳይቀሩ ነገሬ የማይባሉበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ሽብርተኝነትን ለመቆጣጠር ወጣ የተባለው አዋጅ፣ የመገናኛብዙሃን እና የሲቪክ ማህበራት ህጎች ለዚህ ምስክሮች ናቸው። ህገ መንግስት ተርጓሚ ተብሎ የተቀመጠው አካልም የአቶ መለስን አመራር የመሞገት ሞገስ ያለው አይመስልም - አይን በአይን ህገመንግስቱን የሚጥሱ ህጎች ሲወጡ በአንዱም ላይ ተቃውሞ ሲሰማ አልተደመጠምና።



አቶ እየሩሳሌም የጫካው መለስ ራሳቸው የሚያደርጉትን ነገር ሳይቀር እንደ ወንጀል ጠቅሰው ተቀናቃኞቻቸውን ይከሱ ይወቅሱበት ነበር ያሉት የአቶ መለስ ስብእና በከተሜው መለስ ውስጥም በጉልህ ይስተዋላል። ራሳቸው አቶ መለስ ይመሩት የነበረው ህወሃት ትግራይን ነፃ ለማውጣት ብረት አንስቶ አስራ ሰባት አመት መዋጋቱ እውነት ቢሆንም እሳቸው መንግስት ከሆኑ በኋላ የወጡበትን ብሄር ነፃ እናወጣለን የሚሉ ድርጅቶችን በጠባብነት ይፈርጁ ነበር። ነፃ አውጭ ነን ባዮቹ ብረት ያነሱ ከሆኑ ደግሞ የስድብ እርግማኑ መጠን ይጨምርና ጠባብ በሚለው ላይ የእንትን ተላላኪ፣ ሃገር አፍራሽ፣ ፀረ-ልማት፣ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ህዝብ የመሳሰሉ አጠልሽ ቅጥያወች ይጨመሩላቸዋል።

የአቶ መለስ ህወሃት እዚህ የደረሰው ለሻዕቢያ አቤት ወዴት ብሎ ቢሆንም አሁን ወደሻዕብያ ጠጋ ጠጋ የሚሉ የኢህአዴግ ባላንጣ ፓርቲዎች ስማቸው ሀገር ከዳተኛ ነው። በጫካ ሳሉ ኢትጵያን ሽራርፎ «ታላቋ ሶማሌ»ን ለመገንባት ደፋቀና ሲል የነበረው ዚያድባሬ በሰጣቸው የሶማሌ ፓስፖርት ሲንቀሳቀሱ እንደነበረ በገዛ አንደበታቸው የተናገሩት አቶ መለስ በተመሳሳይ መንገድ የሚሄዱ የዘመኑ ብረት አንጋች ተቃዋሚዎችን ሲየብጠለጥሉ ጊዜ አይበቃቸውም ነበር።

ተፈጥሯዊው የወጣትነት እድሜ የሚያመጣው ለውጥን መሻት ከዩኒቨርሲቲ ደደቢት ያበረራቸው አቶ መለስ የአሁን ወጣት ስለለውጥ እንዲያስብ አይፈልጉም ነበር። የሚፈልጉት በጥቃቅን እና አነስተኛ ተደራጅቶ የእሳቸው መንግስት ባሰበለት መጠን እንዲኖር ነው። እሳቸው እንዳደረጉት ስለውጥ እነሳለሁ ካለ ስሙ አደገኛ ቦዘኔ፣ የሆነ ሰው ተላላኪ (እንጂ በራሱ አስቦ ለውጥ የማይፈልግ)፣ የጎዳና ላይ ነውጠኛ ወዘተ ነው።

## 3.5 ፕሬዚደንት መለስ

የአስራ ሰባት አመቱን ትግል ደርግን በመጣል ያጠናቀቀው ኢህአዴግ አዲስአበባን ከተቆጣጠረ በኋላ የሽግግር ወቅት ባለው እና ራሱን ለዘመናት ስልጣን ባመቻቸበት አራት አመት አቶ መለስ የሀገሪቱ ፕሬዚደንት ነበሩ። በዚህ ወቅት ነበር ፓርቲያቸው ስልጣን ላይ የሚሰነብትበትን መደላድል በጥንቃቄ ያበጃጁት። የሽግግሩ ወቅት ሲያበቃ በሰላም እና ዲሞክራሲ ሃይሎች

እንደሌላው ህዝብ ተጨቋኞች ነበሩ እኛ ጨቋኝ አማራ የምንለው የሸዋ አማራን ሲሆን የምንዋጋው በአዲስ አበባ የሸዋ አማራን የበላይነት ለማቆየት የሚታገለውን ልማድ ነው። » ሲሉ የጨቋኝነቱን ጦስ ለሸዋ አማሮች ሰጡት። ይህኛው የአቶ መለስ አረዳድ ከ1997 ምርጫ በኋላ «ዲሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ በፃፉት ድርሳን የመቶ አመቱ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚጀምረው ከሸዋ አማራው ሳህለስላሴ (የአፄ ሚኒሊክ አያት) ቤተሰብ ታሪክ ጋር ነው ባሉት አባባላቸውም ይንፀባረቃል።

በአቶ መለስ የስልጣን ዘመን አማራ የሚለው ስም ትምክህተኛ ከሚል ቅፅል ጋር መጠራቱ የተለመደ ነበር። ኢትዮጵያን ከተወላጅ እኩል የሚያውቋት (ኢትዮጵያዊው ስሜ ሊበን ነው የሚሉት) አሜሪካዊው ሶሾሎጅስት ዶናልድ ሌቨን አቶ መለስን በብሄር ፖለቲካ ላይ ያላቸውን ትኩረት በማስተዋል ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን የሚያቀነቅኑ ኢትዮጵዊያንን ሃሳብ እንዴት ያዩታል ሲሉዋቸው ይህን የሚሉ በኢትዮጵያዊነት ስም የበላይነታቸውን ለማስጠበቅ የሚጥሩ ትምክህተኛ አማሮች ናቸው ሲሉ እንደመለሱላቸው ዶናልደ ሌቨን ከኢሳት ጋር በነበራቸው ቆይታ ተናግረዋል። ይህኛው የአቶ መለስ አባባል ከአማራ ብሄር ውጭ ያሉ ህዝቦች ያላቸውን የኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ስሜት የረሳ ነው።

በተመሳሳይ ወዳጃቸው አቶ መለስ በመንግስት የመሬት ባለቤትነት እና የዘር ፖለቲካ ላይ ያላቸውን አቋም እንደማይወዱላቸው የሚናገሩት በአሜሪካ የውጭጉዳይመስሪያቤት ውስጥ የአፍሪካ ጉዳዮች ሃላፊ የነበሩት ሄርማን ኮህን አቶ መለስን መንግስታቸው ለምን የመሬት ባለቤትነት በመንግስት እጅ እንዲሆን እንደወደደ ጠይቀዋቸው እንደነበረ ለኢሳት ይገልፃሉ። ለጥያቄው የአቶ መለስ መልስ ‹መሬቱን ለገበሬው በግል ሃብትነት ብንሰጥ ሊሸጠው ይችላል፣ መሸጥ በህግ ከተፈቀደ ደግሞ አማሮች ገዝተው እንደበፊቱ ገበሬውን ወደ ጭሰኝነት ይቀይሩታል ብለን ስለምናስብ ነው› ብለው እንደመለሱላቸው ይናገራሉ አሜሪካዊው ሄርማን ኮህን። መሬት መግዛት የሚችለው አማራ ብቻ ነው ወደማለት የሚቃጣው ይመስላል ይህኛው የአቶ መለስ ንግግር።

አቶ መለስ ጠንከር ብሎ የሚገዳደራቸውን ሃይል ህዝባዊ ድጋፍ የሚያሳጡበት የሚመስላቸው መንገድ ቡድኑን ‹የነፍጠኛውን ስርአት ለማምጣት የሚጥሩ የአማሮች ስብስብ› ማለትን ነበር። ቀደም ሲል በቅንጁት እና አሁን ደግሞ



በአንድነት ላይ ኢህአዴግ የሚሰነዝረው ድርጅቶቹን በአማራ ፓርቲነት የመፈረጅ ተደጋጋሚ ንግግር ለዚህ አስረጂ ነው።

## 3.8 የፈተና ቀናት

በሽግግሩ ዘመን የተጀመረው የኢህአዴግን ስልጣን የማጠባበቁን ስራ በ1995 ህገ-መንግስት ህጋዊ መሰረትካገኘ በኋላ ነበር ባልታሰበ ሁኔታ ህወሃት ከውስጥ የመሰንጠቁ ነገር የተሰማው። በወቅቱ ውስጣዊ ሽኩቻው በዋናነት ሚደረገው በመለስ እና በተወልደ ጀርባ በመሰለፍ ሚናቸውን በለዩ የህወሃት ታጋዮች ነበር። ከጫካ ጀምሮ አብሯቸው ለመጣው ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነትም ሆነ መቸሊ ላይ ለተደረገው ልመና እና ውግዘት አልበገር ያሉት የስዬ እና የአቶ ተወልደ ቡድኖች የህወሃትን ህልውና አደጋላይ የጣሉት መሰለ። ይህ አቶ መለስን ሰላም ሲነሳ አቶ ስብሃት ነጋን የሚያክሉ አዛውንትን በእንባ አራጨ (የመቀሌውን ስብሰባ በሚያሳየው ፊልም አቶ ስብሃት ነጋ ሲለቅሱ ይታያሉ)። ይህ ሁሉ የክስተቱን አደገኝነት እና በአመራሮች ዘንድ የፈጠረውን ድንጋጤ ብርታት ያሳያል።

በዚህ ወቅት አቶ መለስ ጎልያድን በመዘረር የእስራኤልን ህዝብ ልብ ከመውደቅ ያዳነውን ዳዊትን ተመስለው ብቅ አሉ። መትተው የሚጥሉበትን ቦታ የሚያውቁት አቶ መለስ ለተገዳዳሪወቻቸውም የፉከራቸውን ያህል፣ ለደጋፊወቻቸውም የስጋታቸውን ያህል ባልሆነ ሁኔታ ህወሃት እንዲያንሰራራ አደረጉ። አቶ መለስ ፈተናውን በአሸናፊነት ቢያጠናቅቁም በወቅቱ የገጠማቸውን ተግዳሮት ክብደት ግን በህይወታቸው ከገጠሟቸው ሶስት ከባድ ፈተናዎች አንዱ አድርገው ያወሷቸው ነበር።

ህወሃትን ከመፈረካከስ አደጋ የማዳኑ ስራ ለአቶ መለስ ከባድ ፈተና ቢሆንም ችግሩን በአሸናፊነት ማለፋቸው የተከታዮቻቸውን እምነት እንዲያገኙ አብዝቶ ረድቷቸዋል። ነባር የህወሃት ታጋዮች በአንጃነት ተፈርጀው ከህወሃት መሰናበታቸው የአቶ መለስ ፖለቲካዊ ተክለስብእና ግዝፈት (political personality cult) እየጨመረ እንዲመጣ አድርጎ በስተመጨረሻውም ከሞቱ በኋላ እንኳን ስማቸው በህይወት ካሉበት ጊዜ በላይ እንዲጠራ፣ ቃላቸው እንደፈጣሪ ቃል ስህተት የሌለው ተደርጎ እንዲታሰብ አድርጓል።

አስፈንክት ከሚለው የህግ የበላይነት መርህ ጋር ይጋጫል። ተቃዋሚዎቹ በመረጃ የተደገፈ የሚያስከስስ ጥፋት ከሰሩ መክሰስ ነበረባቸው እንጂ ምርጫው በኢህአዴግ ድል ሲጠናቀቅ በሰዶ ማሳደድ ስም የሚተው ለክስ የተዘጋጀ ማስረጃ በፊትም መኖሩ ያጠራጥራል። በጥቅሉ ከላይ የተገለፀው የአቶ መለስ ከምርጫ በፊት እና በኋላ ንግግር ኢህአዴግ ለምርጫ ያለውን አረዳድ እና ለጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲ ያለውን በጎ ያልሆነ እይታ ያሳያል። ይህ ደግሞ በሃገራችን የዲሞክራሲ ጅንበር የምትወጣበትን ቀን ያረዝመዋል።

## 3.13 የእረፍት ናፍቆት

አቶ መለስ የገደላቸው በሽታ እንዳለባቸው ያወቁት በ1998 እንደሆነ በሞቱ ሰሞን ከታላላቅ ባለስጣኖቻቸው በኢቲቪ በኩል ይነገር ነበር። በ2002 ከኢትዮጵያ ፈርስት የመጣው ዲያስፖራ ጋዜጠኛ በኢቲቪ ቃለምልልስ ሲያደርግላቸው ከዚህ በኋላ እረፍት እንደሚፈልጉ፣ እረፍት እንደናፈቃቸው አጫውተውት ነበር። አያይዘውም በእረፍት ጊዜያቸው መፃፍ እንደሚፈልጉ ሲገልፁ «ማለፍም ስለሚኖር ከስር ከስር መፃፈ እንዳለብኝ አስባለሁ» ብለው ነበር። አባባሉ የተቆራኛቸው ህመም ከባድ በመሆኑ ረዥም እድሜ እንደማያኖራቸው ቀድመው የገመቱ መሆኑን ያሳያል።

እረፍት ያስፈልገኛል ያሉት አቶ መለስ ከስልጣን ገለል የማለት እቅድ እንዳላቸው ቢገልሁም ሃገራቸው ውስጥ ሆነው የፓርቲያቸውን ስራ መስራቱን ግን እንደሚቀጥሉ ገልፀው ነበር። እሳቸው እንደግለሰብ ከስልጣ መንበሩ ቢለቁም ፓርቲያቸቸው ኢህአዴግ ግን ከሃገሪቱ የመንግስትነት መንበር እንዲጠፋ የሚፈልጉ አይመስልም ነበር። ለዚህ ተግባራዊነት አቶ መለስ ወሳኝ እርምጃዎችን አከናውነዋል፤በ ጃጋን አርባ አመት በስልጣን ላይ ስለቆየው እና አሁንም በስልጣን ላይ ስላለው ፓርቲ እያነሳሱ አንድ ፓርቲ ስልጣን ላይ መቆየቱ በራሱ ችግር አይደለም ሲሉም ያስረዱ ነበር - ሟቹ መለስ።

በ1997 በተደረገው ሃገራዊ ምርጫ ማግስት በማንኛውንም ክፍያ ስልጣንን የማዳን ውክቢያ፣ እሱን ተከትሎ ኢህአዴግን አውራ ፓርቲ ለማድረግ የተደረገው ትንሽ ትልቁን በአባልነት የመሰብሰብ ስራ እና በተቃራኒው ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የማኮሰሱ የአቶ መለስ መንግስት እርምጃ ለሃገሬው



ህዝብም ሆነ ለውጭ መንግስታት ከኢህአዴግ በቀር ኢትዮጵያን ለመምራት የተዘጋጀ አካል እንደሌለ እንዲያምን አድርጓል። ይህንን አመለካከት በጥሩ ሁኔታ እንደገነባ ያወቀው ኢህአዴግም ስላመጣው ልማት እና ወደፊት ሊያመጣ ስላሰበው ልማት ሲባል ከዚህ በኋላ ለሚቀጠሩ ሃምሳ አመታት በስልጣን ላይ መቆየት እንዳለበት እያወሳ ነው። ፓርቲያቸው በስልጣን ላይ ሲሰነብት አቶ መለስ በህይወት ቢኖሩ ኖሮ ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው የሃገሪቱን ፖለቲካ የመዘወሩን ስራ መቀጠላቸው እንደማይቀር መጠርጠሩም እውን የማይሆን ግምት አይደለም። ከዚህ በተለየ እይታ አቶ መለስ እረፍት እፈልጋለሁ፣ ስልጣን እለቃለሁ ይበሉ እንጂ ሞት ባይቀድማቸው አሁንም ፓርቲየ ይፈልገኛል ብለው በስልጣን መንበሩላይ ስላለመቆየታቸው እርግጠኛ መሆንም አይቻልም ነበር።

## 3.14 ከመስጊድ ገዳም የዘለቀ ውጥረት

የአወሊያ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመምህራኖቻቸውን መባረር እና በኋላም የትምህርትቤታቸውን መዘጋት በመቃወም የተጀመረው የተቃውሞ እንቅስቃሴ እያደር እያደገ መጥቶ አንድ አመትን አስቆጠረ። የተቃውሞ ድምፅ እያሰማ ያለው ህዝበ-ሙስሊም ጥያቄያችን የሃይማኖት መሪዎቻችንን የመምረጥ መብታችን ይከበር፣ መንግስት የአህባሽ ሃይማኖትን በግድ ለማስፋፋት ከሚያደርገው ጣልቃገብነት ይቆጠብ የሚል ነው ቢልም መንግስት ደግሞ እንቅስቃሴውን እስላማዊ አክራሪነትን በሃገሪቱ ለማስፋፋት ብሎም እስላማዊ መንግስትን ለመመስረት የሚደረግ የሰላፊስቶች እንቅስቃሴ ነው ሲል ተርጉሞታል። ይህን አስመልክቶ ለአቶ መለስ በህይወታቸው የመጨረሻ በሆነው የፓርላማ ውሎዋቸው ሰፋ ያለማብራሪያ ሰጥተው ነበር። ከአቶ መለስ ሰፊ ማብራሪያ በተጨማሪ በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስተር ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም የተደረገው እስከ ሃረር የተጓዘ ከእስልምና ሃይማኖት መሪዎች ጋር የተደረገ ውይይት የሙስሊሙ ማህበረሰብ ጠንክር ያለ ተቃውሞ ምን ያህል የአቶ መለስን መንግስት እንዳሳሰበ እና ትኩረቱን እንደሳበ ያሳያል።

የአቶ መለስ መንግስት በየቀኑ እየበረታ ለሚሄደው የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተቃውሞ እልባት ሳይሰጥ ነበር ከወደ ዋልድባ ገዳም ሌላ ተቃውሞ የገጠመው። መንግስት የዋልድባ ገዳም ይዞታ ነው የተባለውን መሬት

ላይ የነበራቸው ሚና የሚናቅ ባይሆንም ካድሬዎቻቸው እንደሚያጋንኑት አለመሆኑን ነው።

## 3.16 «ወፈ-ክፋው» የካምፕዴቪድ ጉዞ

መንግስታቸው አመጣው በተባለው የልማት እምርታ በፕሬዚዳንት ኦባማ ጠሪነት አቶ መለስ በካምፕዴቪዱ ስብሰባ እንዲካፈሉ መጋበዛቸው ታይቶ የማይታወቅ ልማት አመጣሁ ለሚለው መንግስታቸው መልካም የፕሮፖጋንዳ ግብአት ነበር። በአንፃሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ከሆነው ጋዜጠኛ አበበ ገላው ከልማታዊነታቸው አምባገነንነታቸው ይብሳል የሚል አንድምታ ያለው በጩኸት የታጀበ ተቃውሞን ያስተናገዱበትም ነው - የካምፕዴቪዱ ስብሰባ። የጋዜጠኛው በጩኸት የታጀበ ተቃውሞ የአቶ መለስን መንግስት አምርሮ ለሚተቸው ዲያስፖራ እንደትልቅ ጀብዱ ተቆጥሮ ጋዜጠኛውን እንደ የጀግና መጨረሻ አስቆጥሮት ነበር። በአቶ መለስ ደጋፊዎች ዘንድ ደግሞ አበበ ገላውን ሃገሩን በባዕዳን ፊት ያዋረደ፣ መልካም ገፅታዋን ያጠለሸ ተደርጎ ሲብጠለጠል ከርሟል። እንደ ኢህአዴግ ደጋፊዎች የአበበገላው በሃይለኛ ጩኸት የታጀበ ተቃውሞ አፄ ሃይለስላሴ በ»ሊግ ኦፍ ኔሽን» ንግግር ባደረጉ ወቅት ከኢትዮጵያ ጠላቶች ከገጠማቸው ንግግራቸውን የማደናቀፍ ጩኸት ጋር መሳ አድርገውታል።

አጋጣሚው የአቶ መለስ ደጋፊዎችም ሆኑ ተቃዋሚዎች እንዳጋነኑት ሳይሆን ረጋ ባለመንፈስ ቢጤን ያን ያህል መጋነን ያለበት ጉዳይ አይደለም። የልዕለ ሃያሏ ሃገር የአሜሪካ ፕሬዚዳት ጆርጅ ቡሽም በአንድ ወቅት ከጋዜጠኛ በተወረወረ ጫማ ለትቂት ተስተው ነበር። ጆርጅ ቡሽ ይህ የአሜሪካ ዲሞክራሲ በኢራቅ ላይ ያመጣው በጎ ተፅዕኖ መገለጫ ነው በማለት ነበር ቀለል አድርገው የተረጎሙት። ወደ አቶ መለስ ጉዳይ ስንመለስ የአበበን ጩኸት አዘል ተቃውሞ ያመጣው በሃገር ውስጥ የህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት መታፈን ነው። በሃገር ውስጥ አቶ መለስን ስለመንግስታቸው እንከን በግልፅ መጠየቅ ቢቻል ኖሮ በሰው ሃገር መድረክ መጯጯህ ባልመጣ ነበር። እውነታው በተቃራኒው በመሆኑ ጋዜጠኛውም አጋጣሚውን አቶ መለስን ያለአእላፍ ወታደሮቻቸው በግላጭ ያገኘበት ቅፅበት አድርጎ በመውሰዱ ተገቢ የመሰለውን አድርጓል።



ከካምፕዴቪዱ ስብሰባ በኂላ የታዩት አቶ መለስ የድሮው አልነበሩም። ሰውነታቸው በጣም ከመቀኒሱ በላይ የመታከት አይነት ገፅታ ፊታቸው ላይ ይታይ ነበር። ቀጣይ ስብሰባ በሜክሲኮ ሉስካቦስ ያደረጉት መለስ በትቂት ቀናት ውስጥ ደብዛቸው ጠፋ። በጠና መታመማቸው ከሃገር ውጭ በከተሙ የመገናኛ ብዙሃን መናፈስ ከጀመረ ቢቆይም ድብቁ ኢህአዴግ የሚዘውራቸው የሃገራችን መገናኛብዙሃን ግን እንደተለመደው የልማቱን መሟሟፍ ብቻ ነበር አበክረው የሚያወሩት።

ስለአቶ መለስ የጤና ሁኔታ ከሃገር ውስጥ በግልፅ የተነገረ ነገር ባይኖርም ከህወሃት ሰዎች ውስጥ የተሻለ ለመገናኛብዙሃን መረጃ የመስጠት ልምድ ያላቸው አቶ ስብሃት ነጋ ለቪኦኤ የሰጡትን ቃለ-ምልልስ ልብ ብሎ ላደመጠ «....አሁን የስልጣን ሽግግር ላይ ነን» ያሏት ቃል የአቶ መለስን ማረፍ የምትጠቁም ነች። በተጨማሪ አቶ ስብሃት በዛው በቪኦኤ «ፋጢማ መጣች በቀለ ሄደ ኢህአዴግ ማስተዳደሩን ይቀጥላል» ሲሉ የአቶ መለስን ዳግም መታየት አለመቻል የሚያረጋግጥ ድምፀት ያለው ንግግር ተናገሩ። አቶ መለስ ወደ ስልጣን የመመለስ እድል ቢኖራቸው ኖሮ አቶ ስብሃት እንደዚህ እንደማይናገሩ እሙን ነው። በአንፃሩ የአቶ በረከት ስለአቶ መለስ በመስከረም ወደ ስራ መመለስ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ደግሞ ሌላው አደናጋሪ ነገር ነበር።

ምንም ተባለ ምን የሞቱን ዜና ማዘግየት አንጂ ደብቆ መቅረት አልተቻለም እና ኢቲቪም የግዱን ሞታቸውን አወራ፣ የአስከሬን አቀባበሉን ስነስርዓትም በቀጥታስርጭት አስተላለፈ። አቶ በረከትም ስለጓደኛቸው ሲያነቡ ታዩ። አቶ መለስ በቀይምንጣፍ፣ በብዙ አጀብ ሲመላለሱበት በነበረው አውሮፕላን ማረፊያ እስትንፋስ አልባ በድናቸው በአራት ማእዘን ሳጥን ታሽጎ በሰው ሸክም ሲወርድ ሲታይ የሚፈጥረው ስሜት ይረብሽነበር።

የአቶ መለስ ሞት ለኢህአዴግ ባለስልጣናት ድርብ ሃዘን ነበር። መንግስታዊ የስልጣን ደረጃቸውን በማይመጥን ሁኔታ ሃዘናቸውን እየየ በበዛበት ሁኔታ መግለፃቸውም የሃዘናቸውን ብርታት ያሳያል። ባለስልጣናቱ በባልደረባቸው በመካከለኛ እድሜ ላይ መሞት ከሚሰማቸው ሃዘን ባልተናነሰ የኢህአዴግን ስልጣን ከማስቀጠሉ ፈታኝ ስራ ጋር በድንገት መጋፈጡም አስደንጋጭነቱ ቀላል አይደለም። የባለቤታቸው የወ/ሮ አዜብ መረር ሃዘን እና ዋይታም አቶ መለስ ለሚስታቸው የነበራቸውን መልካምነት ያሳያል።

# ስለ ስልጣን

የሰው ልጅ ፖለቲካዊ እንስሳ እንደመሆኑ በአለቃ ምንዝር መከፈሉ የሚጠበቅ ነው። ዋናው ነገር አለቃ የተባለው አካል ስልጣኑን ከመጀመሪያው ለምን ፈለገው? እንዴትስ እየተጠቀመበት ነው? የሚለው ጉዳይ ነው። የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ የሁለተኛውን ጥያቄ መልስ መነሬስ ያመላክታል። የሰዎች ወደ ስልጣን ማቃተት የተለያዩ ግልፅ እና ስውር ምክንያቶች ይኖሩታል። ግልፁ ምክንያት ስልጣን ፈላጊዎቹ በአንደበታቸው የሚናገሩት፣ በፕሮግራም ማኒፌስቶአቸው የሚጽፉት ላይኛ ምክንያት እና አላማ ነው። ይህም በብዛት የሚገለፀው ለህዝብ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ደረጃና ፖለቲካዊ ነጻነት ለማምጣት ነው በማለት ሲሆን የውስጥ ስውሩ ግን አይነገርም። ይልቅስ ከስልጣን በኋላ ከሚሰራው ስራ በተግባር የሚታይ ነው።

ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚያስብ አካል ስልጣን ሲጨብጥ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራባቸውን ጉዳዮች በፕሮግራም፣ ማኒፌስቶው አስቀምጦ ቶሎ ያደርሰኛል ብሎ ባመነበት መንገድ ወደ ስልጣን ጉዞውን ይጀምራል። ጉዞው ዝናር እና መውዜር አንስቶ ዱር ቤቴ በማለት፣ የባለጋራው አቀማመጥ እንደ መሶብ ክዳን ከሆነደግሞ በመፈንቅለመንግስት በማሽቀንጠር አለያም በሰለጠነ መንገድ በተሻለ የሃሳብ ልቅና በሰላማዊ መንገድ በተገዳዳሪ እግር በመተካት ሊሆን ይችላል። የኋለኛው ፈርጅ ብዙ ጥቅም አለው። አንደኛ ወደ ስልጣን የሚመጣበት መንገድ የህይወት መስዋትነትን አይጠይቅምና መተላለቅ የሌለበት ሰላማዊ ትግል ነው። በዚህ መንገድ ወደ ስልጣን የመጣ አካል ስልጣኑን ለመልቀልቀቅም የሚያወራርደው የሙት ቁስለኛ መጠን የለውምና የተሻለ ሲመጣ ስልጣን ለማስረከብ አያቅማማም። በሃሳብ ልዕልና በልጦ ወደ ስልጣን ስለመጣ መበለጥ ሊኖር እንደሚችል እያሰበ ይቆያል እንጂ ስልጣን ለዘላለም የሚጣዱበት ነው ብሎ አያስብም።

ወደ ስልጣን መምጫው መንገድ የትኛውም ቢሆን ስልጣኑ በእጅ ከተደረገ በኋላ የሚሰራው ስራ ከመጀመሪያው ስልጣኑ ለምን እንደተፈለገ የማሳየት አቅም አለው። በተጨማሪም ቡድኖቹ ስልጣን ላይ ከመፈናጠጣቸው በፊትም የትግል ፕሮግራም እና ማኒፌስቶአቸውን በማየት አዝማሚያቸውን





መገመት ይቻላል። በርግጥ ሁሉም ወደ ስልጣን የሚገሰግስ አካል ‹የምታገለው ለህዝብ አንዲ እና እንዲያ ያለ የተሻለነገር ላመጣ ነው› ይላል እንጂ ለራሴ ሚሊየነር ልሆን፣ ከስልጣን ጋር ቅበሩኝ ልል ነው ሲል የተሰማ የለም። በቃሉ የሚገኘው፣ ያወራውን የሚፈጽመው ግን ትቂቱ ነው። ከዚህ አንፃር በሃገራችን ከዘውዳዊ ስርአቱ ማክተም በኋላ የመጣውን ወደ ስልጣን ገስጋሽ ቡድን ከስልጣን በፊት ቃልና ከስልጣን በኋላ ተግባር ብንፈትሽ ከደርግ መጀመር ሊኖርብን ነው።

ጥያቄው ሌላ የነበረው ደርግ ወደ ሃገራዊ ስልጣን እመጣለሁ የሚለው ግምት ስላልነበረው ስልጣን ከያዘ በኋላ ስለሚሰራው ነገር አውርዶ አውጥቶ ያዘጋጀው የትኩረት አቅጣጫ አልነበረውም። ልቅስ ይህ ቡድን ሳያውቀው ዙፋን ላይ ያደረሰውን ህዝባዊ ማእበል ተጠቅሞ፣ የለውጡን ሂደት ያበሰሉ ምሁራንን ሃሳብ ነጥቆ ባለቤት መሰለባቸው እንጂ። ደርግ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ያደረጋቸው መሬት ላራሹን ጨምሮ የፊውዳል ስርአቱ ያረፈባቸውን መሰረቶች የሚፈራረስ ስራ ከስልጣን በፊት በንድፈሃሳብ የተለማቸው ሳይሆኑ ከኢህአፓ እና ከመኢሶን ፕሮግራሞች የቀዳቸው ነበሩ።

ይሄ ሳያስብ ወደስልጣን የተሳፈረበት ሁኔታ ነበር ከስልጣን በኋላ ያለውን ደርግ እንደ ደነበረ አውሬ ያገኘውን የሚናከስ፣ የሚሰራውን የማያውቅ፣ ከሁሉ ጋር የሚላተም ደረገው። ወታደራዊ ቡድኑ ወደ ስልጣን በጣም በቀረበባቸው ቀናት ሲያውጅ ሲሰራ የነበረው ነገር እግራሞትን የሚፈጥር ነበር። ንጉሱን በቁጥጥሩ ስር ካደረገ በኋላ እንኳን በድፍረት በእግራቸው ለመተካት ሲሽከረመም ብዙ ጊዜ አሳልፏል። ይህ ደግሞ ወደ ስልጣን ሲወጣ እየተሞሸረ ያለው የወታደር ቡድን ስዩመ-እግዚአብሄር እያለ ከሚሰግደው፣ የንጉስ ስልጣን የማይደፈር የማይገሰስ ነው ብሎ ከሚያምነው አብዛኛ ህዝብ የተሻለ የፖለቲካ ንቃት እንዳልነበረውም ማስረጃ ነው።

የንጉሱን በሌላ መተካት ለማወጅ ትቂት ቀናት እስኪቀሩት ድረስም ለሃገሪቱ የሚበጀው ምን አይነት ስርአት ነው ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ መልስ አልነበረውም። ዘውዳዊ ስርአቱን ለማስቀጠል በልጅ ሚካኤል እምሩ በኩል ለመምጣት ሲወዛገብ እንደነበርም የአንዳርጋቸው አሰግድ «በአጭር የተቀጨረኸርም ጉዞ» የተባለ መፅሃፍ ያስነብባል። እንደምንም ብሎ ድፍረቱን አሰባስቦ ስልጣን ላይ መውጣቱን ሲያውጅ ደግሞ በአንደ የንጉሱ ዙፋን

ሆና አታውቅም። ይህ የሆነው ግን ዜጎቿ ዲሞክራሲን ስለማይሹ፣ ለተግባራዊነቱም ስላልታገሉ አይደለም፤ የተከፈለውን መስዕዋትነት የሚመጥን ውጤት አልመጣም እንጂ ስለህዝባዊ መንግስት ምስረታ ብዙዎቹ ውድ ህይወታቸውን ሰውተዋል።

## ትግል Vs አብዮት

አብዮት ለትርጉም አስቸጋሪ ከሆኑት ትቂት ዕንሰ ሃሳቦች ወገን እንደሆነ ካርል ካቱስኪ የተባሉ ፀሃፊ «what is Revolution?» በሚለው ፅሁፋቸው ይገልፃሉ። እንደ ፀሃፊው አብዮት በግርድፍ ትርጉሙ አዝጋሚ ባልሆነ ሁኔታ ለውጥ የሚመጣበት ሂደት ነው። ለአብዮት ገቢራዊነት ትግል አስፈላጊ ቢሆንም ትግል ሁሉ አብዮት እንደማያመጣ ሃገራችን ምስክር ናት። በሃገራችን ሰማይ ስር መንግስታዊ ለውጥ በምድራዊ ሃይል ማምጣት እንደሚቻል ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው ከ1953ቱ ያልተሳካ የመፈንቅለ-መንግስት ሙከራ ነው። የመፈንቅለ-መንግስት ሙከራው አልሞት የተነሳውን ስልጣኑ በህገ-መንግስት የተገደበ ዘውዳዊ ስርአት የመመስረቱ ነገር ባይሳካም ‹መንግስት መለኮታዊ በመሆኑ በምድራዊ ሃይል አይቀየርም› የሚለውን የቆየ ፖለቲካዊ አይነ-ጥላ የገፈፈ እንቅስቃሴ ነበር። በመሆኑም ከ1953 በኋላ በሃራችን ብዙ ትግሎች ተካሂደዋል። የገበሬዎች፣ የተማሪዎች፣ የሰራተኞች (ከተማ ነዑስ ከበርቴው)፣ በፓርቲ ጥላ ስር የተሰባሰቡ ፖለቲከኞች፣ መውዜር ታጣቂ ዱርቤቴ ባዮች የልባቸውን ያላደረሰውን የመንግስት አስተዳደር ለመቀየር ውጤት ላይ ያደርሰናል ባሉት መንገድ ታግለዋል/እየታገሉም ነው።

ነገር ግን ረዥምም ጊዜ የወሰደው ትግል የፈሰሰበትን ደም እና ላብ የሚመጥን ውጤት አላመጣም። ከላይ የተጠቀሱት እና ሌሎችም በሃገሪቱ የተደረጉ ከትጥቅ ትግል እስከ በዋና ከተማ ላይ በሽጉጥ መተላለቅ፤ የፖለቲካ ፓርቲ መስርቶ ከመታገል እስከ የምርጫ ውጤት ተጭበርብሯል በሚል ውዝግብ መጋደል መታሰር ድረስ የደረሱ ትግሎች ሃገሪቱን ያልተሳኩ ትግሎች ሙዚየም አደረጋት እንጂ ለተግባራዊ ለውጥ አልሆኗትም። ከዚህ የተነሳ በግሌ እስከዛሬ በሃገራችን ትግል እንጂ አብዮት አልተደረገም ብዩ አምናለሁ። ምክንያቱ ደግሞ ገና ከጠዋቱ ለ1950ዎቹ እና1960ዎቹ ትግሎች ዋነኛ ምክንያት የነበሩ ማህበረ-ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች በተገቢው ሁኔታ አልተመለሱም ብዩ ስለማምን ነው። ትቂት ለመጥቀስ ያህል ኢህአፓ



ሲታገልለት የነበረው ህዝባዊ መንግስት የመመስረት ጥያቄ አሁንም አልተመለሰም። ህዝባዊ መንግስት ማለት ሌላው ቢቀር የህዝብን ጥያቄ በተገቢ ሁኔታ ማድመጥ የሚችል እንጂ ብቻውን የሚያወራ፣ ህዝብ ችግሬ ይህ ነው ሲል የለም ችግርህን የማውቀው እኔ ነኝ የሚል አይነት መንግስት አይደለም። በሃገራችን እስካሁን ብቅ ያሉ መንግስታት ደግሞ ህዝብን ሲያደምጡም ሆነ በችግሩ ላይ የተመሰረተ መፍትሄ ለማፈላለግ ሲጥሩ አላየንም። በምትኩ ከባህር ማዶ የቃረሙትን ፖሊሲ አምጥተው ሲጭኑ እና ለስልጣናቸው ማራዘሚያ ይሆናል ያሉትን ማድረግ የሚቀናቸው ናቸው።

መኢሶን ሲታገልለት የነበረው ፖለቲካዊ ንቃትን በህዝብ ዘንድ የማስረፅ ነገርም ገና ውሃው ያልሞቀ ጉዳይ በመሆኑ አሁንም ህዝባችን ፖለቲካን የነብር ጭራን እንደ መያዝ ይቆጥረዋል። መንግስት አድራጊ ፈጣሪ ህዝብ ደግሞ እሽባይ ተገዥ ብቻ ሚመስለው ዜጋ የትለለ ነው። እነ ዋለልኝ መኮንን፣ ጥላሁን ግዛው እና ሌሎች ዘመናቸው ህይወታቸውን ያጡለት የመሬት ባለቤትት ጉዳይ፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት፣ የመደራጀት ነገር፣ የዜጎች እኩልነት፣ የግብር ጉዳይ፣ መንግስታዊ ሙስና ወዘተ አሁንም ጥያቄ እንደሆነ ቀጥሏል። በኢኮኖሚው መስክም ቢሆን ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ የሃገራችን ገበሬ በነአፄ ድልናአድ ዘመን ይደረግ እንደ ነበረው በሁለት በሬ እና በባለ አንድ ጥርስ ማረሻ እፍኝ ሙሉ ምርት ለማምረት ወደ ሰማይ አንጋጦ ዝናብ ከመጠበቅ ፈቅ ነቅነቅ ሳይል ባለበት አለ። ባስ ሲልም በጦር ወይም በዶማ መቆፈር ይመጣል። መሬት ላራሹ ተብሎ ብዙ የተሆነለት ትግልም መሬትን ለመንግስት አድርጎ ተጠናቋልና የገበሬው ሁለንተናዊ እጣፋንታ በመንግስት መዳፍ ስር እንደሆነ ቀጥሏል።

በአንድ ሃገር አብዮት ተካሂዷል ለማለት ብዙ መስፈርቶች ቢኖሩትም ቢያንስ የማህበራዊ ግንኙነቱ እና የስልተ-ምርት ባለቤትነት (በማምረቻ መሳሪያባለቤትነት) ላይ ለውጥ መታየት አለበት ይላሉ ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ በቅርቡ ከኢሳት ቴሌቭዥን ጋር ባደረጉት ውይይት። በዚህ እሳቤ ሲታይ ዘውዳዊ ስርዓቱን የገረሰሰው የሃገራችን ትግል የፊውዳሉ ስርዓት የቆመበትን የመሬት ከበርቴ-ጭሰኛውን ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ስላጠፋው በተወሰነ መልኩ ለውጥ አምጥቷል ብሎ ማሰብ ይቻላል። ነገር ግን አሁንም መሬት የአራሹ ገበሬ የግል ሃብት እስካልሆነ ድረስ ለዚሁ የተደረገው እንቅስቃሴ ግቡን መቷል ለማለት አያስደፍርም።

## የተሳካ አብዮት ዋነኛ መገለጫዎች

የአብዮት ትርጓሜ አስቸጋሪነቱ ለምሁራን ብቻ እንዳልሆነ የሚገልጹት ካርል ኩቱስኪ አብዮተኞች በተለይ መሪዎች ራሳቸው የትግላቸውን አላማ ለማስቀመጥ ብዙ ጊዜ እና ሃይል ይጨርሳሉ ይላሉ:: አክለውም የአብዮቶች አካሄድ እና ውጤት መልከ-ብዙነት ትርጓሜውን አስቸጋሪ እንዳረገት ያስረዳሉ:: አብዮቶች ያልተጠበቀ ውጤት ከማምጣት እስከ መክሸፍ የሚደርስ ፍፃሜ ሲኖራቸው የታለመላቸውን ግብ ለመምታት የታደሉ አብዮዮችም በአለማችን ታይተዋል:: በቅርቡ «የአረብ ፀደይ አብዮት» በመባል የሚታወቁትን ብንወስድ እንኳን የቱኒሲያው እና የሊቢያው የተሳኩ ቢሆኑም የግብፁ እና የሶሪያው ያልታሰበ ውጤት ያመጡ፣ መዘዛቸው ገና ተመዞ ያላለቀ ይመስላል:: የሶርያው በተለይ ህገ-መንግስት እንዲሻሻል በመጠየቅ ተጀምሮ ከአርባ አንድ አመት በላይ የቆየውን የአሳድ ቤተሰብ ስርወ-መንግስት በዲሞክራሲዊ መንግስት የመተካት ጥያቄ ላይ ደርሷል:: በዚህ መሃል በአማካይ በቀን የአንድ መቶ ሰዎች ህይወትን የሚያስገብር ሶስት አመት ያስቆጠረ ፍጅት በሃገሪቱ የነገሰ ቢሆንም የትግሉን የመጀመሪያም ሆነ የመጨረሻ ጥያቄ የመለሰ ለውጥ በሃገሪቱ እየታየ አይደለም::

አብዮት የተጠበቀውን ውጤት ሳያመጣ ሲቀር፣ በከፊል ግቡን ሲመታ ወይም ሲከሽፍ ስኬታማ አልሆነም ሊባል ይችላል:: አብዮትን የሚያቀጣጥሉ ለውጥ ፈላጊዎች ትግል የሚያደርጉት ያሰቡትን ለውጥ ለማምጣት ነውና ለውጥ የሚያመጣ አብዮት ምን አይነት ገፅታዎች ይኖሩታል ወደ ሚለው ሃሳብ ልለፍ:: በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ፕሮፌሰር የሆኑት ስሞን ስቻማ "Elements of successful Revolution" ሚለው ፅሁፋቸው ሁሉን የሚመዘግበው ታሪክ አብዮትን ስኬታማ የማድረጊያ መንገዶችን ከተሞክሮ እንድንረዳ ያደርገናል ይላሉ:: እንደ ፀሃፊው አብዮት ከሁሉ በፊት ሁሉም ለውጥ ፈላጊዎች ሊደራደሩበት የማይችሉት የተወሰነ የለውጥ ግብ ያስፈልጋቸዋል:: በዚህ ረገድ የግብፅን እና የሊቢያን አብዮት ብንወስድ እንቅስቃሰው ሲጀመር ለውጥ ፈላጊዎቹ የሙባረክ እና የጋዳፊን ከስልጣን መውረድ በምንም ሁኔታ የማይደራደሩበት ግብ አድርገው ነበር የተነሱት:: ግብጾች ይህ አውን ካልሆነ ቤታቸው እንደማይገቡ ተናግረው ታህሪር አደባባይ ከትመው እንደነበር ይታወሳል:: በሊቢያ ሁኔታም ጋዳፊን ከጉድጓድ ጎትተው እስኪያወጡ ድረስ እረፍት አልነበረም:: ይህ የሁለቱ ሃገሮች ሁኔታ



ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ ግን አብዮተኞች የሚፈልጉት ለውጥ መልከ-ብዙ ነው:: ምሳሌ የመንግስት ለውጥ፣ የህገ-መንግስት መሻሻል፣ የዲሞክራሲ ተቋማት ገለልተኛነት፣ አወቃቀር፣ አሰራር፣ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም፣ የግብር አከፋፈል ሁኔታ፣ መንግስት የሃገርን ሃብት የሚጠቀምበት መንገድ፣ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ሁኔታ ወዘተ ሊሆን ይችላል:: ግብ ከማስቀመጡ እኩል አብዮተኞቹ ከግላዊ ጉዳዮች ይልቅ ለተቀመጠው ትልቅ ግብ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት ልዕልና ላይ መድረስ አለባቸው:: ይህ መሆኑ የስልጣን ሽኩቻ፣ የግል ቂም በቀል፣ ሙስና እና ሌሎች ችግሮች በታጋዮቹ መሃል እንዳይከሰቱ እና ትግሉን እንዳያዳክሙት ይረዳል::

ሌላው ለስኬታማ አብዮት አስፈላጊው ነገር የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የጋራ ገዥ አስተሳሰብ (Ideology) መኖር ነው:: ገዥ አስተሳሰቡ ለውጥ ፈላጊዎቹ ሁሉ ትግላቸው የቆመለትን አላማ ጠንቅቀው እንዲውያቁ የሚደረግበት ነው:: በተመሳሳይ ለአብዮት ስኬታማነት እስከመጨረሻው የሚፀና፣ በተሻለ ሁኔታ የትግሉን አይድዮሎጅ ማስረፅ የሚችል ጠንካራ አመራር አስፈላጊ ነው:: አመራሩ አብዮተኞቹ የሚቃወሙትን እና እንዲለወጥ የሚፈልጉትን መንግስት ፖለቲካዊ ህፀፆች ንቅሶ በማውጣት በእውቀት የሚከተሉ ታጋዮችን የማብዛት ስራ በመስራት ብቻ ሳሆን ከትግሉ በኋላ ሊመጣ ስለታሰበው መንግስት ተፈጥሮ ግንዛቤ በመፍጠር በኩል ትልቅ ድርሻ አለው:: በተጨማሪም ትግሉ ወደአልሆነ አቅጣጫ ሄዶ ያልተፈለገ ውጤት እንዳያመጣ ወይም እንዳይቀለበስ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የመምራቱን ትልቅ ሃላፊነት የሚሸከመው አመራሩ ነው:: በዚህ መልክ የተሳካለት አብዮት በመምራት ማህተማ ጋንዲ፣ ኔልሰን ማንዴላ፣ ፊደል ካስትሮ፣ ማኦዜዱንግ ጆሴፍ ስታሊን ተጠቃሾች ናቸው::

እንደ ካርል ኩቱስኪ አብዮት እንዲሳካ አምባገነን መንግስታትን አጣብቂኝ ውስጥ የማስገባት አቅም ሊኖረው ያስፈልጋል:: የአብዮታዊያኑ እንቅስቃሴ አይሎ ወይም አምባገነን መንግስታት በራሳቸው የውስጥ ችግር ተዳክመው መለሳለስ ሲጀምሩ ያ የአብዮት ስኬት ምልክት መሆኑን ያስረዳሉ ፀሃፊው:: በ13ኛው ክ/ዘ በእንግሊዝ ተነስቶ የነበረው አብዮት የዘመኑን ፈላጭ ቆራጭ ንጉስ ጆንን አጣቂኝ ውስጥ ከቶ በሃገሪቱ እስከ ዛሬ የሚሰራበትን ህገ-መንግስት መሰል ሰነድ (ማግናካርታ) እንዲፅፍ በማድረጉ በዚህ ረገድ እንደምሳሌ ልናነሳው እንችላለን:: በተጨማሪ የኢራን ጀመሪያው አብዮት

ቋንቋ ሊያናግሩት ዱር ቤቱ ብለዋል። ከኒህኞቹ ብዙ የማይርቁት ደግሞ ኢህአዴግን ከስልጣን እስካወረደልን ድረስ ማንኛውንም የትግል ስልት እንከተላለን ሲሉ የሁለገብ ትግል ስልትን እያካሄዱ እንደሆነ ይናገራሉ። አራተኞቹ ደግሞ የሰሜን አፍሪካውን የአረብ አብዮት አርአያ የሚያደርጉ እና የወቅቱ የሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ «በመሬት አንቀጥቅጥ» ህዝባዊ አመፅ የመንግስት ለውጥ ማምጣት የሚያስችል እንደሆነ የሚወተውቱ ናቸው። የሁለገብ ትግል አራማጅ ወገኖችን በተመለከተ ለትንታኔ የሚበቃ መረጃ ስለሌለኝ የተቀሩትን ሶስት የለውጥ መንገዶች እንዴትነት እና ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ተግዳሮቶች ከኢህአዴግ ፖለቲካዊ ማንነት እና ከሌሎች የሃገራችን ተጨባጭ ፖለቲካዊ እውነታዎች አንፃር ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

## እሳቤ አንድ፡ ለውጥ በምርጫ ካርድ

በምርጫ ውጤት ለውጥ ማምጣቱ ከሁሉም የለውጥ መንገዶች የተሻለ፣ የህይወትም ሆነ የንብረት ውድመትን ሳያስከትል ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ከመሆኑ በተጨማሪ ያለንበትን ዘመን የሚመጥን የእውቀት መንገድ በመሆኑ ተመራጭ የለውጥ መንገድ ነው። ሆኖም ግን ይህ መንገድ የተመራጭነቱን ያህል በተለይ በአፍሪካ ተግባራዊ እየተደረገ አይደለም። ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱ አፍሪካን ከቅኝግዛት ለማላቀቅ ሲታገሉ የነበሩት እና በኋላም የየሃገራቸውን መንበረ-ስልጣን የጨበጡ መሪዎች ለአፍሪካ የሚያስፈልጋት የአንድ ጠንካራ ፓርቲ አመራር እንጂ መድበለ-ፓርቲ ስርአት አይደለም ብለው ያምኑ ስለነበር ነው። ይህ ጠንካራ ፓርቲ የሚባለው ደግሞ በአብዛኛው ከቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ይደረግ የነበረውን ትግል የሚመራው ፓርቲ ነው። በነፃ አውጭ ፓርቲዎቹ ስም ስልጣን ላይ የተቆናጠጡት ነፃ አውጭ መሪዎች ይህን ሲሉ ነፃ በወጡት ሃገሮቻቸው ምድር የመድበለ-ፓርቲን ህልውናን ከፈቀዱ በተቃዋሚ ፓርቲዎች በኩል የቀድሞ ቅኝ ገዥዎቻቸው በሃገሮቻቸው ፖለቲካ ውስጥ እጃቸውን ያስገቡ ይሆናል ከሚል ስጋት ነው። ይህን ሃሳብ ከዋሚ ኒክሩማን ጨምሮ ብዙዎቹ የአፍሪካ ነፃ-አውጭ ፓርቲ መሪዎች የሚያራምዱት አቋም ነበር።

ይህ ዘይቤ አሁን ድረስ በስልጣን ላይ ባሉ ትቂት «የነፃነት አባት» ፕሬዚዳንቶች ላይም ይስተዋላል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት የዙምባቤው ሮበርት ሙጋቤ ናቸው። ሮበርት ሙጋቤ ተቀናቃኞቻቸውን ሞርጋን



ቻንጋራይን «የምዕራባዊያን ተላላኪ» ሲሉ ዘወትር የሚወርፏቸው ከዚህ የተነሳ ነው። ይህ እሳቤ ከቅኝ ግዛት ማክተም በኋላ በጥቂር አምባገነን መሪዎች ላይ ብረት አንስተው ስልጣን በያዙ (እንደ ኢህአዴግ ያሉ) የቀድሞ ሽማቂዎች ዘንድም እንደልምድ ተይዞ በመቀጠሉ በአህጉሪቱ አብዛኛ ሃገሮች ስኬታማ የመድበለ-ፓርቲ ስርአት መመስረት እንዳዳገተ "African Studies Association" የተባለው ተቋም በሚወያባቸው ዕሁፎቹ ያስረዳል። ከነፍጥ አንጋች ነፃ አውጭዎች ወገን የሆነው ኢህአዴግም መንግስታዊ ስልጣን የመያዙ እጣ ሲገጥመው የመድበለ-ፓርቲ ስርዓትን ህልውና በህገ-መንግስት ቢፈቅድም ተግባሩ ላይ ሲመጣ የሮበርት ሙጋቤን ቃል በመዋስ ጠንካራ ተቃዋሚዎችን በምዕራባዊያን («በኒዎሊበራል ሃይሎች») ተላላኪነት ይከሳል፣ በልማት አደናቃፊነት ይፈርጃል፣ ነገሩ ሲጠና ደግሞ ወደ እስርቤት ያግዛል። የአፍሪካ ነፃአውጭ መሪዎችን የአንድ ጠንካራ ፓርቲን አስፈላጊነት ዜማም ቀየር አድርጎ ‹ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ለልማት የሚተጋ አውራ ፓርቲም ነው፤ ያደግሞ እኔ ነኝ› ይል ይዟል። በውጤቱም የዲሞክራሲ መገለጫ የሆነው የመድበለ-ፓርቲ ስርዓት እና እሱን ተከትሎ የሚመጣው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እድገት ጉዞው አንድ ወደፊት ሶስት ወደ ኋላ አይነት እየሆነ ያለበት ሁነት ሰፍኗል።

## በሰላማዊ ትግል ላይ የኢህአዴግ «ጌም»!

ኢህአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ ማግስት ሃገርን በጋራ ለመምራት ከመኢሶን፣ ኢህአፓ፣ ኢዲሃቅ እና ኢሠፓ በቀር የሃገሪቱን የለውጥ ሃይሎች የሚያሳትፍ ጥሪ አድርጎ ነበር። ይህ ወቅት ለኢህአዴግ የትጥቅ ትግሉን ድል በሴራ ፖለቲካ ደግፎ ነጋሲነቱን በአስተማማኝ መደላድል ላይ ያስቀመጠበት ወሳኝ ጊዜ ነው። በሽግግሩ ወቅት የተደረገው የሰላም ጉባኤ ጥሪ፣ እሱን ተከትሎ ከባለድሉ ኢህአዴግ ውጭ ላሉ ፓርቲዎች የተረፈው የስልጣን ክፍፍል ጅማሬ እና የአቶ መለስን በስልጣን ላይ ብዙ አታዩኝም መሃላ ላስተዋለ ኢህአዴግ እስከ ሸበት ሽምግልና ዘመኑ ስልጣን ላይ ይኖራል ብሎ ለመጠርጠር ፍንጭ አይሰጡም ነበር። የሆነው ግን ሌላ ነው።

የሽግግር ወቅቱን በሚፈልገው መንገድ ማለፉን ያረጋገጠው ኢህአዴግ ጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን በዙሪያው የማቆየቱ አስፈላጊነት አልታየውም። በተለይ አነግ አስፈላጊነቱ ማብቃቱ ብቻ ሳሆን አስፈሪነቱም እየታየው መጣ። እናም

በስልጣን ዋዜማ የጀመረውን አህጼድን የማንጎቱን ስራ ስለጨረሰ አነግን «ጠባብ» የሚል ስም አንጠልጥሎለት መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ ሲል አሰናበተው። እስጊ የመሰለውን ሃይል ሳያስወግድ እንቅልፍ የሌለው የአቶ መለስ ፖለቲካዊ ስብዕና አነግን ካስወገደ በኋላ የሌሎቹ እስጊነት ስላልታየው በምርጫ ወቅት ያጅቡት ዘንድ ትተቸው ነበር። አቶ መለስ በአነግ ላይ ያደረጉት እርምጃ እስከ ህልፈታቸው አብሯቸው የኖረ ፖለቲካዊ ስብዕናቸው ነው። አነግን ለማጥፋት አህጼድ የተባለውን እንጎቻ የማብሰሉን ዘዴ ቀድ በ1997 ምርጫም በስራ ላይ ያዋሉት አካሄድ ነው። ቅንጅት የተባለውን ጠንካራ ተፎካካሪ ለማጥፋት «ነውጠኛው» የሚል ተቀፅላ ለጥፈው እስርቤት ሲያውርዱት ፓርላማ ገብቶ ውጥረቱን የሚያረግብላቸውን «ለዘብተኛ» (አሁን ቤተኛ የሆነ ይመስላል) ቅንጅት አነጉ። ቀጥሎም በህዝብ ልብ የታተመውን የፓርቲውን ምልክት ለሌላ «ለዘብተኛ» እንጎቻ ጆባ አሉት። በዚህ ሁኔታ ያዳከሙት ቅንጅት የራሱ የውስጥ ሽኩቻም ተጨምሮ የአነግ እጣ ገጥሞት ዋናዎቹን ወደ ስደት ደጋፊዎቹንም ወደ ተስፋ መቁረጥ ሸኝቷል። ይህን ተከትሎም የፖለቲካችን ሁለመና እንዳደረ ገንፎ የማያኝ ፈዛዛ እንደሆነ እዚህ ደርሷል።

## የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው «ነብይ»

ምርጫ 1997 ሁለት ሶስት አመታት ሲቀሩት አቶ መለስ ዜናዊ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራንን በዕህፈትቤታቸው ጠርተው ባናገሩበት ወቅት አንድ የዩኒቨርሲቲው ምሁር በሚያስደንቅ ድፍረት እና የሃሳብ ፍሰት ጠ/ሚኒስትሩ ሰላማዊ ትግልን ለማስኬድ የሚያስችል ስብዕና ባለቤት እንዳልሆኑ እና እርሳቸው (አቶ መለስ) በስልጣን ላይ እስካሉ ድረስ በሃገሪቱ በሰላማዊ ትግል ለውጥ ይመጣል ብለው እንደማይገምቱ የተናገሩበት ቪዲዮ ከሰሞኑ በማህበራዊ ሚዲያዎች ተለቋል። ሰውየው ይህን ሲናገሩ አቶ መለስ ምንም አይነት መልስም ሆነ ማስተካከያ እንዳይሰጧቸው አጥብቀው ጠይቀዋል። ምክንያታቸው ያደረጉት ደግሞ አቶ መለስ የሚመልሱላቸውን ሳይነግሯቸው እንደሚያውቁ በመጠቆም ነበር። የአቶ መለስን አፀፋ ላለመስማት አጥብቀው የጠየቁት ምሁር ንግግራቸውን የቋጩት ጠ/ሚኒስተር መለስን ቅን ሆነው ሃገሪቱንም በቅንነት ይመሩ ዘንድ በመማፀን ነው።



በግሌ ለአንድ ችግር መፍትሄ ለማግኘት በችግር ፈጣሪው ሰው ፊት ስለችግር ፈጣሪነቱ አስረግጦ መናገር ምትክ የሌለው መፍትሄ ነው ብየ አምናለሁ። በሃገራችን ግን ይህ የተለመደ አይደለም። እንኳን በመንግስት የመጨረሻው ቁንጮ የተቀመጠን ሰው ቀርቶ ለምንቀርበው ሰውም እንዲህ እንቅጩን መናገር አይሆንልንም። የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲው ምሁር ግን ከዚህ ተዋጹ ሰው ናቸውና ድፍረታቸው አድናቆትን ያጭራል። በመቀጠል ስለአቶ መለስ ፖለቲካዊ ስብዕና የተናገሩት ነገር እውነትነቱም ትንቢትነቱም አስደናቂ ነው። አቶ መለስ እያሉ በሰላማዊ ትግል ለውጥ እንደማይመጣ በ1997 ከወሰዷቸው እርምጃዎች መረዳት ቀላል ነው። የምሁሩ ንግግር ግን የ1997ቱን ምርጫ ተከትሎ ከተደረገው የአቶ መለስ ተስፋ አስቆራጭ እና አሳዛኝ እርምጃ ቀደም ብሎ የተነገረ ስለሆነ ነው ትንቢትነው ማለቴ!

እኔም የሰውየውን ሃሳብ እጋራለሁ። አቶ መለስ እያሉ በሰላማዊ ትግል የመንግስት ለውጥ ይመጣል ብሎ መጠበቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ እንደ ማሾለክ ያለ ቀቢፀ ተስፋ ይመስለኛል። ለዚህ ዋነኛ ምክንያቶቹ የምርጫቦርድ እና የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ገለልተኝነት ጉዳይ አንዱ እና ዋናኛው ሲሆን ኢህአዴግ ለሰላማዊ ትግል ማስኬጃ እንቅስቃሴዎች የሚሰጠው ትርጉምም ሌላው ነው። አቶ መለስ ከ1997 ምርጫ በኋላ ለሰላማዊ ትግል ጉዞ እንደ እስትንፋስ የሚያስፈልጉ እንቅስቃሴዎችን ስማቸውን ቀይረው በሌላ ተክተዋቸው ነበር። ለመጥቀስ ያህል ሰላማዊ ሰልፍ «የጎዳና ላይ ነውጥ» የሚል አስገራሚ ስም ተሰጥቶት በጥይት የሚያስቆላ ድፍረት ሲሆን፤ብዛታቸው በአይን የሚታይ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ያነገቡ እልፍ ሰላማዊ ሰልፈኞችም «ጥቂት ባንክ ዘራፊዎች» ወደ ሚል ተራ ውንብድና አንሰው ነበር። የመድበለ ፓርቲ ስርዓት በህገ-መንግስት በታወጀበት ሃገር የተቃውሞ ፖለቲካ ፓርቲ አባል፣ አመራር ወይም ደጋፊ መሆን በፀረ-ሰላምነት፣ በፀረ-ህዝብነት እና በልማት አደናቃፊነት የሚያስፈርጅ «እርጉምነት» ከሆን ሰነበተ። እነዚህን የሰላማዊ ትግል ስልቶች በበጎ ጎናቸው አይቶ፣ የዲሞክራሲያዊ መንግስት ዋነኛ መገለጫ ወደ ሆነው ልዩነትን በውይይት መፍታት ካልሆነ ደግሞ በልዩነት የማለፍን መሰረታዊ ነገሮች መቀበል ያቃተው የአቶ መለስ ኢህአዴግ ለሰላማዊ ትግልም ሆነ ለምርጫ ያለው ትርጉም አጠያያቂ ነው።

ሌላው ተስፋ አስቆራጭ ነገር አቶ መለስ ለፓርቲያቸው አዲስ አበባ ላይ ሙሉ በሙሉ መሸነፍ የሰጡት ትርጉም ነው። ነገሩን «ሽንፈት» ብሎ ከመጥራት ይልቅ አቶ መለስ ያሉት ‹የአዲስ አበባ ህዝብ በነበሩብን ትቂት ድክመቶች ምክንያት ባለመደሰቱ አካሄዳችንን እንድናስተካክል ማስጠንቀቂያ ሰጠን እንጅ አስተዳደራችንን ጭርሱን አልፈልግም ማለቱ አይደለም› የሚል ግራ አጋቢ ትንታኔ ሰጡ። አባባሉ በወቅቱ የኢህአዴግ አንጎል ከነበሩት ከአቶ መለስ አፍ መስማቱ በሃገሪቱ በምርጫ የመንግስት ለውጥ ይመጣል የሚለውን እሳቤ የሚፈታተን ነው።

በድህረ 1997 ምርጫ ኢህአዴግ የተያያዘው ተመዕዋች ፓርቲዎች የማፍላት ስራ ሌላው ፓርቲውን ትዝብት ውስጥ የጣለና በሰላማዊ ትግሉ ላይ የተፈጠረ ነቀርሳ ነው። እነዚህን ፓርቲዎች የሚመሩ ሰዎች የኢትዮጵያን ህዝብ የባርነት ሌሊት የሚያረዝሙ፣ በሰላማዊ ትግል ላይ የሚዘባበቱ፣ ከኢህአዴግ ጋር ከገቡት ሃገርን በዲሞክራሲ እጦት ቀፍድዶ የመግዛት እና የማስገዛት ቃልኪዳን ባለፈ የሃገር እጣፋንታ የማያስጨንቃቸው፣ በአስመሳይ አካሄዳቸው ለእውነተኛ ለውጥ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችን ልፋት ገደል የሚከቱ ስለሆኑ ከታሪክ ተወቃሽነት አያመልጡም። እነዚህ ፓርቲዎች ለሰላማዊ ትግል መቀጨጭ ከኢህአዴግ ያላነሰ ሚና ያላቸው፣ ለበደላቸው የሚበቃ ቅጣት የማይገኝላቸው የለውጥ ጠሮች ናቸው። ፓርቲዎቹ ለተፈጠሩለት የኢህአዴግ የመድበለ-ፓርቲ ስርአት አምጥቻለሁ ክርክር ማስረጃነት መሪዎቻቸው በምርጫ ሰሞን የሚወስዱት ገንዘብ እና ከኢህአዴግ ጋር የሚፈራረሙት የስነ-ምግባር ሰነድ በቂ ነው። ኢህአዴግ ዘጠና ዘጠኝ በመቶ በሆነ ውጤት «ማሸነፉም» ሆነ «አውራ ነኝ» በማለቱ የዲሞክራሲ ተገዞር መበላቱ አያስጨንቃቸውም። ፓርቲዎቹ ከኢህአዴግ ጋር በገቡት ኪዳን ኢህአዴግን የመድበለፓርቲ ስርዓት ምልክት የሆነውን ከተቀናቃኝ ፓርቲዎች ጋር መወዳደሩም፣ እንደነገሩስ ከስልጣን ላይ አለመጥፋቱም እንዳይቀርበት በማድረጋቸው ከኢህአዴግ ዘንድ ብድራታቸውን አያጡም። ለኢትዮጵያ ህዝብ ግን በአንዳች አይጠቅሙትም። አይጠቅሙትም ማለት ግን አይጎዱትም ማለት አይደለም! በድህነቱ ከመዘበት፣ በዲሞክራሲ እጦቱ ከማላገጥ፣ በለውጥ ፋላጎቱ ላይ ደንቃራ ከመሆን በላይ ምን ጉዳት አለ? አጥፊነታቸውን ለመቀነስ ታዲያ ሰላማዊ ትግሉ ከኢህአዴግ እኩል እነዚህን ፓርቲዎች ወደ መታገልም ማደግ አለበት።



ኢህአዴግ በምርጫ 2002 ዘጠና ዘጠኝ በመቶ በሆነ ድምፅ ማሸነፉን ተከትሎ ያስወጣው ሰልፍ ላይ አቶ መለስ ፊት ላይ ይነበብ የነበረው «ሆድ ሲያውቅ...» የሆነ የድልአድራጊነት ደስታ፣ የኢህአዴግ ጠቅላይ የፓርላማ ባለቤትነት የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እድገት ማሳያ መሆኑን የተነተኑበት ሁኔታ ሁሉ የሰላማዊ ትግልን ተስፋ ሰጭ እድገት ሳይሆን ተቃራኒውን አመላካች ነው። ይብስ የሚገርመው ተቃዋሚ ፓርቲዎች የፓርላማ ወንበር ባላገኙበት ሁኔታ በሃገራዊ ጉዳዮች መሳተፋቸው እንደማይስተጓጎል ቃል የገቡበት ንግግር ፓርቲውን ብቻ ሳይሆን ሰውየውንም እንደግለሰብ ትዝብት ውስጥ የጣለ ነበር። ባለፉት ሃገራዊ ምርጫዎች ተቃዋሚዎች በፓርላማ ወንበር ይዘው እንኳን ገና መናገር ሳይጀምሩ በ ‹ሰአት አልቋል› ሰበብ ሃሳባቸው እንዳይደመጥ ሲደረግ ያላየን ይመስል ‹ተቃዋሚዎች ፓርላማ ባይገቡም ግድ የለም በሃገራቸው ጉዳይ ይሳተፋሉ› ማለት፣ አልፎ ተርፎ በፓርላማ ወንበር ላይ ሁሉ የአንድ ፓርቲ አባላት መኮልኮል የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካ እድገት መገለጫ ነው ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ሰላማዊ ትግል፣ ምርጫ፣ የመድበለ-ፓርቲ ህልውና ማለት በኢህአዴግ አረዳድ ምን ማለት እንደሆነ ግር ያሰኛል።

በተጨማሪ የአቶ በረከትን የሁለት ምርጫዎች ወግ ላነበበ ኢህአዴግ በሰላማዊ ትግል የሚቀናቀኑትን ፓርቲዎች ሚያያበትን እይታ በደንብ ያሳያል። በበኩሌ የአቶ በረከትን መፅሃፍ ሳነብ የተረዳሁት ለኢህአዴግ በሰላማዊ መንገድ በሚፎካከሩት ፓርቲዎች እና በጫካ በሳንጃ በአፈሙዝ ሲዋጋው በነበረው ደርግ መሃከል ልዩነት እንደሌለ ነው። ለኢህዴግ የተለየ ሃሳብ ያለው ሁሉ ጠላት ነው፤ጠላት ደግሞ ድባቅ መመታት አለበት! ለዚህ ይመስለኛል የቅንጅትን አመራሮች እና ደጋፊዎች እስሩንም፣ ጠብመንጃውንም፣ ህጉንም፣ ፕሮፖጋንዳውንም ተጠቅሞ ደብድቧቸው እስካሁንም ስማቸው እንዳይነሳ የሚፈልገው።

## ተስፋ አለ?

ስልሳን ሳይደፍኑ ሞት የቀደማቸው አቶ መለስ የሚመሩት ፓርቲ ዋና ከመሆን አልፈው ፓርቲው ማለት እሳቸው፤ እሳቸው ማለትም ሃገር እስከ ሚመስል ድረስ የእምባገነንነትን ከፍታ ረግጠው ነበር። ሰውየው ወደ እምባገነንነቱ ከፍታ ይወጡ የነበረው ዋና ዋናዎቹን የዲሞክራሲ መርሆዎች

ያሳለፈችው ሃገራችን አሁን የሚያስፈልጋት ተጨባጭ ውጤት የሚያመጣ እርምጃ እንጅ እንዳለፉት ትግሎች መስዕዋትነትን ብቻ የሚያመጣ ሆኖ የሚቀር መሆን የለበትም። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ በግሌ አዋጭ የሚመስሉኝን የቢሆን መንገዶች ላሳይ።

መንገድ አንድ፡ ይህ መንገድ ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ እጅ ያለ እና ተመራጭነት ያለው መንገድ ይመስለኛል። እንደሚታወቀው ኢህአዴግ ለረዥም ዘመን አሸናፊነትን ብቻ ሰንቆ በሚነሳው የአቶ መለስ ፖለቲካዊ ስነ-ልቦና ሲሾር የኖረ ፓርቲ ነው። ምርጫውም ምርጫ፣ ድርድሩም ድርድር የሚሆነው ኢህአዴግን አሸናፊ እስካደረገ ድረስ ብቻ ነበር። ይህ ይሳካ ዘንድ ደግሞ ምርጫ ቦርድን አይነት የዲሞክራሲ ተቋማት ቀርቶ ሽምግልናን የመሰሉ በሃገራችን ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ማህበራዊ ልማዶች ሳይቀሩ ኢህአዴግ በአሸናፊነት ማማ እንዲቀመጥ በሚሰሩ ግለሰቦች እንዲዘወሩ ተደርጎ ኖሯል። ይህ በርግጥ ፓርቲው እስከዛሬ ስልጣን ላይ እንዲቆይ ማድረጉ እርግጥ ነው። ስልጣን ላይ ደግሞ እንደምንም ብሎ መሰንበት ይቻል ይሆናል እንጅ እንደ መለኮት ዘላለም ስልጣን ላይ መቀመጥን አያስችልም። ተወደደም ተጠላ አንድ ቀን ወንበር መከዳቱ አይቀሬ ነው። ኢህአዴግ አሁን በሚያደርገው መንገድ ስልጣን ላይ መሰንበት ደግሞ የማይቀረውን አወዳደቅ የሚያከፋ እንጅ የሚያሳምር አይሆንም።

ኢህአዴግ ስልጣን ከማናቀሩ የተነሳ ስልጣን ላይ የቆየበት ዘመን ርዝመት ለራሱ የታወቀው ባይመስልም የቆየበት ዘመን እጅግ ረዥም ነው። ከዚህ በላይ ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችል መስህብም የለውም። በፖለቲካው ሆነ በኢኮኖሚው ረገድ አመጣሁ የሚለው ለውጥ ረዥም የስልጣን እድሜውን የሚመጥን አይደለም። ስለዚህ ፓርቲው ወደደም ጠላም ህዝቡ ለውጥ ይፈልጋል። ለውጡን ሰላማዊ በማድረጉ በኩል ደግሞ ከኢህአዴግ ብዙ ይጠበቃልና ሁሌ ላሸንፍ ባይ ፖለቲካዊ ስነ-ልቦናውን ከአቶ መለስ ጋር መቅበር ይጠበቅበታል። ድርድር ማለት ሽንፈት ማለት እንዳልሆነ ተገንዝቦ ስለሃገር ያገባኛል ከሚሉ ሃይሎች ጋር ሁሉ የእውነት የሆነ ድርድር ያደርግ ዘንድ ግድ ነው። ይህን ማድረግ ለራሱም የሚጠቅመው መንገድ ነው። ድርድሩ የዲሞክራሲ ተቋማትን እና የመገናኛ ብዙሃንን ገለልተኝነት የሚያረጋግጥ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በነፃነት ይንቀሳቀሱ ዘንድ የሚፈቅድ ፖለቲካዊ ከባቢ የሚያመጣ መሆን አለበት። ይህን ካደረገ በኋላ



ያለ እኔ አይሆንለትም የሚለው ህዝብ ይመርጠው እንደሆን የሚያይበት፣ ከዚህ የተለየ ውጤት ሲመጣ ከቻለም የሚቀበልበትን ስነ-ልቦ አዳብሮ ነፃ ምርጫ ማካሄድ ይጠበቅበታል።

መንገድ ሁለት፡ ለዚህኛውም መንገድ ስምረት የኢህአዴግ ለለውጥ መዘጋጀት ያለመዘጋጀት ዝንባሌ ወሳኝ ነው። ኢህአዴግ ብዙ አመት ሀረ-ልማት፣ ሀረ-ሰላም እያለ ሲያብጠለጥላቸው ከነበሩት ተገዳዳሪዎቹ ጋር ቁጭ ብሎ መደራደሩን (መንገድ አንድን) እንደ ሽንፈት ከቆጠረው ሃገሪቱን ለተወሰነ አመት ተረክቦ፣ ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቿን መልክ አስይዞ ለዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚያዘጋጅ የባለሙያዎች መንግስት (Technocratic Government) እንዲቋቋም ማድረግ ቢችል በለውጥ ስም የሚመጣውን ደም መፋሰስ እና የንብረት ውድመት ማስቀረት ይቻላል። የቴክኖክራቶች መንግስት ጥልቅ እውቀት እና ልምድ ያላቸውን ምሁራን በየተማሩበት መስክ ሃገራቸውን እንዲያስተዳድሩ በየሚኒስተር መስሪያቤቱ እና በየሴክተሩ ይሾማል። ይህ ሲደረግ የተሿሚዎቹ ፖለቲካዊ አቋም ግምት ውስጥ አይገባም። የዚህ አይነት መንግስታት ዋናው አላማ ሃገርን ከገባችበት ማጥ ማውጣት ስለሆነ የሚፈለገው ሙያዊ ብቃታቸው እንጅ ፖለቲካዊ አቋማቸው አይደለም፤ስልጣን ላይ የሚቆዩትም ለትቂት አመታት ነው።

ይህን ዘዴ ጣሊያን ከሶስት አመት በፊት ተጠቅማበት ነበር። በወቅቱ ጣሊያን በከፍተኛ የኢኮኖሚ ዝቅጠት ላይ የነበረችበት ወቅት ነበር። ይህን ተከትሎ የሃገሪቱ መራሔ መንግስት የነበሩት ቤርሉስኮኒ የጣሊያን ፓርላማ በመንግስታቸው ላይ ያለውን እምነት የሚለካበት (Vote of confidence) አስርተው ያገኙት ውጤት ዝቅተኛ ሆነ። ይህም ለሃገሪቱ ፕሬዚዳንት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ለሁለት አመት የሚቆይ የቴክኖክራቶች መንግስት ተቋቋመ። አዲሱን ካቢኔ እንዲመሩ የተደረጉት በወቅቱ በአውሮፓ ህብረት ሴንትራል ባንክ ውስጥ ይሰሩ የነበሩት ማሪያ ሞንቲ ሲሆኑ ሰውየው በሙዊ ብቃታቸው እና በፖለቲካዊ ስብዕናቸው መልካምነት የተመሰከረላቸው እንደሆኑ በሰፊው ተዘግቦ ነበር። እንደተጠበቀውም ማሪያ ሞንቲ እውቅ ባለሙያዎችን በየሚኒስተር መስሪቤቱ መድበው ካቢኔያቸውን አዋቅረው ሃገሪቱም ከችግሯ አገግማ ወደ ተሻለ መንገድ እንድትጓዝ ሁለት አመት በርትተው ከሰሩ በኋላ ሃገራዊ ምርጫ ተደርጎ ለተመረጠው መንግስት ሃገሪቱን አስረክበዋል።

መስያ ሊሆን አይገባም ነበር። አይንን በጨው አጥቦ መዋሸትስ በምን ሁኔታ ነው የብልህነት መገለጫ የሚሆነው?

በተወሰነ መልኩ የተሻለ ፖለቲካዊ ግንዛቤ ቢኖረን ኖሮ ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚቋምጠው አካልም ለመምራት ያለውን ብቃት ከግምት ውስጥ ያስገባ ነበር። እዚህ ላይ ሙሴ የእስራኤልን ህዝብ ለመምራት ከፈጣሪ በተመረጠ ጊዜ የተናገረውን ማስታወስ ይቻላል። የሚመራውን ህዝብ ጠያቂነት አስቀድሞ የተረዳው ሙሴ ይሄን ታላቅ ህዝብ በኔ አቅም መምራት እንዴት ይቻለኛል ብሎ ከመረጠው ፈጣሪ ጋር ሙግት ገጠመ። የሙሴ ስጋት እንግዲህ ጠያቂ ህዝብ እንዴት እንደሚያስፈራና እንደተንደረደሩ ማስተዳደር እንደማይቻል ያሳያል። የሚሊሺያ ልብስ አውልቆ ሱፍ መልበስ እና በቃላት ጨዋታ ጸጉር መሰንጠቅም ፖለቲካን በተሻለ ለሚያውቅ ህዝብ በቂ የመሪነት ችሎታ አይደለም።

## ፖለቲካ ሁለንተና ነው!

ከሌሎች እንስሳት በተለየ የሰው ልጅ ማህበራዊ እና ፖሊቲካዊ እንስሳ በመሆኑ ፖሊቲካን ከሰው ልጅ ለይቶ ማስቀመጥ አይቻልም። ፖሊቲካን በቅርቡ መከታተል፣ ብሎም በፖለቲካው ዓለም የራስን ድርሻ ለመወጣት በቂ እውቀት ማካበት እንደ ስልጣን ወዳጅነት ወይም ነገር ፈላጊነት መታየት የለበትም፤ ነገሩ ተፈጥሮአዊ ነውና።

መውጣት መግባታችን ፖሊቲካ ነው። የኑሮ መርከስ መወደድ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት በቅጡ ማግኘት አለማግኘቱ፣ የሥራ እድል ጉዳይ፣ አንድ መስሪያ ቤት ሄደን በአግባቡ መስተናገድ አለመስተናገዳችን፣ እና ሌሎች የህይወት ድር እና ማጋችን ሁሉ የሚዳወረው በፖሊቲካ ነው። ‹እኔ ፖለቲካ አልወድም፣ የሆነ ቢሆን አያገባኝም› ማለት አልበላም፣ አልጠጣም፣ ትራንስፖርት አልጠቀምም፣ ገበያ ወይ ሱቅ ሄጄ ዕቃ አልገዛም፣ ስራ አልፈልግም ወዘተ ማለት መሆኑ ነው።

## ፖለቲካዊንቃት ለምን?

የአንድ ሀገር ህዝብ ፖለቲካዊ ንቃት ማደግ ለሀገር እድገት የሚያበረክተው በጎ ተፅኖ ብዙ ነው። ከዋነኞቹ ተፅዕኖዎች መሃከል የመንግስትን ስልጣን



ማረቅ አንዱ ነው። የተሻለ ፖለቲካዊ ንቃት ያለው ህዝብ ህገ-መንግስታዊ እና ሰብአዊ መብቶቹን ጠንቅቆ ያውቃል፣ መንግስት ምን እየሰራ እንደሆነ በአንክሮ ይከታተላል። የወደደው ሲደረግለት ደግፉል፣ ትክክል ያልመሰለውን ይጠይቃል። ይህ ደግሞ ማንኛውንም የመንግስት እንቅስቃሴ ጥንቃቄ የተሞላበት ያደርገዋል። ይህ ሆነ ማለት ህገ-መንግስታዊነት እና ተጠያቂነት በመንግስት ዘንድ ይኖራል ማለት ነው። ጠቅለል ሲልም መንግስታዊ አምባ ገነንነት የመፈጠር እድሉ የቀነሰ ይሆናል ማለት ነው። ነገሩ በተቃራኒው ከሆነ ደግሞ ህገ-መንግስቱ ምንም ያህል በዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተቃኙ አንቀጾችን ቢይዝ አፈፃፀሙን ህዝብ ካልተከታተለው መንግስትም ከህገ-መንግስታዊነት ሰያፈነግጥ ሃይ ባይ ከሌለው ህገ-መንግስት ባለበት ሁኔታም ቢሆን መንግስታዊ አምባገነነነት ሊሰፍን ይችላል። መሪዎችም ወደ ግብዝነት እና ማን አለብኝ ባይነት ሊያሽቆለቁሉ የሚችሉበት እድልም ሰፊ ይሆናል።

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ሙስናን ለመዋጋት፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ለማምጣት፣ በአጠቃላይ የሰለጠነ ፖለቲካዊ ድባብ ለመፍጠር ህዝባዊ የፖለቲካ ንቃት አስፈላጊ ነገር ነው። እንደሚታወቀው ዴሞክራሲን ለመገንባት ህዝባዊ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና አለው።መንግስታዊም ሆነ ሌላ አይነት ሙሰናን ለመከላከል መንግስት የሀገርን ሀብት እንዴት እያስተዳደረ እንዳለ መከታተል የሚያስችል ህዝባዊ ንቃት ያስፈልጋል። የነቃ ህዝብ ከመተየቅ አይሰንፍም። የሚጠይቅ ህዝብ የሚመራ መንግስት ደግሞ እጆቹን ከሙስና እና ብልሹ አሰራር እጆቹን ይሰበስባል። ይህ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልንና የተስተካከለ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያመጣል። ሰፋ ወዳለው ፖልቲካዊ ንቃት ሲኬድ ደግሞ በየጊዜው የሚወጡ ህጎችን ከዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ የመተቸት፣ የመደገፍ እና የማስተካከያ ሃሳቦችን መሰንዘርን ያስችላል።

## ጉዞ ወደ ፖሊቲካዊ ንቃት

ሀገራችን የቆየ የመንግስትነት ታሪክ ቢኖራትም የፓርቲ ፖለቲካ ልምዷ ከደርግ ስርአት ጋር የሚቆጠር ዕድሜ ያለው ነው።በቅ ካሉት ፓርቲዎች ውስጥ ደግሞ ህዝባዊ የፖለቲካ ንቃትን ማሳደግን ነገሬ ብሎ የያዘው ፓርቲ መኢሶን ነበር። እንደ መኢሶን ፕሮግራም ፓርቲ ምስረታ ወደ ሚባለው ስራ ከመኬዱ በፊት ህዝባዊ ንቃት ለማምጣት መሰራት አለበት። ይህ ድንቅ

ይህ ምናልባትም በመንግስት በኩል ያልው ማንኛውንም ክሽታ የመቆጣጠር «ጠንቃቃነት « እና አስጊ ሆኖ የተገኘ እንቅስቃሴን ድባቅ ለመምታት ያለውን «ብርታት» በማሰብ የሚያውቀውንም ለመጠየቅ «ብንናገር እናልቃለን» በሚል ዝምታን የመረጠበት ነገር ይስተዋላል። በመንግስት በኩልም የ1997ን ምርጫ ተከትሎ የተደረጉ የተማሪዎችን እንቅስቃሴዎች በመልካም ያየው አይመስልም። እንደውም ነገሩን ከትምህርቱ የታለመለተን ግብ አለመምታት ጋር አያይዞት አረፈው። እንግዲህ መደገፍና መቃወም የትምህርቱን ግብ መሳት ከሆነ ትክክለኛ ግብ ተብሎ የታሰበው ምን እንደሆነ ግልፅ አይደለም።

## መፍትሄ ቢሆነን

ሁለንተናዊ ኑሮአችን የፖለቲካዊ ማንነታችን አሻራ ያረፈበት እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል። በሌላ አባባል ፖለቲካችንን በቅርብ መከታተል የውዴታ ግዴታችን ነው ማለት ነው። ይህን ማድረጋችን መሰረታዊ ችግራችንን ተረድተን ለመፍትሄው የበኩላችንን እንድናደርግ አቅጣጫ ያሳየናል። እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄ አሁን ያለውን ውስን ፖለቲካዊ ንቃታችንን ለማሳደግ ምን መደረግ አለበት የሚለው ነው።መንገዱ የትየለሌ ነው ነገር ግን ወሳኝ የመሰሉኝን፣ መሰረታዊ አውቀትን ለማሻሻል የሚረዱ መንገዶች ያልኩአቸውን ላንሳ።

በመጀመሪያ ስለፖለቲካ ያለን አመለካከት መቀየር አለበት። በመሰረታዊነት ከፖለቲካ ጋር ያለን ትስስር ተፈጥሮአዊ መሆኑን ማመን አለብን። ከፖለቲካ ለመራቅ የምናደርገው እርምጃ ሁሉ ወደ ተገሸርነት የሚያስጠጋን እንደሆነ መረዳት አለብን። ፖለቲካን ለማወቅ ደግሞ የግድ በድግሪ ላይ ድግሪ መጫን የለብንም። በማንበብ፣ ሚዛናዊ ዜና (መረጃ ) የሚያቀርቡ መገናኛ ብዙሃንን መከታተል፣ ቢያንስ በሳምንት አንድ ሁለት ጋዜጦች ብናነብ ቀስ በቀስ ወደ ጉዳዩ እንድንሳብ ያደርገናል።አሁን በሀገራችን አብዛኛው ሰው የተካነው ኪስን የመተንተን እውቀት ትምህርት ቤት ገብቶ ከመማር የመጣ አይደለም። ለኪስ የምንሰጠውን ጊዜ እና ያገባኛል ባይነት በጣም ጥቂቱን እንኳን ወሳኝ ለሆነው ፖለቲካዊ ሁነቶቻችንን ለመከታተል ብናውለው ብዙ ነገራችን ይቀየር ነበር።

እንደሚታወቀው አወዛጋቢው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማስተዳደር የወጣው ሕግ የሲቪክ ማህበራት በግንዛቤ ማስጨበጥና ዲሞክራታይዜሽን



ሥራ ላይ የነበራቸውን አስተዋፅኦ አዳክሞታል። በአሁኑ ሰዓት ያሉ የሲቪክ ማህበራት እንድም መንግስት ራሱ እንደፈለገ የሚዘውራቸው አለያም መንግስት እንዳይከፋባቸው በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሰሩ ናቸውና ከነሱ ብዙ መጠበቅ አይቻልም። በመሆኑም ይህን ስራ ለመስራት በተሻለሁኔታ መስራት የሚችሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው።

የገዢውም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን ሲመለምሉ የአባላቱን ቁጥር ከማሳደጉ ጎንለጎን የአባላቶቻቸውን ፖለቲካዊ ንቃት ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም አባል አንድ አይነትፖለቲካዊ ንቃት  ደረጃ ሊኖረው ስለማይችል ሁሉንም በወል አባላት ብሎ ከመፈረጅ ይልቅ ንቃታቸውን ባገናዘበ መልኩ ደረጃ ተሰቶአቸው ክፍተት ያለበት ክፍተቱን የሚሞላበትን ሁኔታ መመቻቸት ይኖርባቸዋል።

በዚ በኩል ደርግ የተሻለ የአባላት አመላመል ስርአት ነበረው። ሁሉም አባላት እኩል ደረጃ አልነበራቸውም። እንደ ንቃታቸው እና የተመለመሉበት ጊዜ ርዝመት «ታሳቢ»፣ «እጩ»፣ እና «ሙሉ አባል» በመባል ይከፋፈሉ ነበር።  አሁን ወዳለው ልምድ ስንመጣ ምን አይተውና ፈልገው አባል እንደሆኑ እንኳን የማያውቁ፣ አለአማወቃቸው ደግሞ ግድ የማይሰጣቸው አባላትን ሰብስቦ ይሄን ያህል ሚሊዮን አባላት አሉን ማለቱ ብቻ እንደ ትልቅ ግብ እየተቆጠረ ያለበት ነገር ይታያል። አባላቱንም በጾታ፣ በሊግ፣ በዘር፣ በእድሜ፣ የታገለ እና ያልታገለ በማለት ካልሆነ ፖለቲካዊ ንቃትን በተመለከተ ሲከፋፈሉ አያጋጥምም። ይህ እውነታ በተቃዋሚ ፓርዎችም የሚስተዋል ነገር ነው። በዚህ መንገድ የተሰበሰቡ አባላት ለፓርትውም ቢሆን አይበጅም። ነገሩ ክር ስቶስን ሳያውቁ ሲከተሉ እንደነበሩት እአላፍ ህዝቦች በቁርጥ ቀን የገቡበት ሲጠፉ ይችላል፤ ምክንያቱም ዕናት የሚመጣው ከዕውቀት ነውና።

## 6.2 ስደት በየዘመኑ እና በየፈርጁ

ዜግነት በውልደት ወይም በህግ የሚገኝና ሰዎችን ከአንድ ሃገር (በህግ ከሆነ ደግሞ ከአንድም በላይ) ጋር የሚያስተሳስር ገመድ ነው። በህግ የሚገኘው የተሻለ ነገር ፍለጋ እናት ካልሆነች ሃገር ጋር በእትብት ሳይሆን በህግ፣ ከአንጀት ሳይሆን ካንገት የሚደረግ ህብረት ነው። በውልደት የሚገኘው

ዘሩፍናቸው በባለቀኖቹ ፋኖዎች ሲገለበጥም ያሸሹትን ገንዘብ ወደ ሀገር ካገዘና እንዲገባ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም። በእግራቸው የተተካው ደርግ ከሁሉ አልንሳህ ሲለው በሙስና አይጠረጠርም። ቢቻል ለሃገር ከየትም ብሎ ማምጣት ይከጅለው ይሆና እንጂ ከደሃ ሃገር መቀነት ገንዘብ ለመቆንጠር አይዳዳውም። ይህ በጨካኝ ፊቱ ላይ የተቀመጠ ውበቱ ነው።

የአሁኖቹ ደግሞ የነዋይ ነገር የመነሰሳቸው መጀመሪያ ነው። ‹ብዙ አመት አሸዋ ላይ ተንከባሎ የተዋጋዉ ጎበዝ ስኳር ሲልስ ተያዘ› ብለው የበረሃ ጓዳቸውን ገና ከጠዋቱ ዘብጠያ ያወረዱት በዚሁ በነዋይ ጉዳይ ነው። በማግሻው ሙሰኛና አሁን በታሰሩት መንጋ ባለስልጣናት መሃከል እንደአስፈላጊነቱ ብዙዎች ስኳር በመላስ ተከሰው ሌሎቹን ያጉሩበት ወደ ነበረው ዘብጥያ ወርደዋል።

ሙስናን በተመለከተ በመንግስት የሚወሰደው እርምጃ አንድም የዘገየ ነው ሁለትም ስር ነቀል አይደለም። በመሆኑም ሙስና በሃገራችን የፈጣን ስኬት መንገድ እየተደረገ መጥቷል። በተለይ የመንግስት ባለስልጣናት ገንዘብ በመመዝበር ከሀገር ውጭ በሚገኙ ዘመናዊ ባንኮች እንደሚያከማቹ የሚከስ ፍንጭ የተገኘባቸው አሁን አይደለም። ከስምንት አመት በፊት የመንግስት ዋና ዋና ባለስልጣናትን ጠቅሰው በውጭ ሃገር ገንዘብ ስለማሸሻቸው ማስረጃ አቅርቤ መሞገት እችላለሁ ያሉ አንድ ትውልደ ኢትጵያዊ የህግ ምሁር ተነስተው ነበር። መንግስትም ባይገፋበትም ‹ያለስራዩ ስሜ ጠፋ› ብሎ ግለሰቡን ስም በማጥፋት እከሳለሁ እያለ ነበር። በመጨረሻ የመንግስት ዋና የሆኑት ሰው በምሬት የመንግስት ሌቦች ገንዘብ እንደሚያሸሹ የተናገሩት ነገር የበፊቱን የመንግስት ስሜ ጠፋ ስሞታ እውነተኝነት ጥያቄ ውስጥ ይጥለዋል።

## ስደተኛ ቅርስ

በእኛ ጉብዝና ከሚሊዮኖች አመት በፊት አፋር በረሃ ውስጥ እንደቀበርናት የምንኮራባት ሉሲም በስደት ከኖረችበት ባህር ማዶ በ2003 ተመልሳለች። በወቅቱ ኢቲቪ ያቀረባቸው ባለሙያወችም ስፍረን፣ ቆጥረን እሷ መሆኗን አረጋግጠናል ብለዋል። በግሌ ሉሲ ወደ ቱሪስቶች በመሄዷ አልስማማም። ምክንያቱ ደግሞ ቅርሷ ቱሪስቶችን የመሳብ ተፈላጊነቷ ከፍ ያለሆኖ ሳለ ይህን በማይመጥን ሁኔታ የፈላጊ ያለህ እያሉ በአለም ዳርቻ መዞሩ ክብረ-ነክ ነው ብየ ስለማምን ነው። ለማንኛውም በስደት የቆየችው ቅርስ ምን ያህል ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ትርፍ እንዳስገኘች የተነገረ ነገር የለም።

እንደሉሲ ለመጎብኘት በመንግስት በኩል የማይላኩ፣ ቆጥረን፣ ለክተን የማንረከባቸው አንድም ለቅኝ ግዛት በመጡ ጉልበተኞች የተዘረፉ ሁለትም በሃገር በቀል ዘራፊዎች ባህር የተሻገሩ ብዙ ስደተኛ ቅርሶች አሉን። ስለሃገራችን ቅርሶች የአውሮፓን ሙዚየሞች ማጣበብ ዳንኤል ክብረት በአይኑ ካየው ተነስቶ ብዙ አስነብቦናል።

## ስደተኛ መንፈስ

ከተሰደደብን ዜጋና ቅርስ በተጨማሪ የብዙዎቻችን ያልተሰደደ አካል በመንፈስ ባህር አቋርጦ፣ እውቂያኖስ ተሻግሯል። ያለስደት መፍትሔ ያለ አይመስለኝም። ይድላን አይድላን ሳናውቅ ለመሄድ እግራችን ቁጭ ብሎም ይወዛወዛል። በእቃ መጫኛ ታንከር እንደ ንፍሮ ተከድነው ህይወታቸው ያለፈ ወገኖቻችንን አሳዛኝ ፍጻሜ እየሰማንም ስደተኛው መንፈሳችን መሻቱን አያቆምም።

## መኖር ማን ይጠላል ባገሩ…

ፈርጀ ብዙው ስደታችን ምክንያቱ ብዙ ነው። ዋናው ለስደት ክንፍ ማብቀል የሚያስመኙን ግን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግራችን ነው። ባእዳንን በለም መሬታችን አምርተው እንዲያፍሱ የሚጋብዘው መንግስታችን ዜጎቹ ሚሰደዱብትን መንገድ ህጋዊ እንዲያደርጉ ይመክራል እንጂ ለምን እንደሚሰደዱ ምክንያቱን በማሰላሰል መድከም አይፈልግም። የዜጎቹ እንደሞተ ውሻ መንገድ ለመንገድ መጎተትም አንድ ያጎደለው ነገር እንዳለ አያሳየውም። በምትኩ ስደተኞቹን በህጋዊ መንገድ እንዲሰደዱ አጥብቆ ይመክራል እንጂ። ምንም ሆነምን አንድ ሃቅ አለ ሃገራችን በጉያዋ የያዘችው ሃብት አንሶ አይደለም ልጆቿ በአመት አንድ ቀን ዝናብ ወደ ሚዘንብበት በረሃ ለአገልጋይነት የሚሰደዱት። ይልቅስ የስደታችንን ፈርጅ ያበዛው በስልጣን ላይ የሚጨክን መሪ እጦት፣ የሀገርበቀል ፖሊሲአለመኖር እናየመልካም አስተዳደር መጥፋት እንጅ።

በኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ እና በሻምበል ለገሰ ስፋው አጋፋሪነት የተከናወነዉ የደርግ መንግስት የሰፈራ ፕሮግራም ያመጣው በጎም ሆነ መጥፎ ተፅኖ (Impact Assesment) በሳይንሳዊ መንገድ እና በገለልተኛ ወገን ስላልተጠና አሉታዊና አዎንታዊ ጎኑን አወዳድሮ በርግጠኝነት መናገር አይቻልም። የሆነ ሆኖ ሰፈራው በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች መጠነኛ በጎ ተፅዕኖ እንዳለው መካድ አይቻልም።

## ጉዞ ወደ ምግብ ዋስና

የኮሎኔልመንግስቱ አስተዳደር የሰራውን ስርቶ ከስልጣን ከተሰናበተ በኋላ የመጣው የኢህአዴግ መንግስትም ገና ደርግን በመጣሉ ሀሴት ውስጥ እያለ ህዝቡን ቢያንስ በቀን ሶስት ጊዜ እመግባለሁ ቢልም ወደተግባሩ ሲመጣ በተራቡት ዜጎች ቁጥር ላይ መከራከሩ ላይ በረታ እንጂ ረሃብን ከሃገር ማጥፋቱ ዳገት ሆኖበታል። የሆነው ሆኖ እሱም እንደ ቀደምቶቹ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ከማውጣት አልቦዘነም። የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያግዛል ተብሎ በተቀረፀው መረሃ-ግብር ስር የሴፍቲኔት ፕሮግራም፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሰፈራን ማካሄድን እና ምርታማነትን መጨመር የሚሉትን ፕሮግራሞች ነድፎ ለተግባራዊነታቸው እየሰራሁ ነው ሲል ኖሯል። በመረሃ-ግብሩ ስር ካሉት ፕሮግራሞች አንዱ የሆነው የሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ዝናብ ቢዘንብም ባይዘንብም እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች ከለጋሾች በተገኘ ምፅዋት እህል ቀምሰው የሚያድሩበትን መንገድ ያመቻቻል። በፈቃደኝነት ላይ ተመሰረተ የሰፈራ ፕሮግራሙም የደርግን የግዳጅ ሰፈራ ስህተቶች ያረመ ሲሆን ሰፈራው የሚካሄደው በክልል ውስጥ ብቻ መሆኑ ሃገራዊ ትስስርን ከመፍጠር እና በቂ የመስፈሪያ ቦታዎችን ከማግኘት አንፃር የራሱ ዉሱንነቶች ይኖሩታል። የግብርና ምርታማነትን ለመጨመር የሚደረገው ጥረትም የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን አሰልጥኖ በሃገሪቱ ገጠራማ ቦታዎች በማሰማራት ለአርሶአደሩ ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግን፣ እንደ ማዳበሪያ፣ ምርጥዘር እና ሌሎች የግብርና ግብአቶች አቅርቦት ማሟላትንም ይጨምራል። ከዚህ ሁሉ በኋላም የበሬ ግንባር በምታክል መሬት ላይ «ተአምር» የሚሰሩ አርሶ አደሮችን የማብዛት አላማ ያለው ነው።



የሆነው ሆኖ የምግብ ዋስትናው ፕሮግራም ስሙን ገቢራዊ ለማድረግ ብዙየሚቀረው እንደሆነ በገጠር እና በከተማ እየታየ ያለው የምግብ እህል እጥረት፣ ከአመት አመት መቀነስን ያላሳየው የተረጂ ህዝብ ቁጥር እና ሌሎች ተዛማጅ እውነታዎች ምስክሮች ናቸው። በሌላ በኩል መረሃ-ግብሩን የነደፈው እና እየሰራበት ያለው የሃገራችን መንግስት የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንፃር አመርቂ ውጤት እንዳስመዘገበ ሲናገር በኩራት ነው፣ ስኬቱንም የሚያሳየውም በሪቫን ያሸበረቁ «ሚሊየነር» ሞዴል አርሶ አደሮችን በመሸለም ነው። ተሸላሚ አርሶአደሮቹ አሉኝ የሚሉት የጥሬ ገንዘብም ሆነ የንብረት መጠን አይን ከሚያየዉ ገፅታቸዉ ጋር አይገጥምም።

## ሦስቱ ምክሮች

በተከታታይ በተደረጉ ሃገራዊ ምርጫዎች አሸናፊነቱን እያወጀ ከገዥነት መንበር ያልጠፋዉ ኢህአዴግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በገዥ ፓርቲነቱ ላይ አውራነትንም ጨምሯል። የአውራነቱን ሃሳብ ይፋ ከማድረጉ በፊት ወደ አውራነቱ የሚያደርሰውን ጉዞ የጀመረው ከ 1997 አገራዊ ምርጫ ማግስት ባደረገው አባላትን የማብዛት ስራ እንቅስቃሴ ነው። እንቅስቃሴው ተከታታይ ስልጠናዎችን በመስጠት ተጀምሮ በማቅረብት እና በማደራጀት ያደገና ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ስራ ነው።

አስፈላጊው ስልጠና የተሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በእድሜ፣ በፆታ፣ በመኖሪያስፍራ (በሴል) እንዲራጁ ከተደረገ በኋላ «ንጉስ ለወደደው» የሚገባውን ሁሉ ለማድረግ እየተሞከረ ነው። የትምህርትም ሆነ የስራ እድሎች የሚሰጡትም በቅድሚያ ለአባላት መሆኑንም አዋሳ ላይ በተደረገዉ የፓርቲው ሰባተኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ በሲቀመንበሩ ማካይነት ይፋ ተደረገ። መደራጀትም ብቸኛው መፍትሄ ሆነ። የመደራጀትን መፍትሄነት አፅኖት ለመስጠት ሟቹ ጠቅላይሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ወጣቶችን ሰብስበው ሲያወያዩ ፊታቸው የተኮለኮሉትን እና እሳቸው አንድ ቃል በተነፈሱ ቁጥር ያጨበጭቡ የነበሩትን ወጣቶች ሶስት ምክር ምክር ልምክራችሁ አሉና «አንደኛ ተደራጁ፣ ሁለተኛ ተደራጁ፣ ሶስተኛ ተደራጁ» ሲሉ ነበር የመደራጀትን የማይተካ ሚና ያስረዱት። በዚህ መልኩ የማደራጀቱ እና የመደራጀቱ ስራ በሰፊው ተገፋበት። መደራጀቱ ለሚደራጁት በከተማ የስራና የትምህርት እድልን የሚያስገኝ ሲሆን በገጠር ደግሞ የተለያዩ የግብርና

ግብአቶችን ለማግኘት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው፤ ለአደራጆቹ ደግሞ እያንዳንዷን ኮሽታ ለመቆጣጠር ሳይረዳ አልቀረም።

## ህገወጦችን ማፈናቀል?

በአንድ በኩል ዜጎችን የማደራጀቱን ስራ አጥብቆ የያዘዉ መንግስት በሌላ በኩል ድንበር ዘለዉ ጫና የሚያቃጥሉ፣ ያለክልላቸዉ ሄደዉ የእነሱ ያልሆነን አካባቢ መንግስታዊ መዋቅር የሚቆጣጠሩ ህገወጦች ያላቸውን ዜጎች ወደ «ሃገራቸው» እንዲመለሱ ማድረጉን የጀመረው ከጠቅላይሚኒስትር መለስ ሞት ትቂት ቀደም ብሎነበር። ሚኒቹ ጠቅላይ ሚኒስትርም የእርምጃውን ትክክለኛነት ማስረዳቱን ሳያቋርጡ ነበር ለሞት የዳረጋቸው የጤና እክል የገጠማቸው። ከእሳቸው ሞት በኋላም ቢሆን ማፈናቀሉ ተጠናክሮ ቀጥሏል፤ የተቀየረ ነገር ቢኖር ለመፈናቀሉ በምክንያትነት የቀረበው ነገር ነው። በአቶ መለስ አንደበት የጥፋተኝነቱ ድርሻ ሙሉበሙሉ የተሰጠዉ ለተፈኛቃዮቹ ነበር። ዋል አደር ተብሎ ደግሞ መፈናቀሉን ያመጣው የበታች ሹማምንት ግብታዊነት ነው ተባለ።

## «ሃገሬ ክልሌ»

የማፈናቀሉ ፖሊሲ ዋነኛ ተጠቂ የሆኑት የአማራ ብሄር ተወላጆች መፈናቀል የተጀመረው እንደ ሃገራችን አቆጣጠር በ2003 በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል ልዩስሙ «ጉራፈርዳ» በተባለው ወረዳ ነበር። የአማራ ብሄር ተወላጆች ወደጉራፈርዳ ጉዞ አሀዱ የተባለዉ ከላይ እንደተጠቀሰዉ በደርግ መንግስት የሰፈራ ፕሮግራም ጉራፈርዳ ለመንደር ምስረታው ከተመረጡ ቦታዎች አንዱ በመሆኑ ነበር። ሰፋሪዎቹ ወደ ጉራፈርዳም ሆነ ወደሌሎቹ ባቢያዎች ሲጓጓዙ እንደ ግኡዝ እቃ በመኪና አጭቆ ከመላክ ባለፈ ፈቃዳቸውን እንኳን የጠየቃቸው አልነበረም። ይህ የሚያሳየው ደግሞ ሰፋሪዎቹ በሚሰፍሩባቸው ቦታዎች ለመገኘታቸው በራሳቸው ያደረጉት አንዳች አስተዋፅኦ እንዳልነበረ ነው። በኢህአዴግ መንግስት የሚወቀሱበትን የጉራፍርዳን መንግስታዊ መዋቅር የመቆጣጠር «ወንጀልም» በቦታው ረጅም ጊዜ በመኖራቸው፣ ከምንም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው ያገኙት የዜግነት መብት እንጂ ጥፋትም አልነበረም።



በርግጥ ከደርግ መውደቅ በኋላ ሃገሪቱ ዘርን ማዕከል ያደረገ ፌደራላዊ ስርአትን በመከተሏ ክልላዊነት አፅዕኖት እየተሰጠው ቢመጣም የፈተኞቹን ዋኖቻቸውን ፍለጋ ከክልላቸዉ (አማራ ክልል) ወደ ሰፋሪዎቹ የሄዱ አይጠፉም። ይሄም በህገ-መንግስቱ በተሰጠ በሃገሪቱ የትኛውም ቦታ ተዘዋውሮ የመስራት መብት የተደገፈ ህጋዊ አካሄድ ነው። በተጨማሪም በ2001 ዓም በአካባቢው አዲስ ወረዳ ሲመሰረት አካባቢውን ለማልማት የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ ወደ አካባቢው ቢመጣ ወረዳው በደስታ የሚቀበል መሆኑን በይፋ በመግለፅ ባደረገው ግብዣ መሰረት በርከት ያሉ ዜጎች ከአማራ ክልል ወደ ጉራፍረዳ አቅንተዉ፣ የአዲሱ ወረዳ አስተዳደርም ህጋዊ ቦታ እንደሰጣቸዉ ተፈናቃቹ ጠያቂ ሲያገኙ የሚገልፁት ሃቅ ነዉ። ይሄ ሁሉ ምክንያታዊነት እና ህጋዊነት ግን «ወደ ሃገራችሁ ሂዱ» ከሚለዉ ፍርደ ገምድል የሹማምንት ቀጭን ትዕዛዝ እና የመፈናቀል እንግት ሊያድናቸዉ አልቻለም።

የመፈናቀል ክስተቱ አንድ ግልፅ የሚያደርገዉ ነገር ቢኖር አንድ ሰው ሀገሩ ያለ እንዲመስለውና በሃገር ላይ ሲኖሩ የሚሰማዉ ሁለንተናዊ የመረጋጋት እና የመተማመን ስሜት እንዲሰማው እትብቱ በተቀበረበት አካባቢ ማደግ፣ መኖር እና እዛው ማርጀት አለበት ማለት ነዉ። ሀገሬ ክልሌ ማለት ይሄ ነው!

## የመሸኛው መፈክር

መፈናቀል ምን አይነት ህመም እንደሚኖረው ለማወቅ የግድ መፈናቀል ላያስፈልግ ይችላል። ቤት አልባ በበዛበት ዘመን ቤት ለመቀየር ስናስብ እንኳን እቃችንን ማጓጓዙ፣ አዲስ አካባቢን መላመዱ የሚያስከትልብንን ምቾት የሌለዉ ስሜት ማሰቡ የሚሄዱበትን እንኳን ሳያዉቁ የተፈናቀሉ ወገኖቻችን ፈተና ክብደት እንድንገምት ይረዳናል። ተፈናቃዮቹ ልጅ ውላጅ ካላቸው ደግሞ ችግሩ ይብሳል። መፈናቀሉን አስመልክቶ በ2002 በአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ (VOA) አየር ላይ በዋለ ፕሮግራም በወላጆቹ መፈናቀል ምክንያት ትምህርቱን ለማቋረጥ የተገደደ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ የሚሰማውን እንዲናገር ጋዜጠኛ እስክንድር ፍሬዉ ጋብዞት ነበር። ህፃኑ የተገኘው አዲስ አበባ በሚገኘዉ የመኢአድ ቢሮ ተጠልሎ ነበር፤ባለበት ሆኖ ግን የሚያሳስበዉ የትምህርቱ መቋረጥ እንደ ነበር የተናገረው ህፃን

ቅጥያ ያደረገው። ለበሄር ብሔረሰቦች መብት ተቆርቋሪነቱን የሚያጎላውም አማራን በትምክህተኝነት በመፈረጅ ነበር። ይሄ አይነቱ የአፍ ፕሮፖጋንዳ በተግባር መደገፉም አልቀረም። ከበደኖ እስከ አርባጉጉ ድረስ የተደረገው ጥፋት የዚህ በቅጡ ሳይታሰበበት የተለፈፈው ፕሮፖጋንዳ ውጤት ነበረ። ደግነቱ ሃገሩ ኢትዮጵያ ነውና ነገሩ እንደአጀማመሩ አልቀጠለም።

ኢህአዴግ በስልጣኑ መባቻ የተፈጠሩትን ዘርን ማዕከል ያደረጉ ግጭቶች የዘር ፖለቲካን በማጦዝ ስህተት ላይ የተመረኮዙ መሆናቸውንና ነገሩ ለራሱም ስልጣን የማይበጅ መሆኑን ዘግይቶም ቢሆን በመረዳቱ ያለፈውን ስርዐት ሲከስበት የነበረውን ኢትዮጵያዊነትን የማጉላት ስራ ተያይዞታል። ልማታዊ ነኝካለ ወዲህ ደግሞ ሁሉን ነገር ትቶ ልማት ብቻ እንዲታሰብ ይወተውት ይዟል።

## የልማታዊነት ተቃርኖ

ልማታዊነቱ አርሶ አደሩ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ እንዳደረገው የሚናገረው ኢህአዴግ ዋና ሰው አቶ መለስ በመንግስታቸው የማይስተሰረይ ሃጢያት ማለት ልማቱን የሚያደናቅፍ ስራ መስራት እደሆነ አበክረው ይናገሩ ነበር። «ልማቱ ለአንድ ደቂቃ አይደናቀፍም» ሲሉም ያክሉ ነበር። ከዚህ በተቃራኒው በደቡብ ክልል ጉራፈርዳ አካባቢ ጦም አዳሪውን መሬት ያለሙ አርሶ አደሮችን «ሞፈር ዘመት» የሚል ስም ተጨምሮላቸው ጉልበታቸውን አፍስሰው ካለሙት መሬት ላይ በሚያሳዝን ሁኔታ እንዲፈለናቀሉ ተደርጓ። ስለዚሁ ሲጠየቁም አቶ መለስ ድርጊቱ ትክክል ነው እንደማለት የሚቃጣው ሙግት ነበር በፓርላማ ያደረጉት። ልማት ልማት በሚለው አንደበታቸው ከተወለደበት ሰፈር ርቆ የሄደሰው የሚያለማው ልማት በአፍንጫችን ይውጣ እንደማለት ‹ጉራፈርዳ ጎጃምን ጎጃምን ሸተተ› አሉ እንጅ ልማቱ አልታያቸውም። ራቅ ብሎ ሄዶ ማልማት የተፈቀደው ለህንድ ኩባንያዎች ብቻ ይሆን? ወይስ አበባ እያመረቱ ለባላንታይንስ ቀን የሚያደርሱ ፈረንጅ አልሚዎች ይሆኑ ለኢህአዲግ ትርጉም ሰጭ ልማታዊያን?

አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ነገር እንደተከሰተ የሚታወቅ ነው። «ልማታዊነቱ» እስከ ካምፕዴቪድ ያስጠራው መንግስት ደሃ ገበሬዎችን ለእድገት ደፋቀና ከሚሉበት እያፈሰ በሽንጣም አውቶብስ ወደ «ሃገራቸው»



ማመላለሱን ተያያዘው። ጠያቂ ሲበዛበት ደግሞ ‹እኔ አይደለሁም መሬት መቸብቸብ የለመዱ ምንዝሮች ናቸው ቀይዋጋቸውን ያገኛሉ› ሲል ፎከረ። የጉራፈርዳወቹ ጉዳይ ‹ውሾን ያነሳ ውሻ ይሆን› ተብሎ የአእላፍ ነፍሳት ጉዳይ እንደቀላል ነገር በዝምታ የታለፈ ሲሆን የቤኒሻንጉሎቹ ጉዳይ በተሻለ ትኩረት ተሰጥቶት ቢያንስ ሰዎቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ተደርጓል፣ ጥፋቱን ያደረሱ መሬት ነጋዴ የበታች ባለስልጣናትም ይጠየቃሉ ተብሎ የነበረ ቢሆንም አንዳቸውም ምንም ሳይደረጉ ተለባብሶ ቀረ። አርሶ አደሮቹን ወደ ቀያቸው የመመለሱ ስራም ቅንነት የጎደለው፣ ከልብ ያልተያዘ፣ እንደው ጥያቄ ስለበዛ ብቻ የጨኸቱ ብርታት ለስልጣንም ጥሩ አይለም ተብሎ በሚመስል ሁኔታ የግብርይውጣ የተደረገ እንደሆነ ያስታውቃል።

## የመልስ ጉዞው ጥቅም ለማን?

ሰመጉ እንደ ሃገራችን አቆጣጠር በግንቦት 2005 ባወጣው ሪፖርት ከመፈናቀሉ ተመላሽ የሆኑ ዜጎች የባሰ እንግልት እንደጠበቃቸው ይገልፃል። ወደ ቀያቸው ተመለሱ የተባሉት ዜጎች ንብረታቸውን እንዳላገኙ፣ ገሚሶቹ መሬታቸው ጌቶቻቸውን ባሙኑ ምንዝሮች እንደተነጠቀ እንደቀረ፣ መሬታቸውን ያገኙት ደግሞ ንብረታቸው ተዘርፎ ባዶ እጃቸውን በመሆናቸው እንደ ዘር፣ ማዳበሪያ አይነት የምርት ግብአቶችን ለመግኘት እንዳልቻሉ፣ በብድር ለመውሰድ ሲጠይቁ ብሄራቸው እየተጠቀሰ አገልግሎቱ እንደማይገባቸው ተነግሯቸው እንደሚመለሱ፣ ገፋ ሲልም ድብደባ እና እስራት እንደሚደርስባቸው ቦታው ድረስ ባለሙያዎችን አሰማርቶ መረጃ ያጠናቀረው ሰመጉ በሪፖርቱ ያትታል። የደረሰባቸውን እንግልት ሁሉ በተለይ ለውጭ ሚዲያ መናገር ቅጣት ያስጨምራል ይላል ሪፖርቱ።

በተመላሽ ተፈናቃዮቹ ላይ የደረሰውን ሁሉ ላጤነ በዜጎቹ መመለስ ይበልጥ የተጠቀመው መንግስት መሆኑን መረዳት ይቻላል። ምክንያቱም በወቅቱ የዜጎቹ መፈናቀል በመንግስት ላይ ያስነሳው የተጋጋለ ጉርምርምታ ቀዝቀዝ ያለው ዜጎቹ ወደቀያቸው የመመለሳቸው ዜና ሲሰማ ነበር። የመንግስት ያለወትሮው ጥፋተኛነኝ ማለትም ይህንኑ ትርፍ ከማሰብ ይመስላል።

የግድብ ግንባታ እንቅስቃሴ የተሻለ ስራ መስራቱ የማይካድ ነው። አቶ መለስ ይሄ በተሰራበት ዘመን የሃገሪቱ መሪ በመሆናቸውም የሚወስዱት ምስጋና ይኖራል። በተጨማሪም የግብፅን እና የሱዳንን ይሁንታ ማግኘት ባይችልም የቅኝግዛት ዘመኑን ስምምነት የሚተካ በተፋሰሱ ሃገራት መሀከል ስምምነት (የኢንቴቤው ስምምነት)እንዲፈረም ያደረጉት ጥረት እውቅና ሊሰጠው የሚገባ የአቶ መለስ ሚና አለበት።

ነገር ግን አሁን አሁን በተጋነነ ሁኔታ የአባይን ነገር ከኢህአዴግ አልፎ ከአቶ መለስ ጋር የማጣበቁ ነገር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ምክንያቱም የአባይ ጉዳይ ከፖለቲካ አቋም በዘለለ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ልቦና የተቀመጠ ማህተም ነው። በሌላ በኩል የአቶ መለን ፖለቲካዊ ተክለ ሰብእና የሚያመልኩት መኖራቸውን ያህል በደግ አይን የማያዩትም አሉ። ስለዚህ የአባይን መገደብ ጉዳይ ከአቶ መለስ «ብልህ አመራር»፣ «የሀገር ተቆርቋሪነት» «ያልተደፈረውን ደፋሪ ቆራጥነት» ብቻ ጋር ማያያዝ ከታቀደው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በአባይ አጀንዳ ዙሪያ የማሰባሰብ አላማ ጋር ይጣረሳል። እንደውም ስ ፦ ብዙውን ግድብ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለሶስተኛጊዜ ስሙን ቀይሮ በሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ስም ለመጥራት ሃሳብ እንዳለ ኢቲቪ እያዳነቀ ሲወራ ነበር - ጠቅላይሚኒስትሩ በሞቱ ሰሞን።

ይሄ አካሄድ የአቶ መለስ ፖለቲካዊ ማንነት የማይዋጥላቸው ነገርግን ስለአባይ ሃገሩን ያለመጥቀም ቅንአት ያላቸውን ኢትዮጵያዊያን ለግድቡ እውንነት ድጋፋቸውን ከማድረግ እያራቃቸው ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የአቶ መለስን አስተዳደር አጥብቆ የሚያወግዘው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራ ስሜት ነው። የኢህአዴግ ባለስልጣናት ለአባይ ቦንድ ሽያጭ እና የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ ባህር በተሻሩበት ወቅት የሚያጋጥማቸው ከባድ ተቃውሞ የዚሁ የኢህአዴግ የተሳሳተ አካሄድ ውጤት ነው። የኢህአዴግን በቀል በመፍራት እንደ ውጭ ሃገሩ ግልፅ አይውጣ እንጅ አስተሳሰቡ በሃገርቤት ነዋሪውን ዜጋ ዘንድም ይስተዋላል።



## የድንገቴው አባይን «መድፈር»

ትክክለኛ የህዝብ መንግስት ባለበት ሃገር ትልልቅ ሃገራዊ አጀንዳዎች በመንግስት ብቻ ታስበው ለህዝብ በመጨረሻው ሰአት ይፋ አይደረጉም። በምትኩ ከጥንስሱ ጀምሮ ህዝብ ተወያይቶበት የባለቤትነቱን ድርሻም እንዲወስድ ይደረጋል። ከዚህ በተቃራኒው የአቶ መለስ አስተዳደር ባለፈው አመት በድንገት ዱብ ያደረገው አባይን የመገደብ እቅድ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ቀርቶ ከአቶ መለስ በታች ያሉ ዋና ባለስልጣናት እንኳን የመከሩበት ጉዳይ አይመስልም። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው ደግሞ አቶ መለስ በሞቱ ማግስት ባለስልጣናቱ ሟቹን አለቃቸውን ከፍ ያደረጉ መስሏቸው የግድቡ እቅድ ጥንስስም ውልደትም በብቸኝነት የአቶ መለስ ብሩህ አእምሮ ውጤት እንደሆነ የተናገሩት የራሳቸው ቃል ነው።

አባይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ነገር ነው። አፈር ጠርጎ የሚወስድ ወንዝ ብቻ አይደለም። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ለዘመናት በአባይ ባለመጠቀሙ የመበለጥ እና የመጠቃት ስነልቦና አለበት። ስለዚህ የአባይ ጉዳይ ለእኛ የኢኮኖሚ እና የጂኦ-ፖለቲካ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የስነልናም ጉዳይ ነው። ለዛም ነው አባይ ሊገደብ ነው ሲባል የሃገራችን ህዝብ በወል የተደሰተው። ለምን ለሃይል ማመንጫ ብቻ መስኖ የማናለማበት ማንን ፈርተን ነው ብሎ አጥብቆ ያልጠየቀው። የፈት የፈቱን ብሎ ምንም ዋጋ ያስከፍል፣ ማንም ይገድበው፣ ብቻ አባይ ይገደብ እና የዘመናት የመበለጥ ጥቃታችን ያብቃ ያለው፤ የወር ደሞዝህን ሲባል ሳይተርፈው ያበደረው የአባይ ነገር በኢትዮጵያዊያን ዘንድ ከፖለቲካዊ አቋም፣ ዘር ቋንቋ፣ ሃይማኖት... አለፍ ያለ ቦታ ስላለው ነው።

እንደዚህ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ የሆነውን እና በታችኛው ተፋሰስ ሃገራት እንደ አንድ አይን የሚታየውን አባይን ለመደብ ሲታሰብ ታዲያ እንዲህ በድንገት መሆን አልነበረበትም። ሃገር ከጥግ እስከ ጥግ መነጋገር ነበረበት። ያሉትን ተግዳሮቶች አሁን አፍጥጠው ሲመጡ ሳይሆን ቀደም ተብሎ ከሰፊው ህዝብ ጋር ውይይት ቢደረግ የተሻለ የህዝብ ባለቤነትን ማምጣት ይቻል ነበር። ትርፍ ኪሳራው፣ የገንዘብ ምንጩ፣ ውስብስብ የዲፕሎማሲያዊ እንቆቅልሹም መውጠንጠን መወሰን የነበረበት «በባለ ራዕዩ መሪ« የአእምሮ ጓዳ ብቻ መሆን አልነበረበትም። እንደው አቶ መለስ ሁሉን አዋቂ «አውቅ ጢቅ« ተደርገው ቢታሰቡ እንኳን ምሁራንን ማማከሩ፣ ህዝብን በጉዳዩ ላይ

በተመለከተ በግብፅ የሚመጡ መንግስታት ሁሉ አቋማቸው ተመሳሳይ ነው ብዬ ስለማስብ ነው:: ስለዚህ ነገሩ ቀደም ብሎ ቢጀመርም የኡስኒ ሙባረክ አስተዳደር ሊል የሚችለው ነገር የሙርሲም ሆነ የተከታዮቻቸው አልሲሲ መንግስት ከሚለው እምብዛም የሚለይ አይሆንም ነበር ብዬ እገምታለሁ:: የነገሩ መሃንዲስ የተባሉት አቶ መለስ የኡስኒ ሙባረክ መንግስት ወንበር የተነቃነቀበትን የግብፅን ክፉ ቀን ጠብቀው ወንዙን ለመገደብ መነሳታቸው ከኡስኒ ሙባረክ አስተዳደር ይገጥማቸው የነበረውን የወዲያው እሰጣገባ እንዲያመልጡ መርዳቱ አልቀረም::

ይሄ ማለት ግን የግብፅ ክፉ ቀን አያልፍም ማለት አይደለምና የአቶ መለስ አባይን ለመገደብ የመረጡት ቀን እና አጋጣሚ ከግብፅ ጋር የሚኖረውን እሰጣገባ ያዘገየው ይሆናል እንጂ አያስቀረውም:: አሁን በተግባር እየታየ ያለው የግብፅ ሁኔታ ይህን የሚያጠናክር ነው:: ግድቡ እንደተጀመረ ሰሞን ምንም የተቃውሞ ድምፅ ሳታሰማ የቆየችው እና አሁን ጦር ለመምዘዝ የምትገለገለው ግብፅ እያደረገች ያለው ነገር ይህን የነገር መዘግየት መቅረት እንዳልሆነ የሚያስመሰክር ነው::

ዞርዞሮ እሰጣገባው ማይቀር ከሆነ ደግሞ ኢትዮጵያ የአረብ ስፕሪንግ ያመጣውን ግርግር ሳትጠብቅ ጉዳዩን ቀደም ብላ ብነታሳ ኖሮ ተገቢውን ዲፕሎማሲያዊ ስራም ለመሞከር ያስችላት ነበር:: ይሄ ደግሞ ከምንም በላይ ለግድቡ መስሪያ የሚያግዝ ገንዘብ ለማፈላለግም ይመች ነበር:: በዚህ እሳቤ ውስጥ ግን የአቶ መለስ መንግስት አባይን ለመገደብ ሲነሳሳ በሃገር ውስጥ ፖለቲካ ሊኖረው የሚችለውን ፍላጎት ሳይጨምር ነው:: በግድቡ ስም ሊገኝ የታሰበውን የውስጥ ፖለቲካዊ ትርፍ ግምት ውስጥ ካስገባን አባይን ለመገደብ የተመመረጠው ሰአት ተገቢ ሊሆን ይችላል::

## አባይን ለመጠቀም ግብፅን ማስፈቀድ አለብን?

ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን ለግድብም ሆነ ለመስኖ ለመጠቀም ሚያደረገው እንቅስቃሴ ሃገር ውስጥ ሰርገው የሚቀሩ ወንዞችን ከመጠቀም በላይ ዲፕሎማሲያዊ ውስብስብ ጉዳዮችን ማለፍን ግድ ይላል:: ምክንያቱም ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ድንበር ሲሻገሩ የሚመነጩበት ሃገር ብቻ ንብረት መሆናቸው ያበቃና የተፋሰስ ሃገራቱ ሁሉ ባለመብትነት ይመጣል:: አባይም



ብዙ ተፋሰሶች ያሉት ሸንጠ-ረዥም ወንዝ ነውና ሃገራችን ምንም እንኳን የወንዙ መፍለቂያ፣ ሰማኒያ ፐርሰንቱን የወንዙን ውሃ የምታበረክት ብትሆንም የተፋሰሱን ሃገራት ጥቅም ሳታማክል ወንዙን እንደልቧ የመጠቀም መብት የላትም:: በስራ ላይ ያሉት የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ህጎችም የተፋሰስ ሃገራቱን እኩል ተጠቃሚነት በሚያበረክቱት የውሃመጠን እና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ እንደሚሆን ይደነግጋል:: በተጨማሪም ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን በተፋሰስ ሃገራቱ ለመጠቀም ሲያስቡ በትኩረት መታየት ያለበት የሌሎችን ሃገራት ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ ነው:: እዚህ ላይ ለሃገራችን በአባይ ላይ ተጠቃሚ የመሆን መብት አረንጓዴ መብራት የሚሆነው በምታበረክተው የውሃመጠን እኩል ተጠቃሚነትን የሚፈቅደው ህጋዊ መሰረት ነው:: በተጨማሪም የታችኞቹን ተፋሰስ ሃገራት ጥቅም ባለመጉዳቱ በኩልም ሃገራችን ያደረገችውን ጥንቃቄ ሱዳን ራሷ የመሰከረችው ነውና በዚህ ላይም ህገ-ወጥነገር አልተሰራም - በኢትዮጵያበኩል::

በሌላ በኩል ግብፅ ይህን ትርጉም ሰጭ ወቅታዊነት ያለው እና የሁሉንም ተፋሰስ ሃገራት ፍላት የሚያሟላ ኅብረሃሳብ ወደጎን በማድረግ ያስፈበትን የቅኝ-ግዛት ህግ ሙሉ በሙሉ የራሷን ፍላጎት የሚያስጠብቅ ስለሆነብቻ ዘላላማዊ ማድረግ ትፈልጋለች:: ለተግባራዊነቱም ሱዳንን ከጎኗ አድርጋ ተገቢ ያልሆነውን ተቀባይ ለማድረግ ስትደክም ኖራለች::

ይሄ አካሄድ ግን የህዝብ ብዛታቸው እየጨመረ በሚሄድ ቁጥር የበለጠ አባይን የመጠቀም ፍላጎት እያሳዩ በመጡት የላይኛው ተፋሰስ ሃገራት ዘንድ ተቀባይነት እያጣ ነው:: በተጨማሪም ሞቶ ርቆ በተቀበረው የቀኝ አገዛዝ ስርአት የተደነገገን ህግ በነፃነት እና እኩልነት ዘመን እየመዘዙ እንደ ትክክለኛ መከራከሪያ ማቅረብ አውቆ የመተኛት ራስ ወዳድነት ስለሆነ ተቀባይነት አይኖረውም:: ይህን በመገንዘብ በተለይ በኢትዮጵያ ግንባርቀደም አስተባባሪነት የተመሰረተው የተፋሰሱ ሃገራ የምክክር መድረክ እና እሱን ተከትሎ የመጣው የኢንቴቤ ስምምነት ይበል የሚያሰኝ እና ግብፅን ከነአፈጀ የራስወዳድ አቋሟ ለብቻ የሚያስቀር እርምጃ ነው::

## መሻሻል እና መብራራት ያለባቸው/የነበረባቸው ጉዳዮች

ኢህአዴግ ዘግይቶም ቢሆን የጀመረውን ግድብ ስኬታማ ለማድረግ አሁን እየሄደባቸው ያሉትን አንዳንድ ተሳሳቱ አካሄዶች ማስተካከል አለበት። በመጀመሪያ ደረጃ አባይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ጉዳይ በመሆኑ የኢህአዴግ ባለስልጣናት እና ደጋፊዎች ራሳቸውን የአባይነገር እንቅልፍ የሚያሳጣቸው በሉና ያሉ ተቆርቋሪዎች አድርገው በጉዳዩ ላይ የተለየ አቋም ያሳየን ዜጋ ሁሉ የሃገር ጠላት አድርጎ ፕሮፖጋንዳ መስራቱ ቢቀር ጥሩ ይሆናል። ምክንያቱም የኢህአዴግ አካሄድ ብቸኛው ትክክለኛ መንገድ ሊሆን ስለማይችል ከኢህአዴግ ሃሳብ ጋር መለያየት ማለት የአባይን መገደብ መቃወም፣ የግብፅ ተላኪ መሆን ማለት አይደለም።

ከዚህ ስህተት ለመዳን የኢህአዴግ ተቃዋሚም ሆነ ደጋፊ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ የአባይን መገደብ እንደማይጠላ ማመን አለበት። ስለሆነም ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በአባይ ጉዳይ ላይ ከማግለል እና ከማጥላላት ቀርበው መልካም ነው ያሉትን አሳብ እንዲሰነዝሩ ቢደረግ አባይን የኢትዮጵያዊያን ሁሉ የጋራ ጉዳይ አድርጎ ኢህአዴግንም ሃምሳ ሎሚን ብቻውን ከመሸከም ያድነዋል። ምሁራንም እንደየ መስካቸው ስለግድቡ ለህዝቡ ማብራሪያ እንዲሰጡ ከባለስልጣናት የእንገነባዋለን የንግግር ስልትላይ ተቀንሶ ቢሰጣቸው መልካም ነው። የውሃና የግንባታ መሀንዲሶች፣ የከርሰምድር ባለሙያዎች (ጅኦሎጅስቶች)፣ የህግ ባለሙያዎች፣ የፖለቲካ እና ዲፕሎማሲ ምሁራን ወዘተ በጉዳዩ ላይ ከፕሮፖጋንዳ በተለየ ሁኔታ ያለውን ስጋት እና አስቻይ ሁኔታ ለህዝብ ያስረዱ ዘንድ መድረኮች በከፊት አለባቸው።

ስለ አባይ ጉዳይ ያሉ እውነታዎችንም መንግስት በጊዜ ለህዝቡ ይፋ ማድረግ አለበት። ህዝብ የሚፈለገው መዋጮ ለመሰብሰብ ብቻ መሆን የለበትም። መዋጮውን ለመሰብሰብም ቢሆን በቅድሚያ በህዝብ ዘንድ የባለቤትነት መንፈስ መፈጠር አለበት። ለዚህ ደግሞ ከመንግስት ዘንድ ከአሁኑ በጣም የተሻለ ግልፅነት መምጣት አለበት። ኢህአዴግ ግን አንዳች ነገሮችን ሁሉ ሚስጥር የማድረግ አባዜ አለበትና ይሄን እያደረገ አይደለም። የግብፅ ባለስልጣናት በሀገራቸው ላይ ቡራከረዩ ሲሉ ከነበረበት ድንገት ተነስተው ከኢትጵያው አቻቸው ጋር ለመወያየት መጥተው ሲሄዱ ምን የተለየ ነገር እንደ ተፈጠረ አይነገርም። ኢቲቪም እንደ ተለመደው ገበስ ገበሱን ነው የሚያወራው።



የህዝቡን ሙሉ አመኔታ ለማግኘት ግድቡን እየሰሩ ያሉት ሃገር በቀልና የባህር ማዶ ኩባንያዎች ለስራው የተመረጡበትን መስፈርት በተመለከተ በህዝብ ዘንድ ያለውን ግርታ የሚያጠራ ማብራሪያ መስጠት ከመንግስት ይጠበቅ ነበር። ለምሳሌ በግልገል ጊቤ ሁለት የሃይል ማመንጫ ግድብ ስራ ውጤታማ ያልነበረው የጣሊያኑ ሳሊኒ ኩባንያ ያለውም ያለጫረታ የአባይን ድልድይ እንዲሰራ የተደረገበት ምክንያት ግልፅ መደረግ የነበረበት ሌላ ነጥብ ነው። የብረት ማቅለጡ ሚና የተሰጠው መከላከለያ ኢንጅነሪንግ፣ ሲሚንቶ የማቅረቡን ሃላፊነት የወሰደው የኢፈርቱ መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ እና እህት ኩባንያው መስፍን ኢንጅነሪንግም አቅማቸው የግድቡን ቃላቅነት የሚመጥን መሆኑ እና ከማን ጋር ተወዳድሮ እንደተመረጠ ማወቅ ይፈልግ ነበር ደሞዙን የሚገብረው ህዝብ።

ዲፕሎማሲውን በተመለከተም በባድመ ጉዳይ የታየው አይነት ጥፋት እንዳይደገም ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ከመጀመሪያው የግድቡ ስራ ውሳኔ ይፋ ሲደረግ ግብፅ ምንም አይነት ተቃውሞ እንዳላነሳች፣ እንደውም ሃገራችን በአባይወንዝ የመጠቀም መብቷን እንደተቀበለች ሲነገረን ከነበረው በተቃራኒ ግብፅ ስንበት ብሎ ደግሞ ሃገራችንን እስከመውጋት ልትሄድ እንደምትችል ስትዶልት የነበረበትን ፊልም በአይናችን አይተናል። በዛው ሰሞን የታችኛው ተፋሰስ ሃገራትን አቋም የመደገፍ ዝንባሌ አሳየች የተባለቸው ሱዳን ቢያንስ የኢንቴቤውን ስምምነት እስካልፈረመች ድረስ በአቋሟ ፅናት እርገጠኛ መሆን አይቻልምና የሱዳን አቋም ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ መጣራት አለበት እንጅ ቶሎ እምነት ተጥሎበት ማዘናጋትን እንዳያመጣ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

ግብፅን በተመለከተም «ነላበደች በስተቀር ጦርነት አታነሳም« ከማለት ባለፈ ጦርነት የማታነሳበትን ምክንያት ከስሜታዊነት በተላቀቀ ሁኔታ በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ ማብራሪያ መስጠት ከመንግስት ይጠበቃል። ግብፅ የጉንደት እና ጉራ ሽንፈቷን እያስታወሰች እስከዛሬ ስለምትፈራን ጦርነት አታስብም የሚለው የባለስልጣኖቻችን ክርክር እንኳን አድማጭ ሊቀበለው ራሳቸውም አምነውበት የሚሉት ነገር አይመስልም። ይልቅስ ወቅታዊ ሁኔታዎችን እየጠቀሱ እነሾ እርግጠኛ የሆኑበትን የግብፅን ወደጦርነት ያለመግባት ምክንያት ለህዝብ በሚያሳምን መልኩ ማስረዳት አለባቸው።

በተጀመረበት ሰሞን ታሳየው ነበረው ከዝምታ እስከ የይሁንታ አዝማሚያ ጊዜ ለመግዛት ታደርገው የነበረ ስልት መሆኑን ቆየት ብላ ደግሞ የምታሰማው ዛቻ ምስክር ነው:: ከዚህ መለስ ብላ ደግሞ አዲስ አበባ ድረስ ገስግሳ መጥታ እንስማማ፣ እንነጋገር፣ ወንድማማች ህዝቦች ነን እያለች ስትለን ነበር:: ቀጥሎ ደግሞ ምን ትል ይሆን የሚለው ነገር ለኢትዮጵያ የማያሳስብ አይደለም::

አባይ ጉዳይ ውስበስብ እና ላቅ ያለ የዲፕማሲ ጥበብን የሚጠይቅ ነው:: የዲፕሎማሲው ነገር ዋናው ሰው አቶ መለስ በህይወት እያሉ እንኳን ብዙ የማይሰምርለት የኢህአዴግ መንግስት ይህንን ውስብስብ የዲፕሎማሲ ስራ በልቅና መወጣት ይችል ይሆን የሚለው ጉዳይም ያሰጋል:: ስጋቱን የሚያብሰው ደግሞ መንግስት በጉዳዩ ላይ የምሁራንን እገዛ ሲጠይቅ አለመታየቱ ነው::

ከላይ የተቃቀሱትን ሳንካዎች አልፎ ግድቡ እውን ቢሆን እንኳን በደለል የመሞላቱ ስጋት እና ደለሉን ለማዕዳት ሃገራችን የሚጠበቅባት ገፋ ያለ ወጭም ሌላ እራስምታት ነው::

## 6.5 የቆሞ ቀርነት ፖለቲካ!

በፊውዳሊዝም ፖለቲካዊ ዘይቤ የኖረው የሃገራችን ዘውዳዊ መንግስት የእድሜውን ርዝመት ያህል ሃገሪቱን ውጥንቅጥ ውስጥ ከቶ የኖረ ነው:: ከዚህ ዘመን ውስጥ ደግሞ «ዘመነ መሳፍንት» ተብሎ የሚጠራው ከ 1769-1855 የቆየው ዘመን የሃገሪቱን ህልውና ፈተና ውስጥ ከቶ የነበረ የጦርነት እና የእልቂት ዘመን ነበር:: የዘውዳዊ አገዛዙ ዘመን መደጠሪያው ፊውዳሊዝም፣ ነገስታቱም ከቤተ-ክህነት ያልዘለለ ግንዛቤ የነበራቸው እንደመሆኑ በዘመኑ ስለጠፋው ጥፋት በዚህ ዘመን የንቃት ደረጃላይ ሆኖ መሪዎቹን ከመውቀስ ይልቅ በነበራቸው ውሱን ግንዛቤ ለሃገራቸው ላበረከቱት አስተዋፅኦ እውቅና መስጠቱ ተሻይ ይመስለኛል:: በተለይ የነገስታቱ የሃገር ፍቅር ከዙፋን አውርዶ እንደተራ ወታደር እስከመዋጋት የሚያደርስ ነበርና መወደስ አይበዛበትም::

በአንፃሩ በዛሬ የንቃት ደረጃ ሲፈተሽ ጥፋት የሚባሉ በርካታ እንከኖች እንደነበሩባቸው የማይካድ ሃቅ ነው:: ይህ የሚያግባባውም ትናንትን በዛሬ ሚዛን መመዘኑ ትክክል ነው ተብሎ ከታሰበ ነው:: ያም ሆነ ይህ ‹በሞተ ስርዓት ላይ ከዚህ በላይ ጊዜ ማጥፋት አይገባም› እንዲሉ ፕሮፌሰር መስፍን



ነገስታቱን እነሱ ካለፉ ከስንት አመት በኋላ ወደ ጠረጴዛ የመጣውን የሰብአዊ መብት አከባበር ፍልስፍና እያነሱ እሱን በመተላለፍ ማብጠልጠል እልፍ ማይል ወደ ኋላ ተጉዞ ቆሞ መቅረት ይመስለኛል:: በዘመነ ኢህአዴግ ብቅ የሚሉ ጦማሪያን ደግሞ እጃቸውን የሚያፍታቱት፣ ፖለቲከኞች ህዝባዊ ድጋፍ ለማግኘት የሚሞክሩት እነዚህን ነገስታት በማብጠልጠል ሆኗል:: ነገሩ በአመዛኙ ከኢህአዴግ ወደ ስልጣን መምጣት ጋር ሃገሪቱን ከወረሳት የዘረኝነት አባዜ የሚነሳ ነው:: ለዚህ ማመሳከሪያው የእነዚህ ጦማሪን ትችት ፍላፃ የሚወረወረው ከነሱ ብሄር ባልሆኑ ነገስታት ላይ ሲሆን ›ከእኛወገን› የሚሏቸውን ነገስታት ደግሞ በፊውዳላዊ ስርአት ውስጥ ዲሞክራት፣ ብሁዕ እና ነብር በጥራ የሚገድሉ ጀግኖች ለማድረግ መፋተራቸው ነው:: ነገሩ ባስ ሲል ደግሞ የእኛ ሰፈሩ ባላምባራስ እንትና ከእንትን ምንጭ ማዞሪያ መለስ የተመለመሉ ወታደሮችን ብቻ ይዘው ጣልያንን ስላርበደበዱ የተራራማውን እና ቆላማውን ምድር ህዝብ ይዘው ካሸነፉት አፄ እንትና አንሰው ምክትል ጀግና መደረግ የለባቸውም እየተባለ ቁም ነገር እንደያዘ ሰው በምሬት ክርክር ይገጠማል:: የሰብአዊ መብት ጉዳይ ባልተነሳበት፣ የሰው ልጅን ገበያ አውጥቶ መሸጥ ሽምብራ እንደመሸጥ ነውር በሌለው ዘመን አፄ እንትና ባሪያ እንዲሸጥ ፈቅዶ ነበርና የነፃነት አባት ሳይሆን ሃገር ከሃዲ ነው የሚል ክርክር በዚችው መዕሄት ላይ ያነበብነው «ትንታኔ» ነው:: ለሃገራቸው ክብር ሲሉ ከሃገር ዳርቻ በእግር በፈረስ ተጉዘው በጣምራ ክንዳቸው ጠላትን ድል የመቱ ወንድማማቾችን ለመነጣጠል «አንኮበራዊ» እና «አክሱማዊ» አርበኞች የሚል ስራ-ፈት ሽንሽናም እንደ ደህና ነገር እየተወሳ መጥቷል:: ለአንባቢ ቁምነገር እንደሚያቀብል ሰው ብዕር አንስተው እንደ እየሩሳሌም ቆነጃጅት ‹አክሱማዊያን እልፍ ገደሉ አንኮበሮች ግን ሺ ብቻ› እያሉ ለሰፈራቸው ሰዎች ለመዝፈንም ይሞክራቸዋል:: ይህ ሲባል የተረሳው ጉዳይ ‹አንኮበራዊውም› ሆነ ‹አክሱማዊው› ገኘር ያደረገውን ያደረገው ግዛቱን አስፋፍቶ ከተገኘሮዎቹ የሚሰበስበውን አመታዊ ግብር መጠን ለማሳደግ እንጂ ‹ከአንኮበራዊ› እና ‹ከአክሱማዊ› ማን ይጀግናል ለሚለው መልስ የሚሆን ነጥብ አስመዝግበው አልፈው፣ እኛ የልጅ ልጆቻቸው ደግሞ እንድንተነትነው አልነበረም::

የቆሞ ቀር ፖለቲከኝነት አባዜዎችን የሃገር ድንበር ከቀይ ባህር ማዶ ይሆን ዘንድ የተዋደቁ እንደ አሉላ አባነጋ አይነት ሃገር ወዳዶችን አስበውት በማያውቁት መልኩ የገድላቸውን አኩሪነት እና የጀግኖቹን ወገንተኝነት በተወለዱበት መንደር ብቻ ተወስኖ የሚቀር አስመስሎ ከማሰብ አልፎ

እስከ መፃፍ ይደርሳል። ይህ እንግዲህ ቅሞቀርነት ብቻ ሳይሆን በአስፈሪ ሁኔታ እየተዋሃደን ያለው የዘረኝነት እና የመለያየት አባዜያችን ያመጣው ልክፍት ነው። ከዚህ በተዋጀ ሁኔታ ከታሰበ ግን አሉላም የሁላችንም ጀግና ናቸው፣ ዶግአሊም ሆነ አድዋ የኢትዮጵያዊ ሁሉ ድል ነው፤አሉላ ቀርቶ ዘርአይደረስም ስለኢትዮጵያ የተጋደሉ የኢትዮጵያዊ ሁሉ ጀግና ናቸው።

ከዚህ ባፈነገጠ መልኩ አሉላን የትግራዊያን ብቻ የጀግንነት ምልክት አድገው ሊያቀርቡ ለሚሞክሩ ተከራካሪዎች መቅረብ ያለባቸው ወሳኝ ጥቄዎች አሉ። እነዚህ የወንዝ ልጅ ነን ባዮች በጀግናው አሉላ አባነጋ ስም ተሰይሞ የነበረው ትምህርትቤት በመለስ ዜናዊ ስም ሲቀየር ምነው ይህ ተቆርቋሪነታቸው ለመለስ ሌላ ትምህርት ቤት ይሰራ እንጂ የመለስን ስም ለመስቀል የራስ አሉላ ስም መውረድ የለበትም ለማለት አላስቻላቸውም? ወይስ የአንድ ትግራዊ ስም በሌላ ትግራዊ ስም መተካቱ ችግር የለውም? እርግጥ በዘረኝነት አዙሪት ለተተበተበ ሰው ይህ ያሳምን ይሆናል ተገቢ ነው ማለት ግን አይደለም። ከወንድሞቻቸው ጋር ሲጋደሉ ለሞቱ የህወሃት ሰማዕታት ስንት ነዋይ የፈሰሰበት ሃውልት ሲሰራ የራስ አሉላ አፅም ያረፈበት ቦታ ይህ ነው የሚባል ምልክት የሌለው መሆኑ፣ ይህ ሳያንስ ምዕዋ ላይ ደርግ ያሰራው ሃውልታቸው ሲፈርስ ከአንኮበራዊያን ጋር ለማወዳደር ሲሆን የሚፈጥኑ የወንዝ ልጅ ነን ባዮች ተቆርቋሪነታቸው ምንም ያላናገራቸው ለምን ይሆን? እዚህ ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ድምፃቸውን ማሰማት ያለባቸው ከትግራይ የሆኑ ወገኖች ብቻ ናቸው ለማለት አይደለም። ምክንቱም እንደ አፄ ምኒሊክ፣ አሉላአባነጋ፣ አብዲሳ አጋ፣ ሙሉጌታ ቡሊ (በስማቸው ይጠራ የነበረው የሆለታው የጦር ትምህርት ቤት አሁን በሃየሎም አርአያ ስም ተቀይሯል)፣ በላይ ዘለቀ አይነት የሃገር ባለውለታዎች ስም ተገቢውን ክብር ማግኘት ያለማግኘት ጉዳይ ሁላችንንም የሚመለከት ነው። ለዚህ ወደ ሰዎቹ የትውል መንደር መሮጥ አያስፈልግም፤ቢያንስ ነጭ ወራሪን አንበርክከው ጥቁር አፍሪካዊ ወገኖቻችን ያላገኙትን ክብር በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ለተፈጠርን ሁሉ አጎናፅፈውናልና።

በትግራዊነት እና አንኮበራዊነት ላይ በሚያጠነጥን ስንዘሮ ትንታኔ ፍቅር የወደቁ ተንታኞች ሊላው መለያ የፈለቁበትን ትግራዊነት ለማወደስ እና አንኮበራዊነት ብለው የሰየሙትን አካል ለማንኳሰስ ከአፄምኒልክ ዘመን እስፍ ማለት አለመቻላቸው ነው። በእነሱ መንገድ ተጉዘን በሚገባቸው ቋንቋ



እንነጋገር ከተባለ ወደ ዘመነ መሳፍንት መንዝ ግድ ይላል። ወደዛ ከተኬደ ደግሞ በዘመኑ አሻንጉሊት መንግስታትን እየሾሙ፣ የሃገሪቱን ህልውና ማጥ ውስጥ የከተተ የረዥም ዘመን መተላለቅን ያመጡ፣ በሃገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የማዕከላዊ መንግስትን አቅም ያደቀቀ የአካባቢ አለቆች ጉልበት መፈርጠምን እየኮተኮቱ ያሳደጉ የነበሩት ሚካኤል ስሁል ትግራዊ ናቸውና የአፄ ምኒልክ ስም የሚገረፍበት የቆሞቀርነት ብዕር ለበቅ በዚህ ሰው ላይም ሊወርድ ነው። ከዛ እልፍ እንበል ከተባለ ደግሞ የእንግሊዝን ጦር እየመሩ ወንድማቸውን አፄ ቴወድሮስን ያስገደሉት ትግራዊው አፄ ዮሃንስ የመሆናቸው እውነት አፍጥጦ ይመጣል። ይህን ብለን ሳንጨርስ ደግሞ አፄ ዮሃንስ ከዙፋን ወርደው እንደ ተራ ወታደር ስለሃገራቸው ሊፋለሙ መተማ መገኘታቸውን፣ በዛውም ውድ ህይወታቸውን ማጣታቸውን ታሪክ ያስረዳናል። ይህን በሰማንበት ጆሮ ደግሞ የመቀሌው ራስ ሃይለስላሴ ጉግሳን የባንዳነት ታሪክ ማድመጣችን አይቀርም። ይህ መሰሉ የታሪክ ሽርጉርጉር የሚያስረዳው ሰዎች በወለዱበት መንደር ምክንያት ጀግናም ሆነ ባንዳ ሊሆኑ እንደማይችሉ ነው። ይህን የሚወስነው ከትውልድ መንደር፣ ከቋንቋ፣ ዘር ውጭ የሆኑ ብዙ ምክንያቶች ነው። ይልቅ የታሪክን ግራ ቀኝ ሳናስተውል ልክ ነው ባሉት መንገድ በፍፁም ልባቸው ለሃገራቸው ነፃነት በተዋደቁ ዋኖቻችን ላይ ዘረኝነታችንን በብዕራችን ግንፍላት ለመግለፅ ስንንደረደር የምናስተው ብዙ ይሆናል። ይህ ማለት ቀደምቶቻችን ምንም ስህተት አልሰሩም ማለት አይደለም። ይልቅስ ወደኋላ መለስ ብለን የዋኖቻችንን ስራ ስንገመግም በሚዛናዊ ጭንቅላት፣ ከዘረኝነት በተዋጀ ጨዋ ብዕር፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለትንታኔ የሚበቃ የእውቀት ስንቅ ይዘን መሆን አለበት ለማለት ነው።

በአፄ ምኒልክ ዘመን ቆሞ የመቅረቱ ነገር የኦሮሞ ህዝብን ከኢትዮጵያ እንገነጥላለን ይሄ እንዳይሆን ከተፈለገ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ የተመለሰባት ኢትዮጵያ መመስረት አለባት (ጥያቄ የሌለው ኢትዮጵያዊ ይኖር ይሆን?) በሚሉ የኦሮሞ ብሄርተኛ ልሂቃን ዘንድም ይስተዋላል። እነዚህኞቹ ከሚኒልክ ዘመን በፊት የህዝብ ቁጥር ማሻቀብ በፈጠረው የእርሻ እና ግጦሽ መሬት መሰል የተፈጥሮ ሃብቶች እጥረት ወደ ሰሜን ራያ ድረስ የራቀ ጉዞ አደርገው እንደ ነበረ፣ ይህ ጉዞዋቸው ደግሞ የወይራ ዝንጣፊ የያዙች እርግብ የምትመራው፣ አንድም ሰው ሳይሞት የተደረገ መስፋፋት እንዳልሆነ ቢያውቁትም ደግመው ማሰብ አይፈልጉም። ለምን ቢባል ይህን ማመን የአፄ ሚኒልክን የተስፋፊነት እንቅስቃሴ አሁን በሚራገበው መጠን

ለማራገብ አቅም ያሳጣል። ነገሩ በመስፋፋት ውስጥ ያለው ደም መፋሰስም የኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አምሮቶች ያመጡት በማንኛውም ተስፋፊ ሊከናወን የሚችል ሁነት እንጂ ሰውን በዘሩ ማጥቃትን ኢላማ ያደረገ ክስተት አለመሆኑን ያረጋግጣል። ይህ መሰሉ የመስፋፋት ግስጋሴ ደግሞ የምርጫ ሳጥን ተደፍ የነባሮቹ ህዝቦች ፈቃደኝነት እየተጠየቀ የማይሆን እንደሆነ ወደ መካከለኛ ዘመን የሃገራችን ታሪክ ተጉዞ፣ በአፍሪካ ደረጃ እንኳን በታሪክ መጠነሰፊ መስፋፋት ነበር የሚባልልትን የኦሮሞ ህዝብ የመስፋፊት ታሪክ በወጉ ማጤን ያስፈልጋል። ይህ ግን ዘረኝነትን የተከናነበ ቆሞቀር ፖለቲካዊ ትንታኔን ሰምቶ ስሜቱ እንደገፋው የሚከተለውን ጀሌ ቁጥር ይቀንሳልና በዘር ፖለቲካ አቀንቃኞች ዘንድ አይፈለግም። በመሆኑም የኦሮሞ ህዝብን እና ማዕከላዊውን መንግስት ግንኙነት ፖለቲካዊ ታሪክ በአፄ ምኒልክ የስልጣን ዘመን ጀምሮ የመጣ ነው በማለት እዛው ላይ ቆሞ መቅረቱ በብሄሩ ልሂቃን ዘንድ በብዛት ይስተዋላል። ይህ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሰውን በአፍሪካ ደረጃ ሳይቀር በስፋቱ እና በወሰደው ጊዜ ርስዝማኔ በታላቅነቱ የሚታወቀውን የኦሮሞ ህዝብ ወደ ሰሜን መስፋፋት አውቆ የረሳ፣ በጎንደሪያን ነገስታት ቤተመንግስት የኦሮምኛ ቋንቋ መግባቢያ እስከመሆን ደርሶ የነበረበትን ሃቅ የካደ ክርክር ነው። ታሪክን በዚህ መልኩ በሚፈልጉት መንገድ መተንተኑ በህዝብ ነፃነት ስም መከረኛ ስልጣን ላይ ቂብ ብሎ ተረኛ አምባገነን ለመሆን ነው። በእውነት ለህዝብ ነፃነት ነው ከተባለ ደግሞ ትግሉ ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ታሪክ ሳይጣመም በአሳማኝ መንገድ መቅረብ አለበት።

ከላይ በተወሳው መልክ በምኒልክ ዘመን ላይ ቆመው የሚቀሩ የኦሮሞ ብሄር ፖለቲካ ልሂቃን ከዚህ አለፍ የማለት ነገር በሚታይባቸው ሁኔታዎች ደግሞ ቀደም ሲል ቆመው የኖሩበትን ክርክር በሚጠናክር ሌላ ሁነት ላይ እመር ብሎ እዛ ላይም የጨው አምድ የመሆን ነገር ይታያል። ይህ ዘመን ደግሞ ወደ ኃ/ስላሴ ዘመን ያመራል። ይህኛው ክርክር በኃ/ስላሴ ዘመን በመንግስት ደረጃ በተያዘ እቅድ የኦሮሞ ህዝብ ከአንደኛ ደረጃ በላይ እንዳይማር መደረጉን፣ ይህም በወቅቱ ከስርዓቱ ማገር አንዱ የነበሩት ጀነራል ታደሰ ብሩ ኦሮሞ መሆናቸው ሳይታወቅ እንደተነገራቸው የሚያወሳው ክርክር ነው። ይህ አሳፋሪ እና መሆን ያልነበረበት ነገር ነው። ይህ ነገር እንደ በደል ለኦሮሞ ብሄርተኛ ልሂቃን የነፃነት ትግል ግብአት መሆኑም ከበቂ በላይ ነው። ይህ ሳይረሳ ነገሩ የተለገጠበት መንገድ የሚነግረን አንድ ትልቅ ጉዳይ በዛ ዘመን በትልቅ የመንግስት መንበር ላይ ለመሰየም ዘርን መጠየቅ እና



ማወቅ እንደማያስፈልግ ነው። ለዚህ ማመሳከሪው በወታደራዊ ክንፉ ትልቅ ደረጃ ላይ የነበሩት ጀነራል ታደሰ የዘር ሃረግ ሳይመዘዘዝ በመቅረቱ ይህ ሚስጥር ስለተነገራቸው ነው። እነዚህን እውነታዎች ሳናጤን ዛሬ ላይ ቆመን እንትና የተገደለው፣ የተሰደደው የእንትን ተወላጅ በመሆኑ ነው እያልን በዘር ከረጢታችን ውስጥ ሆነን፣ የዘረኝነት መነፅር አጥልቀን የምንሰጠው ትንታኔ ትርጉም አልባ ይሆናል። ወደዚህ አይነት ትንታኔ የሚመራንም አሁን አዲስ ታሪክ ለመስራት ካለመቻላችን የመጣ ስራፈትነታችን የሰጠን የተትረፈረፈ ጊዜ ውሃ እንድናላምጥ ስላደረገን ይመስለኛል።

ወደዋናው ነገር ስመለስ የኦሮሞ ህዝብ ከአንደኛ ደረጃ በላይ እንዳይማር፣ ቋንቋውም እንዳይስፋፋ ተደርጎ ነበር የሚለው ክርክር በበቂ ማስረጃ እየተደገፈ ይቀርባል። እዚህ ላይአብሮ መነሳት ያለበት ጉዳይ ይህን የሚሉ ልሂቃን አሁን ባህልን የማስፋፋት፣ ትምህርትን ለሁሉም የማዳረስ መብት ህገ-መንግስታዊ እና ሰብአዊ መብት በሆነበት ዘመን የድሮውን እያነሱ ቆሞ ከመቅረት ባለፈ የበፊቱ የትምህርት ክልከላ የጎዳውን ሰፊ የኦሮሞ ህዝብ ክፍተቱን በሚሞላ መልክ ትምህርት እንዲያገኝ የተለየ ጥረት ሲደርጉ አይስተዋልም። የኦሮምኛ ቋንቋ ሁን ተብሎ እንዳያድግ ተደርጓል ብሎ እስከ ዛሬ የሞተውን የዘውዳዊ ስርአት ከመውቀስ አሁን የብሄረሰቦች መብት ተረጋገጠበት በሚባለው ዘመን የተለያዩ መዝገበቃላትን እና የኪነጥበብ ስራዎችን በቋንቋው በማዘጋጀት በፊት ነበረ ሚባለውን ክፍተት መሙላት ይቻላል። በተጨማሪም ቋንቋውን የማይናገርን የሃገር ልጅ የጎሪጥ ከማየት ይልቅ የወንድማማችነት ቅርርብ ፈጥሮ ቋንቋውን በፍላጎቱ እንዲማር ማድረግ ይሻላል። ይህን ለማድረግ ግን ችግር ላይ ቆሞ ከመቅረት ወደ መፍትሄ መንቀሳቀስን ይጠይቃል።

በጊዜ ሂደት ፓን አፍሪካኒዝም ከአፍሪካ ውጭ ያሉ አፍሪካዊያንን ወደሃገራቸው ከመመለስ ይልቅ በያሉበት መብታቸው እንዲከበር ወደ መታገል እንቅስቃሴነት የስልት ለውጥ አደረገ። በተጨማሪም በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ጥቁሮች እና ከአፍሪካ ውጭ ያሉ ጥቁሮችን (ኒግሮዎች) ጥያቄ የተለያየ ስለሆነ የተለያየየ የትግል ስልት እንደሚስፈልገው ታምኖበት የአፍሪካ ጥቁሮች እና ኒግሮዎች ችግራቸውን ባማከለ ሁኔታ ትግል እንዲያደርጉ በተለያየ ጊዜ ባደረጓቸው የፓን አፍሪካኒዝም ስብሰባዎች ላይ ተወሰነ።

አፍሪካን አሜሪካን ወይም ኒግሮ ተብለው የሚታወቁት ጥቁሮች ችግር በነጮች ምድር ላይ እንደመኖራቸው ችግራቸው በጥቁርነታቸው ይደርስባቸው የነበረው የዘር መድሎ እና የመብት ረገጣ ሲሆን በአፍሪካ ምድር ይኖሩ የነበሩ ጥቁሮች ችግር ደግሞ በአውሮፓዊን ቅኝ ግዛት ስር መተዳደራቸው ነበር። በመሆኑም እ.ኤ.አ 1945 ማንቸስተር ላይ በተደረገው 6ኛው የፓን አፍሪካ ጉባኤ አፍሪካ ውስጥ ያሉ ጥቁሮች በራሳቸው ሁኔታ አንድነት ፈጥረው ዐረ-ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ተወሰነ። ይህም ለ1963ቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት መነሻሆነ።

በአጠቃላይ ምንም እንኳን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተወለደው ከፓን አፍሪካን እንቅስቃሴ ቢሆንም ሁለቱን አንድ አድርጎ ማየት ስህተት አለው። የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ከአፍሪካ ውጭ በአለም ዳርቻ ላሉ እና በቆዳቸው ቀለም ጥቁረት መድሎ ለሚደርስባቸው ዳያስፖራ አፍሪካዊያን መብት የቆመ በመሆኑ አለማቀፋዊ ይዘት ነበረው። በሌላ በኩል የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የዚሁ አለማቀፋዊ ትግል ውላጅ ቢሆንም የሚታገለው አፍሪካ ውስጥ ላሉ፣ በትውልድ ሃገራቸው ላይ በባዕድ አስተዳዳሪ ለሚተዳደሩ ጥቁሮች የራስ መንግስት ምስረታ እና ከዛ በኋላ ስለሚኖረው አፍሪካዊ ትብብር ነበር።

ፓን አፍሪካኒዝም እንደ አጀማመሩ አለማቀፋዊ ቅርፅ ይዞ አልቀጠለም። አለማቀፍ ስብሰባዎችን ማድረጉንም በ1945 ካደረገው ስድስተኛው የፓን አፍሪካኒዝም ስብሰባ በኋላ አልቀጠለም። በምትኩ ጥቁሮች በብዛት በሚገኙባቸው የሁለቱ አሜሪካን ግዛቶች በተለይ በየካሪቢያ (West Indies) አካባቢዎች ወደ ሚደረጉ የመብት ማስከበር እንቅስቃሴወች (civil Right Movements) መልኩን ቀይሯል። ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኋላ



በአንፃራዊነት ለሰዎች ሰብአዊ እና ህጋዊ መብቶች መከበር በተሰጠው ትኩረት እና በጥቁሮቹም ተከታታይ የመብት ማስከበር ትግል የፓን አፍሪካኒዝም አላማዎች ከሞላጎደል ተሳክተዋል ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአሁኑ አጠራር የአፍሪካ ህብረት በማዕከላዊ ኮሚሽን ፅህፈት ቤቱ አማካኝነት ከፓን አፍሪካኒዝም በተለየ ህልውናውን ጠብቆ ይገኛል። የተነሳለትን አላማ ከማሳካት አንፃር ከታየ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የአሁኑ አፍሪካ ህብረት ሲያሳካ ካለመው ግብ በሩቅ ርቀትላይ ማገኝ ህብረት ነው።

## የተነከሰው የማን እጅ?

የፓን አፍሪካኒዝም ውላጅ የሆነው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ገቢራዊነት የብዙዎች አስተዋፅዖ እንዳለበት እሙን ነው። ነገር ግን በወሳኝ ሰዓት ተቃራኒ ሃሳቦች ታርቀው ድርጅቱ ህልውና እንዲያገኝ አፄ ሃይለስላሴ ያደረጉትን ጉልህ ሚና «የአፍሪካ አባት» የሚል ማዕረግ በመስጠት ነበር አባል ሃገራቱ የገለፁት። በአፍሪካ አንድነት እንዴትነት ላይ በወቅቱ ነፃ የወጡ ሃገራት አንድ አይነት አመለካከት አልነበራቸውም። ገሚሱ (የሞኖሮቪያ ቡድን) የአህጉሪቱን ፖለቲካዊ ጨምሮ ሁለንተናዊ ውህደት ሲሻ በተቃራኒው (የካዛብላንካ ቡድን) አባል ሃገራቱ ሉአላዊነታቸውን እንደጠበቁ በልል አንድነት ህብረት እንዲያደርጉ ይሞግት ነበር። በዚህ ሁኔታ ልዩነቱን ወደ ስምምነት አምጥቶ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በማዋለዱ በኩል የአፄ ሃይለስላሴ ሚና ጎላ ያለ ቢሆንም አሁን አሁን የጋናውን ዶክተር ክዋሜ ኒክሩማ ቀዳሚ ማድረጉ ነገር ይስተዋላል።

በቻይና ልግስና አዲስ አበባ ላይ በተሰራው የህብረቱ አዳራሽ በርላይም እንደ በረሃ ዛፍ ለብቻው እንዲቆም የተደረገው የክዋሜ ኒክሩማ ሃውልት ነው። ሃውልቱ ለክዋሜ ኒክሩማ ሳይሆን የሚገባው ለአፄ ሃይለስላሴ ነበር ሲሉ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን እና ዶ/ር ያቆብ ኃ/ማርያምን ጨምሮ ብዙ የሃገራችን ምሁራን እና ታላቢዎች ተከራክረዋል። በተቃራኒው የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በወቅቱ አስተያየታቸውን ሲሰጡ የክዋሜ ኒክሩማን ሃውልት መቆም መቃወም ያጎረሰን እጅ መንከስ እንደሆነ ነበር የገለፁት። ምክንያታቸው ደግሞ በፓን አፍሪካን እንቅስቃሴ ከክዋሜ ኒክሩማ የበለጠ አስተዋፅኦ ያበረከተ ከወዴት ማምጣት ይቻላል የሚል ነበር።

አቶ መለስ ሲያክሉም የክዋሜ ኒክሩማን በዶክትሬት ማማያ ፅሁፋቸዉ የኢትዮጵያን ስም ደጋግሞ ማንሳሳት ጠቅሰው ደጋግመዉ በጠሯት ሃገር ላይ በተገነባ ህብረቱ አዳራሽላይ ሃውልታቸው ቢቆም ስለውለታቸው ምላሽ ይሆናል እንጂ ምን ጉዳት አለው ሲሉ ነበር የሃውልቱን ለተገቢው ሰው የመቆም አግባብነት ያስረዱት።

ፓን አፍሪካኒዝምን እና አፍሪካ አንድነት ድርጅትን አንድ ካደረገው የመጀመሪያው የአቶ መለስ ክርክር ብንነሳ ዶ/ር ክዋሜ ኒክሩማ ለፓን አፍሪካ እንቅስቃሴ ብዙ መስራታቸው እውነት ነው። ያማለት ግን በእንቅስቃሴው ውስጥ ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው ማለት አይደለም። እነማርከስ ጋርቬይ፣ ዊሊያም ዱ ቦይስ እና ሌሎች ላቅ ያለ ሚና ያላቸው ሰዎች አሉና ከክዋሜ ኒክሩማ የበለጠ ፓን አፍሪካኒስት ማምጣት አይቻልም ያሉት ነገር ትንሽ የተጋነነ አባባል ነው። በተጨማሪም የፓን በአፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ተዋናይ መሆን ማለት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት እውንነት ቀዳሚ ሰው መሆን ማለት አይደለም። የኢትዮጵያን ስም ምርምር ፅሁፋቸው ላይ ደጋግመው ስላነሱ ሃውልቱ ይገባቸዋል የተባለውም ብዙ ጠንካራ መከራከሪያ አይደለም። ሃገራችን በወቅቱ የነፃነት ተምሳሌት ተደርጋ ትወሰድ ስለነበር ስሟ ተደጋግሞ ይነሳ ነበር እና የኒክሩማን አዲስ የሚያደርገው ነገር የለም።

ለህብረቱ እውንነት የክዋሜ ኒክሩማም ሆነ የአፄ ሃ/ስላሴ ሚና ትልቅ ቢሆንም ብቸኛ ግን አልነበረም። ስለሆነም በግሌ እንደዚህ በብዙ ሰዎች አስተዋፅኦ እውን የሆነ ነገርን ለመዘከር የዋና አስተዋፅኦ አድራጊዎቹን ምስል የሚያሳይ የህብረት ሃውልት ተሰርቶ፤ ላቅ ያለ ተሳትፎ ያደረጉትን ሰዎች ምስል ጎላ ብሎ እንዲታይ ማድረግ ቢቻል የሃውልቱን ትርጉም ሰጭነትም ይጨምራል፤ ውዝግቡንም ይቀንሳልብየ አስባለሁ። የክዋሜ ኒክሩማን እጅ ላለመንከስ የብዙ ሰዎችን እጅ አመድ አፋሽ ያደረገ ነው የሃውልቱ አቋቋም። በተጨባጭ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ በአንድሰው አስተዋፅ ብቻ እውን እንደማይሆን እየታወቀ ወረታውን ሁሉ ለአንድሰው መስጠት አጉርሶ የተነከሰውን እጅ ብዙ ያደርገዋል።



## የአፍሪካ ነፃነት፡ በሃገር ጅብ መበላት

ከከባድ ትግል በኋላ ከቅኝ ግዛት ነፃ የወጡ የአፍሪካ ሃገራት ከነፃነት በኋላ በሃገራቸው አምባገነን መሪዎች መዳፍ ስር መውደቃቸው ነፃነታቸውን ግንጥል ጌጥ አድርጎባቸው አብዛኞቹ ሃገራት መከራቸው ሳይቀል፣ የጦርነት አውድማ፣ የከፋ ድህነት ቀጠና፣ የኋላ ቀርነት ተምሳሌት ሆነው ቀጥለዋል።

ከነፃነት በኋላ አብዛኛውን የአፍሪካ ሃገራት ለመምራት ስልጣን የተረከቡት መሪዎች በነፃት ትግሉ ወቅት ግንባርቀደም ታጋዮች ነበሩና ይህንን እንደውለታ ለህዝባቸው ደጋግመዉ እየነገሩ ራሳቸውን የሃገር ባለቤት ያደርጋሉ። የነፃነት አባትነታቸውን እንዲዘክር የሚያሰሩት ፕሮፖጋንዳም ስልጣን ላይ ተጥዶ ዘመናትን ለማስቀጠር የሚረዳ ስብከታቸው ነው። በዚሁ ስልጣን ላይ ሙጥኝ ማለት ሳቢያ ሃውልት የቆመላቸውን ክዋሜኒክሩማን ጨምሮ ብዙዎቹ የነፃነት ዘመን ታጋይ የአፍሪካ መሪዎች ከስልጣን የሚነሱት በመፈንቅለ መንግስት ካልሆነም በትጥቅ ትግል ነበር። በተለይ በ1970ዎቹ አፍሪካ መፈንቅለ መንግስትን ልማዷ አድርጋ ነበር። አሳዛኙ ነገር በመፈንቅለ መንግስቱ ወደስልጣን የሚያመጣው ወታደሮችን ስለነበረ ሃገሪቱን ወደ ሌላ የወታደራዊ አምባገነንነት ምዕራፍ ከትቷቸው የዲሞክሲያዊ መንግስትን መምጫ ቀን ሩቅ መንገዱንም ውስብስብ አድርጎታል።

ስልጣን በምርጫ ማስረከብ በአፍሪካ ብርቅ በመሆኑ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች የአፍሪካ ጉብኝታቸውን ይህንን ባደረጉ ትቂት ሃገራት ላይ ብቻ እስከማድረግ ይደርሳሉ። በምርጫ ስም ስልጣን ላይ የሚሰነብቱ «ተመራጭ» አምባገነኖችም የትየለሌ ናቸው። የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ስልጣን የሚያፈቅሩት እንዲሁ አይደለም። የሃገርን ሃብት መዝብረው ራሳቸው የድሃ ሃገር ሃብታም መሪ ሲሆኑበት፣ ሰባት ጉልበታቸውንም ቱጃር ሲያደርጉበት እንጂ። ነዳጅ ዘይት ወይም ሌላ የከበረ ማዕድን ባለቤት ሃገር ሚመሩ ከሆነ ሃገርን ጠቅልሎ የመጉረስ ያህል የሃገር ሃብት ይመዘብራሉ። ይህ የሌላቸው ደግሞ በደሃ ህዝብ ስም በሚመጣው የእርዳታ ገንዘብ ኪሳቸውን አዳብረው ከአለም ግንባር ቀደም ሃብታሞች ተርታ የተሰለፉም አይጠፉም። የዶላር ንግድም ሌላው ሃገር ሚዘርፉበት መንገድ ነው። በዚህ አይነት አምባገነን እና ሙሰኛ መሪዎች መዳፍ ውስጥ በሁለንተናዊ ጉስቁልና የሚላጋውን

የጀመረው አፍሪካ አንድነት/ህብረት ከልጅ እግሩ አቻው የአውሮፓ ህብረት ጋር ሲወዳደር ያልተራመደ ጎልማሳ፣ ልጁ የቀደመው አባት መሆኑ በግልፅ ይታያል።

ስፊዋን አፍሪካ አህጉር ወደ አንድ የተዋሃደች ሀገር ከማምጣቱ በፊት በህዝቦቿ መሃል አፍሪካዊ ማንነት የመፍጠር ስራ መሰራት እንዳለበት እሙን ነው። ይህን ለማምጣት የሚደረግ የህዝብ ለህዝብ ቅርርብ፣ የባህል ልውጥን የማዘውተር ስራ ሲሰራ አይታይም። በመሆኑም በአፍሪካ ሃገራት ህዝቦች መሃከል የመቀራረብ፣ ወንድማማችነት ስሜት አይታይም።

በተለይ የመግሪብ ሃገራት የሚባሉ ሰሜን አፍሪካዊ አረብ ሀገራት ከተቀረው አፍሪካዊ ጥቁር ህዝብ ይልቅ ከአህጉሩ ውጭ ወዳሉት የመካከለኛው ምስራቅ ሃገራት የመሳብ ነገር ይታያል። በሌሎቹ የአፍሪካ ሃገራት ህዝቦች መሃከል ያለው በአፍሪካዊነት የመሳሳብ አንድነት ስሜትም በቂ ነው የሚባል አይነት አይደለም። አፍሪካዊ ማንነትን በአህጉሪቷ ህዝቦች መሃል የመፍጠሩ ነገር በዘገየ ቁጥር ብዙ የተባለለት የተባበረች አፍሪካን የመፍጠሩን ነገር ያዘገየዋል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የአፍሪካ አንድነት ወደ አፍሪካ ህብረት ሲቀየር አንዱ አላማው በአለም ኢኮኖሚ የአፍሪካን ድርሻ ማሳደግ ነበር። ለዚህ ተግባራዊነት ደግሞ መጀመሪያ በአፍሪካ ሃገራት መሃከል ያለውን የንግድ ግንኙነት (Intra Continental Trade) ቀና የሚያደርጉ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። በዚህ ረገድ የአውሮፓ ህብረትን አመርቂ ስራ ብንመለከት የአፍሪካ ህብረትን ደረጃ መረዳት ያስችላል። በአውሮፓ ሃገራት መሃከል ያለውን የንግድ ልውውጥ ለማቀላጠፍ እንዲያመች ከሁሉ አስቀድሞ ሃገራቱን በፈጣን የባቡር እና የአስፋልት መንገድ የማያያዝ ስራ ከመሰራቱ ባሻር የሃገራቱ ዜጎች ወደ የትኛውም የአውሮፓ ሃገር በቀላሉ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል የይለፍ (shangen visa) በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። በተጨማሪም በአባል ሃገራቱ መሃከል ያለውን ግብይት ለማቀላጠፍ ዩሮ የተባለ የጋራ መገበያያ ገንዘብ ከተጀመረ ሰነበተ። በኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ያሉ ሃገራት የሚደጎሙበት ስርአትም በተገቢው ሁኔታ እየተሰራበት ያለጉዳይ ነው። ለግሪክ የተደረገውን እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል። ይሄን ሁሉ አህጉራዊ ትስስር እያመቻቸ ያለው አውሮፓ ህብረት እንደ አፍሪካ ህብረት ወደ አንድ አውሮፓዊ ሃገርነት የመድረስ አላማ ሳይኖረው ነው። በተቃራኒው በፖለቲካ



የተዋሃደች አንዲት አፍሪካ የመፍጠር ህልም ያለው የአፍሪካ ህብረት ይህን ሲያደርግ አይታይም። ከአንድ የአፍሪካ ሃገር ወደሌላው ለመንቀሳስ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ብዙ ሳይራቅ ኬንያ ትንሽ የቆየ ሰውን መስማት፣ ደቡብ አፍሪካ ለመድረስ በመንገድ ላይ ካሉ ሃገራት ፖሊሶች ጋር አባሮሽ የሚገጥሙትን የሃገራችን ስደተኞች ታሪክ መስማቱ በቂ ነው።

የአፍሪካን ፀጥታና ሰላም ለማስከበር፣ የአፍሪካን ችግር በአፍሪካዊያን ህብረት በጋራ ለመስራት ሁሌ እቅድ ሚያወጣው የአፍሪካ ህብረት ወደ አንድ ሰላሟ የተናጋ ሃገር ሰላም አስከባሪ ለመላክ ሁሌ አይን አይን የምትታየው የኛዋ ሃገር ኢትዮጵያ ነች እንጂ በተደራጀ መልኩ የሁሉንም ሃገር ጦር ባማከለ ሁኔታ በትክክለኛው ሰአት ሰላም አስከባሪ ልኮ ችግሩ ሳይብስ በየመፍታቱ ስራ ብዙ ይቀረዋል። ባስ ሲልም ስመትልቁ አፍሪካ ህብረት ቁጭ ብሎ የምእራባዊኑ ጦር ገብቶ የአፍሪካን ጉዳይ እልባት ሲሰጥ በሊቢያ እና በኮትዲቯር ሁኔታ ታይቷል። የሊቢያን ህዝብ እልቂት የገታው የምእራባዊኑ ጦር ገብቶ እንጂ የአፍሪካ ህብረት አልነበረም። ህብረቱ የችግሩ የመፍትሄ አካል መሆን ቀርቶ የህዝቦች ስቃይ እንዲያበቃ አምባገነኑን የፕሬዚደንት ጋዳፊ አመራር ሲያወግዝ እንኳን አልተደመጠም። በኮትዲቯር በአላሳን ዋታራ እና ሎረን ባግቦ መሃከል የነበረውን የስልጣን ይገባኛል ውዝግብም የሀገሪቱ ቀድሞ ቅኝ ገዥ ፈረንሳይ ገብታ ነው አንድ ያለችው።

በተመሳሳይ የሞሮኮን እና ከምእራባዊ ግዛቷ የተገነጠለችውን የምዕራብ ሳራዊ ሪፐብሊክን ጉዳይ በመፍታት ፋንታ የአፍሪካ ህብረት ያለሞሮኮ ይሁንታ ለተገንጣየይዋ ሃገር እውቅና በመስጠቱ ሞሮኮ ከ1983 ጀምሮ ከህብረቱ እንደወጣች ቀርታለች። እስካሁን ህብረቱ የሞሮኮን ወጥቶ መቅረት ነገሬ ብሎ ለመመለስ ምንም ሲሰራ አልተሰማም። በሰሜን ማሊ የቱዋሬግ ተገንጣይ ቡድኖች እና በደካማው ማዕከላዊ መንግስት መሃከል የነበረውን ሀገሪቱን ለማፈራረስ የተቃረበ ዉውዝግብ ፈረንሳይ ገብታ የማዕከላዊ መንግስቱን ወታደሮች እና ፖሊስ አሰልጥና፣ አጠናክራ ነው ነገሩ እልባት ያገኘው።

የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ውዝግብ እና እሱን ተከትሎ ከቀደመ ወዳጅነታቸው ጋር በማይገጥም ጠብ ላይ ያሉትን የሁለቱን ሃገር መሪወች የማቀራረቡ ነገርም በአፍሪካ ህብረት በአመርቂ ሁኔታ የተሄደበት አይደለም። የደቡብ እና የሰሜን ሱዳን በአብየ ጉዳይ ላይ ውዝግብ፣ የሶማሊ መንግስት አልባነት፣

በየፍርድቤቶቻቸው እንዲፈቱ ስለሚጠበቅ ለጋሾቹ እጃቸውን ለመዘርጋት ላይፈልጉ ይችላሉ።

ከላይ የቀረቡት ምክንያቶች ፍርድቤቱን የማቋቋሙ ነገር ቢያንስ በቅርብ ጊዜ እንደማይሳካ ጠቋሚዎቻቸው። አፍሪካዊያኑ መሪዎችም ቢሆኑ ይህን አያጡትም። ፍርድ ቤቱን ስለመመስረት የሚያወሩትም ICC በከሰሳቸው ሰሞን ብቻ ነው እንጂ ከላይ እንደተጠቀሰው ሃምሌ ላይ ፍርድቤቱን ማቋቋም እንደማይቻል አምነው ነበር። ይህን ካወቁ አፍሪካዊ ፍርድቤት እንመስርታለን ከማለቱ አዋጭ የሚሆነው በሃገራቸው የህግ በላይነትን አስፍነው፣ በመንግስታቸው ሊፈፀሙ የሚችሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መጠየቅ የሚችል የፍትህ ስርአትመዘርጋቱ ነው። ይህ ካልሆነ በአገራቸው ውስጥ የሚያደርጉት ቅጥ ያጣ የመብት ጥሰት በአለም የፍትህ አደባባይ ቢያስጠራቸው የሚጠበቅ ነው። የቤት አመል ገበያ ያወጣል ማለትም ይህ ነው።

## 7.3 የሞ ኢብራሂም ኢንዴክስ - የአፍሪካ መስተዋት

ምድራችን ከያዙቻቸው ክፍለ-ዓለማት ውስጥ አፍሪካ የዲሞክራሲ ቱርፋት የሆነውን መልካም አስተዳደር በማስፈኑ በኩል እምብዛም አልተሳካላትም። ለሁሉም የአፍሪካ ችግር ቅኝ አገዛዝን ተጠያቂ የሚያደርጉት የ«Dependency Theory» አቀንቃኞች ይህንንም የቅኝ አገዛዝ ተፅእኖ ውጤት ያደርጉታል። ነገር ግን ለረዥም ዘመን በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ የእስያ እና የደቡብ አሜሪካ አብዛኛ ሃገሮች ከቅኝ ግዛት ከተላቀቁ በኋላም ዲሞክራሲን ማሳደግ ችለዋልና የአፍሪካን ያልተሳካ ጉዞ መንስኤ ቅኝ አገዛዝ ብቻ እንደሆነ ማሰብ አያስኬድም። ይልቅስ የአፍሪካ በመልካም አስተዳደር እና ዲሞክራሲን በመገንባት በኩል ፊቀቅ ያለማለት ዋነኛ ምክንያቱ ከቅኝ አገዛዝ ማክተም በኋላ ወደ ስልጣን የመጡ መሪዎች የፖለቲካ ስብዕና እና የአመራር ዘይቤ ነው።

አብዛኞቹ የአፍሪካ መሪዎች ስልጣንን በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ላሸነፈ ከመልቀቅ ይልቅ ምርጫውን የይስሙላ በማድረግ ስልጣን ላይ መከራረምን ይመርጣሉ። የሃገራቸው ህገ-መንግስት በስልጣን ላይ ይቆዩ ዘንድ የሚፈቅድላቸው ዘመን ሲገባደድ ደግሞ የወንበር ፍቅራቸው ህገ-መንግስት እስከ መደለዝ ያደርሳቸዋል። ባስ ያሉት ደግሞ ከነአካቴው የስልጣን



ዘመናቸው በምድራዊ ህግ የማይገደብ ሲሆን ከልጣን የሚለያቸው መቃብር ብቻ ይሆናል። የመሪዎቹ በዚህ መልክ ስልጣ ላይ መጥኝ ማለት የሃገራቱን ለውጥ ፈላጊዎች አማራጭ አሳጥቶ የትጥቅ ትግልን እና መፈንቅለ መንግስትን እንደ አማራጭ እንዲወስዱ በማድረጉ አፍሪካ የእርስ በርስ ጦርነት እና ያለመረጋጋት አምባ እንድትሆን ሆኗል። ይህ አብዛኛውን የአህጉሪቱን ክፍል የድህነት ቀጠና እና የጉስቁልና ምድር አድርጎ ምድሪቱንም ‹ጨለማዋ አህጉር› እስከመባል አድርሷታል።

በምዕራቡ አለም እንደ ትልቅ ጉዳይ የማይታየው ስልጣንን በዲሞክራሲዊ ምርጫ የማስረከቡ ነገር በአፍሪካ የሚያሸልም፣ የሚያስሞግስ ብርቅ ተግባር ነው። ለዚህ እንደማሳያ የሚሆነው እ.ኤ.አ በ2006 የተመሰረተው የሞ ኢብራሂም ተቋም ነው። ይህ ተቋም ስልጣናቸውን በሰላማዊ መንገድ በምርጫ ለረታቸው ተቀናቃኝ ፓርቲ ያስረከቡ የአፍሪካ መሪዎችን ሬብጣ ዶላር ይሸልማል። የተቋሙ መስራች በትውልድ ሱዳናዊ በዜግነት እንግሊዛዊ የሆኑት በጎ አድራጊ እና ስራ ፈጣሪ ዶ/ር ሞ ኢብራሂም በሙያቸው ኢንጅነር እና በአሁኑ ሰአት የ 1.1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ባለቤት ናቸው። ይህንን ሃብት ከማግኘታቸው በፊት በተለያዩ የቴሌ ኮሙኒኬሽን ኩባንያዎች አገልግለዋል። በ1998 «ሴል ቴል» በመባል የሚጠራ የራሳቸውን የቴሌ ኮሙኒኬሽን ኩባንያ መስርተው የነበረ ቢሆንም በ2006 ኩባንያቸውን በ3.4 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሸጠው የሞ ኢብራሂም ተቋምን መሰረቱ።

### የሞ ኢብራሂም ተቋም ምን ይሰራል?

"Governance is Crucial" የሚል ሎጎ ያለው ይህ ተቋም በአፍሪካ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ዋና የሆነውን የዲሞክራሲያዊ አመራር ስብዕናን በመሪዎች ዘንድ ማስፈን ነው። አያይዞም በአፍሪካ ያለውን የፖለቲካዊ አመራር ሁኔታ በተመለከተ ውይይት እና ክርክር እንዲኖር ያደርጋል። ለዚህም ሞ ኢብራሂም ኢንዴክስ የሚባል የአፍሪካን ሃገራት ሁለንተናዊ የአመራር ሁኔታ የሚገመግም ባለ 94 መስፈርት መገምገሚያ አዘጋጅቶ የሃገራቱን ደረጃ ይፋ ያደርጋል። ደረጃው ሲወጣ በዋናነት ታሳቢ የሚደረገው የሃገራቱን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ፣ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የተደረገ ጥረት እና የተገኘ ተጨባጭ ውጤት፣ በሰብአዊ ልማት (Human Development Index) በኩል የተመዘገበ ውጤት፣ የዜጎችን ሁለንተናዊ ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃር

የቆምኩት ለዚህ ነውና አስር እጥፍ እና አስር ጊዜ ሂትለር ነኝ» የጥቁሮች ነፃነት የሚረጋገጠው በቅኝ ገዥ ነጮች የተዘረፉት ንብረታቸው እጃቸው ሲገባ እንደሆነ የሚያምኑት ሙጋቤ በነጮች የተያዘውን የሃገራቸውን መሬት ለጥቁር ገበሬዎች በማከፋፈሉ ብቻ አይበቃም ብለው ያስባሉ:: በሃገሪቱ ያሉት የንግድ ተቋማት በጥቁሮች እንዲያዙ እንደሚሰሩ ይህም የነፃነት ትግላቸው የመጨረሻ ምዕራፍ እንደሆነ በ2008 ምርጫ «ማሸነፋቸውን» አስመልክቶ ባደረጉት ንግግር አስታውቀዋል:: ሮበርት ሙጋቤ ጥቁር የሃገራቸው ልጆች በሃገራቸው ሃብት ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ያደረጉት ጥረት በውሮፓዊያኑ ዘንድ ክፉ ጠላት ቢያደርጋቸውም እውነተኛ ፓንአፍሪካኒስት፣ የጥቁሮች ጠበቃ አድርገው የሚያንቆለጳጵሱዋቸውም ብዙ ናቸው:: በተለይ በስልጣናቸው የመጀመሪያ አመታት በሃገራቸው የተሻለ የኢኮኖሚ እቅም መገንባት ችለው ስለነበረ ተወዳጅነታቸው ከፍ ያለ ነበር:: ከትግል በፊት አስተማሪ እንደመሆናቸው የሃገራቸውን የትምህርት ፖሊሲ በጥሩ ሁኔታ ማስኬድ መቻላቸውም የሚያስወድሳቸው ተግባር ነው:: በ2008 ከዙምባቤ ህዝብ ውስጥ 90% ማንበብ፣ መፃፍ፣ እና ሂሳብ ማስላት የሚችሉ እንደሆኑ ሙጋቤን የሚጠሉት ምዕራባዊያን መገናኛ ብዙሃንም ያመኑት ነው:: ሮበርት ሙጋቤ የመሬት ክፍፍሉን አምርረው ከያዙበት ከ1998 በፊት በምዕራባዊያኑ ዘንድም ደህና የሚባል ተቀባይነት ነበራቸው:: ማሳቹሴትስ እና ሚችገን እስቴት ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ ከታላላቅ የምዕራባዊን እና የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች በርከት ያሉ የክብርዲግሪዎች ተበርክተውላቸዋል::

ከሮበርት ሙጋቤ በተለየ የነፃነት ትግል ምዕራፋቸውን እስርቤት ሆነው ሲያደርጉት በነበረ አታካች ድርድር የቋጩት ኔልሰን ማንዴላ ነጮችን ከፖለቲካው ሀገነት ማስነሳቱ ቢሳካላቸውም በነጮች እና ጥቁሮች መሃከል ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል በማምጣት በኩል የማንዴላ ትግል ብዙ ርቀት አልሄደም:: ኔልሰን ማንዴላ እና ሮበርት ሙጋቤ የሚለያዩበት አንድ እውነታም ይህ ነው:: ሌላው የሁለቱ ልዩነት የቀድሞ ገዥዎቻቸውን ከድል በኋላ ያስተናገዱበት መንገድ ነው:: ማንዴላ እራሳቸውን ለሃያሰባት ድፍን አመታት በእስርቤት ያማቀቃቸውን፣ ህዝባቸውን ከሰው ደረጃ አጉድሎ ወደ እንስሳት ማንነት ባወረደ መንገድ ሲገዛ የነበረ ስርአት ተዋናዮችን ይቅር ብለው ደቡብ አፍሪካ ለሁሉም ነዋሪዎቿ እንድትሆን መጣራቸው በአለም ላይ የሚደነቁ መሪ አድርጓቸዋል:: በተጨማሪም በአብዛኞቹ የአህጉሪቱ የነፃነት



ታጋዮች ዘንድ ባልተለመደ ሁኔታ ስልጣን ላይ ሙጥኝ አለማለታቸው ነው:: አብዛኞቹ የአፍሪካ የነፃነት ታጋዮች ከድል በኋላ በሃገራቸው የፖለቲካ መንበር ላይ መሰንበትን ይመርጣሉ:: ይህንን ሲያደርጉ የህዝባቸውን የለውጥ ፍላጎት በመጨፍለቅ ሲልም ለውጥ ፈላጊ ዜጎችን ማሰርን፣ መግደልን፣ በማሳደድን የጨመረ የሃይል እርምጃን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ አወጣነው በሚሉት ህዝብ ላይ እየወሰዱ ነው:: ማንዴላ ግን እጃቸው የገባውን ስልጣን ነገሬ ሳይሉ በጊዜ ከወንበር የተነሱት ህዝባቸው ይቆዩ ዘንድ እፈልገ እንጅ የለውጥ ያለህ እያለ አልነበረም:: ይህ ሮበርት ሙጋቤ ያላገኙት ከዚህ በኋላም ሊያገኙት የማይችሉት የማንዴላ ልዕልና ነው:: የሁለቱ የነፃነት ታጋዮች እንደ ተራራ የገዘፈ ልዩነትም ይህ ነው::

ለማንዴላ መወድስ የሚበዛው የነጮችን የሃብት መሰረተ ሳይነዱ ስለቀሩ ነው:: ሮበርት ሙጋቤ ደግሞ የነጮችን የሃብት መሰረት ከስሩ ስለነቀሉ ነው የምዕራባዊን መገናኛ ብዙሃን ነውራቸውን የሚያበዙት የሚለው ክርክር እውነትነት ቢኖረውም የማዴላ ከስልጣን የተዋጀ ፖለቲካዊ ማንነት ግን እንደ ነጭም እንደ ጥቁርም ሆኖ ቢታይ ትርጉሙ አንድ ነው:: ይህም ማንዴላ ከስልጣን መነሳት እንደ ማይገድል ያሳዩ፣ አፍሪካም ለአርአያነት የሚበቃ ታላቅ መሪ ሊፈልቅባት እ‹ደሚችል ያስመሰከሩ ብቸኛ መሪ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: የማንዴላ በጊዜ ስልጣን መልቀቅ የትግላቸው እውነተኛ ግብ ህዝብ ነፃነት እንጅ በነፃ አውጭነት ስም የስልጣን ጥምን ለማርካት፣ በሃገር ሃብት ቤተ-ዘመድን ቱጃር ለማድረግ እንዳልሆነ ግልፅ ምስክር ነው:: በዚህ ረገድ ሮበርት ሙጋቤ እንከናቸው ብዙ ነው:: 33 አመት ስልጣን ላይ ከመባጀታቸው በላይ ረዥሙ የስልጣን ዘመናቸው የህዝባቸውን መከራ የሚያከብድ እንጅ የተሻለ ምዕራፍን የሚያመጣ አልሆነም::

የሮበርት ሙጋቤ ታላቅ ስኬት ተደርጎ የሚወሰደው የመሬት ክፍፍሉ አካሄድ ሳይቀር የስልጣን ጊዜያቸውን ለማራዘም ለረዷቸው የጦር አበጋዞቻቸው ያደላ ነው የሚል ትችት አላጣውም:: የመሬት ይዞታ ድልድል በሚያደረግበት ወቅት ሮበርት ሙጋቤ የግብርና ሙያ እውቀቱም ሆነ በስራው የመቀጠል ፍላጎቱ ለሌላቸው የጦር አበጋዞቻቸው በርካታውን መሬት እና የእርሻ መሳሪያዎች በገፀ-በረከትነት በሹመታቸው መሬቶቹ ጦም እንዲያድሩ፣ የእርሻ መሳሪዎቹም እንዲዝጉ በመሆኑ የሃገሪቱ "African Institute for Agrarian studies (AIAS)" የተባለው ተቋም እኤአ በ2006 ዓ.ም በስድስት የሃገሪቱ

## የነፃነት ተጋይነት ማስት?!

ኔልሰን ማንዴላም ሆኑ ሮበርት ሙጋቤ ስለነፃነት ብዙ እስር እንግት አሳልፈዋል። በዚህ ረገድ ሁለቱን ሰዎች በአንድነት መጥራት የሚቻለው ግን በየሀገራቸው ፕሬዚደንት እስከሆኑበት ዘመን ብቻ ነው። የነፃነት ትግሉ በጥቁሮች ድል ተጠናቆ ሁለቱ ታጋዮች የየሀገራቸው ፕሬዚደንት ከሆኑ በኋላ ያለው ማንነታቸው እጅጉን ይለያያል። ኔልሰን ማንዴላ ነፃ ያወጧት ሀገራቸው ከቅኝ ግዛት ማክተም በኋላም ለሁሉም ነዋሪዎቿ የሚመች ፖለቲካዊ ከባቢ ያላት የነፃነት ምድር ትሆን ዘንድ ፋናወጊ ለመሆን ራሳቸው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርን አስጀምረዋል። ተከታዮቻቸውም ሌላው ቢያቅታቸው ከስልጣን በጊዜ መነሳቱ አልከበዳቸውም። በመሆኑም የደቡብ አፍሪካ ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታው ጥያቄ ቢኖረውም በፖለቲካው ረገድ የፈለገውን መርጦ፣ ያልመሰለውን ተቃውሞ በነፃነት እየተነፈሰ ይኖራል።

ሮበርት ሙጋቤ ደግሞ የነፃነት ትግል ማለት ጥቁር ከነጭ ጋር ብቻ የሚያደርገው ትንቅንቅ አድገው እንደማሰብ ይሞክራቸዋልና ነጭ ገዥዎቻቸውን ካስወገዱ በኋላ የእድሜ ልክ ፕሬዚደንት ሆነዋል። ይህን ሲያደርጉ ነፃ አወጣሁት የሚሉትን ህዝባቸውን ድምፅ አፍነው፣ በነፃነት እንዳይናገር ለጉመው ነው። ይህ ድርጊታቸው ከነፃነት ጋር እንደሚጣረስ ሙጋቤ ቆም ብለው የሚያስቡ አይመስልም። በጥቁር አምባገነን መንግስት አሳር መከራ በማየትም ሆነ በነጭ ቅኝ ገዥ በመንገላታት ውስጥ ነፃነት የለም። የሮበርት ሙጋቤ ትግል ያመጣው ደግሞ ነፃነትን ሳይሆን ነጭ ገዥን በጥቁር አምባገነን መተካትን ነው። ይሄ ደግሞ «የአገሬ ጅብ ይብላኝ» ለማለት ካልሆነ ለውጥ የለውም።

ለ33 አመት ሮበርት ሙጋቤ በገዟት ዚምባቤ የመሰብሰብ መብት በህግ ተከለከለ ነው። የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር ወይም ደጋፊ መሆን በአፍ በአፍንጫ ደም እስኪመጣ የሚያስደበድብ አለያም የሚያሳስር «ድፍረት» ነው። እኤአ በ2008 በተደረገው ሃገራዊ ምርጫ ማግስት የሃገሪቱ ዋነኛ ተቃዋሚ ፓርቲ "Movement for Democracy and Cahnge" በምኅፃሩ (MDC) መሪ ሞርጋን ቻንጋራይ በሃገሪቱ ፖሊስ ክፉኛ በመደብደባቸው የተነሳ ብዙ ደም እንደፈሰሳቸው፣ ጀርባቸው፣ እጅ እና እግራቸው ላይም ስብራት ጉዳት እንደደረሰባቸው በወቅቱ ለቢቢሲ ገልፀው ነበር። ስለዚህ ጉዳይ የተጠየቁት



ሮበርት ሙጋቤ ታዲያ «ቻንጋራይ የሚገባውን ነው ያገኘው ማን የተከለከለ ነገር አድርግ አለው» ሲሉ ነበር የመለሱት።በሃገሪቱ ነፃ ጋዜጠኛ መሆንም ለእስር እና ለሞት መደገስ ማለት ነው። ጋዜጠኞቹ ሲታሰሩ ደግሞ ሃሰተኛ መረጃ በማሰራጨት የሚል ታርጋ ተለጥፎባቸው፣ ፍርድ ፊት ቀርበው ነው። ፍርድቤት ሳይቀርቡ የሚገደሉ እና የገቡበት የማይታወቅ ጋዜጠኞችም እንዳሉ ሂውማን ራይትስዎች በየጊዜው በሚያወጣው ሪፖርቱ የሚያስታውቀው ነገር ነው። ለሮበርት ሙጋቤ የእርሳቸውን የስልጣን ዘመን ከመጫኛ መርዘም፣ የአስተዳደራቸውን አምባገነንነት፣ ሙስኝነት የተቸ ሁሉ ከነጮች የወገነ ከሃዲ ነው። በሃገሪቱ የሚካሄድ ምርጫ ትክክለኛ የሚሆነው እርሳቸውን አሸናፊ የሚያደርግ ውጤት ይዞ ከመጣ ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት ፈረንጆቹ Ballot fixing dictator (የምርጫን ውጤት ቀድሞ የሚያውቅ አምባገነን) ይሏቸዋል።

በ2008ቱ ምርጫ የሞርጋን ቻንጋራይ ፓርቲ MDC ብዙ ተግዳሮችን ተቋቁሞ 47.9% ለ 43.2% በሆነ ውጤት የሮበርት ሙጋቤን እናት ፓርቲ ZANU-PFን ማሸነፉን የሃገሪቱ ምርጫ ኮሚሽን በማወጁ ነበር የኮሚሽኑ ዋና ዋና ሰዎች ወደ እስርቤት የተወረወሩት። ወዲያውም በአንደኛው ዙሩ ምርጫ ሁለቱም ፓርቲዎች መንግስት ለመመስረት የሚያበቃ ውጤት አላስመዘገቡም በሚል ሰበብ ሁለተኛ ዙር ምርጫ የሃገሪቱ ህግ እንደሚያዘው 21 ቀንን ሳይጠብቅ ወዲያው እንዲደረግ ተደረገ። በውጤቱም የሮበርት ሙጋቤ ፓርቲ ሃያ አንድ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውጤቱን በእጥፍ አሳድጎ 85%ቱን የመራጭ ድምፅ አገኘ ሲባል ተቀናቃኙ MDC ደግሞ ወደ 9.3% አሽቆለቆለ ተብሎ ያለምንም ሃፍረት ታወጀ። በስተመጨረሻው በSADC አሸማጋይነት ተቀናቃኞቹ ስልጣን ተጋርተው የምርጫው ውዝግብም እልባት አገኘ። እዚህ ላይ ሮበርት ሙጋቤን የመሰሉ አምባገነን ስልጣን ለማጋራት መስማማታቸው ራሱ እንደ መልካም እርምጃ የሚወሰድ ነው።

ከላይ የተዘረዘሩትን የዚምባቤ ትቂት ማሳያወች እና የሌሎች አፍሪካ ሃገራትን እውነታዎች ስናጤን በአፍሪካ የነፃነት ትግል ማለት በአመዛኙ ከነጭ አገዛዝ መላቀቅ ብቻ ተደርጎ እንደሚታሰብ ነው። ሮበርት ሙጋቤን ጨምሮ አብዛኞቹ የአፍሪካ የነፃነት ታጋዮች ሃገሮቻቸውን ከቅኝ አገዛዝ የማላቀቁን ትግል የመሩ መሪዎች በነጮቹ እግር ተተክተው ህዝባቸውን ነፃነት በሌለው ህይወት መሩት እንጂ እንደስማቸው የነፃነት ታጋይ ሆነው

አልቀጠሉም። ይልቅስ የእድሜ ዘመን አምባገነን ገዥ እና ሙሰኞች መሆንን መርጠዋል። ለዚህ ደግሞ ራሳቸው የመሰረቱት የአፍሪካ አንድነት/ህብረት የይስሙላ ምርጫቸውን ተአማኒ እና ፍትሃዊ መሆኑን አረጋግጫለሁ እያለ ውሸታቸውን የሚጋራ ጥሩ ከለላቸው ነው። ህብረቱ ህዝቦቻቸውን ስለምን ለውጥ ትሻላችሁ በሚል በጥይት የሚቆሉ፣ የሚያስሩ፣ ቤት አልባ የሚያደርጉ አምባገነኖችን ጠንከር አድርጎ ሲገስፅም ታይቶ አይታወቅም። በዚህ ረገድ እንደ ብቸኛ ተጠሪ የሚነሱት ኔልሰን ማንዴላ ናቸው። አሳዛኙ ነገር ግን የእሳቸውን ፈለግ ተከትሎ በስልጣን የሚጨክን መሪ ማግኘቱ አሁን የአህጉሪቱ ፈተና መሆኑ ነው።

## 7.5 ምዕራባዊውን አፍሪካ የሚያስረግደው ቦኮ ሃራም

የምዕራብ አፍሪካዊቷ ሃገር ናይጀሪያ ከአስር አመታት በፊት ሃይማኖትን የላይ ምክንያት ባደረገ የእርስ በርስ ጦርነት የምትታመስ፣ መልካም አስተዳደር የራቃት፣ የአምባገነኖች መፈራረቂያ፣ የሙስና ምድር ነበረች። በመሆኑም የመሰረተ ልማቷ ድክመት፣ ኢኮኖሚዋ ድቀት ነዳጅ የሚንቆረቆርባት የበረከት ምድር ሳያስመስላት ዘመናትን ገፍታለች። ሆኖም ባለፉት አስር አመታት እየተሻላት መጥቶ በተለይ በኢኮኖሚው መስክ እምርታን እያሳየች የአፍሪካ ባለታላቅ ኢኮኖሚ ሃገር እስከመባል እየደረሰች እንደሆነ እ.ኤ.አ በሜይ፣ 2014 የተነበበው "News Africa" የተባለው መፅሄት ዘግቧል። እንደ መፅሄቱ ናይጀሪያ እ.ኤ.አ ከ2012 ወዲህ ኢኮኖሚዋ በእጥፍ አድጎ የውጭ ኢንቨስተሮችን የምትጠራ (በአህጉር ደረጃ ከደቡብ አፍሪካ ቀጥሎ ሁለተኛዋ የውጭ ኢንቨስትመንትን ተቀባይ ሃገር ሆናለች)፣ የአክስዮን ገበያ የደራባት፣ በአለም ሁለተኛ ሲሚንቶ ላኪ ሃገር ነች። ሃገሪቱ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎቿን ቁጥር በእጅጉ ከማሳደጓ የተነሳ የአውሮፓዊያን የፍጆታ ሸቀጦች የሚጎርፉባት የገበያ ቦታ ሆናለች።

ይህን ሁሉ የኢኮኖሚ እምርታ በረከት ግን ለሁሉም ናይጀሪያዊያን በእኩል የሚጋሩት አይደለም። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ወደ ሚበረክቱበት ሰሜናዊው የሃገሪቱ ክፍል ሲኬድ ድህነቱ፣ ስራአጥነቱ፣ የመሰረተ-ልማት እጦቱ እንዳለ ነው። ከላይ የተገለፀው በረከት የሚታየው በደቡባዊ የሃገሪቱ ክፍል ለሚኖሩት አብዛኛ ክርስቲያን ዜጎች ነው። በመሆኑም ሰሜናዊው ክፍል ሁሌ ታጣቂ አማፅያን የማይጠፉበት፤ የውዝግብ ቀጠና እንዲሆን



አድርጎታል። በአሁኑ ሰአት ከናይጀሪያ አልፎ ልዕለ ሃያሏን አሜሪካን እያስረገደ ያለው እስላማዊ ታጣቂ ቡድን ቦኮ ሃራም ብቸኛው ባይሆንም በሃገሪቱ ሰሜናዊ ምስራቅ ግዛት ከሚንቀሳቀሱ አማፅያን መሃከል ጡንቸኛው አማፂ ነው። ታጣቂ ቡድኑ የተመሰረተው እ.ኤ.አ በ2002 መሃመድ ዩሱፍ በሚባል መሪ አማካይነት ሲሆን በሃገሪቱ ሰሜናዊ ምስራቅ አቅጣጫ የምትገኘውን ማድሁግሪ ከተማ መዲናው አድርጎ ይንቀሳቀሳል። አማፂ ቡድኑ የምዕራባዊያንን ትምህርት መማር ሃራም (ሃጥያት) ነው ከማለት ማንኛውም ከምዕራባዊን ማህበረሰብ የተገኘ ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ባህል ሁሉ የእስልምናን ትክክለኛ እሴቶች የሚያጠፉ በመሆኑ ከናይጀሪያ ምድር መጥፋት አለበት ብሎ እስከማመን ይደርሳል። ናይጀሪያን ከድሮ እስከዘንድሮ የመሩ መሪዎችም ሃገሪቱን በሸሪያ ህግ እካላስተዳደሩ ድረስ ሙስሊም ቢሆኑም ኢ-አማኒ ናቸው ይላል። ቦኮ ሃራም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ራሱን እያጠናከረ መጥቶ በቀጠና ደረጃ የምዕራባዊ አፍሪካ ሃገራት ስጋት ሆኗል። ቡድኑ "Al-Qaeda in the Islamic Maghreb" በምህፃሩ AQIM ከሚባለው የአልቃይዳ የአፍሪካ ክንፍ እና ከሶማሊው አልሸባብ ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚያመላክቱ ፍንጮች በመገኘታቸው የቡድኑ አደገኝነት በቅርቡ አሜሪካም ታምኖበታል። በመሆኑም እ.ኤ.አ 2013 ላይ ከአለም አቀፍ አደገኛ አሸባሪዎች ተርታ ፈርጃዋለች፤ በአሁኑ ሰአትም ከአልቃይዳ የበለጠ አደገኛ አሸባሪ ስትል ጭራውን ለመያዝ በቀጠናው ወታደራዊ እዝ እስከማቋቋም ደርሳለች።

ቦኮ ሃራም በይፋ የተመሰረተው 2002 ይሁን እንጂ ከናይጀሪያ መንግስት ጋር ወደ ተካረረ ግጭት የገባው ከ2009 ዓም ጀምሮ ነው። የግጭቱ መነሾ መንግስት ያወጣውን ሞተር ሳይክል ያለ ብረት ቆብ (Helmet) ያለመንዳት ህግ በመተላለፋቸው የተወሰኑ አባሎቹ በመንግስት ተጣቂዎች መገደላቸውን ተከትሎ ነበር። በግጭቱ የቡድኑ መስራች መሃመድ ዩሱፍን እና አማቱን ጨምሮ ከ800 በላይ አባላቱ ተገድለውበታል። የቡድኑ መሪ መሃመድ ዩሱፍ መሞት የበለጠ አክራሪ እና ጨካኝ ነው የሚባልለትን የአሁኑ የቡድኑ መሪ አቡበክር ሸካው ወደስልጣን እንዲመጣ ተአድርጎ የቦኮ ሃራምን አደገኝነትም ከፍ አድጎታል። የ2009ኙ የናይጀሪያ መንግስት እርምጃ አምነስቲ ኢንተርናሽናልን ጨምሮ በብዙ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ዘንድ መንግስትን ያስወገዘ ሰብአዊ መብት ጥሰት ነው የተባለለት ነው። እርምጃው ግን ቦኮ ሃራምን ከማዳከም ይልቅ መንግስትን አሳጥቶ ለሽማቂ ቡድኑ አባላትን ያበዛለት ክስተት እንደሆነ ተንታኞች ይገልፃሉ።

3



የሚንቀሳቀሱ የባህር ወንበዴዎችን ጨምሮ የአካባቢው ሃገሮች በርካታ ብረት አንጋች ታጣቂዎችን አቅፈዋል። ለዚህም ነው የቀጠናው ሃገራት ህብረት ሲቀመንበር በቅርቡ ታጣቂዎችን ለመመከት አለማቀፍ ድጋፍ ያስፈልገናል ሲሉ ተማፅኖ ያቀረቡት።

እንደሚታወቀው የነዳጅ አምራች ሃገሮች ከሌሎች በተለየ ሁኔታ የሸማቂዎች እንቅስቃሴዎች ይበረክትባቸዋል። ምዕራባዊ አፍሪካም አልጄሪያ፣ ቻድ፣ ኒጀር እና ናይጀሪያን አይነት በነዳጅ ሃብት የታደሉ ሃገራት ያቀፈ በመሆኑ የሸማቂዎችን ስጋት በጋራ ለመግታት ግምባር የፈጠሩት ከአስር አመት በፊት ነበር። ይህ ስምምነታቸው ነው በአሁኑ ወቅት "Trans-sharan counter Terrorosm Initiative" ወይም AFRICOM ወደሚባል ሁለመናው በአሜሪካ የሚዘወር ወታደራዊ እዝ የተቀየረው። ይህ ሁሉ ጥምረት ግን የቦኮሃራምን በሞት እና አልቂት ከተሞላው እርምጃው ሊገታው አልቻለም።

እንደ ተንታኞች ለቦኮ ሃራም ጉልበት ያስመፈታት ምክንያቱ ቡድኑን በእስላማዊ አክራሪ አሸባሪነት ፈርጆ ሃይማኖታዊ ጥያቄውን ከማጉላት እና ከማውገዝ በዘለለ ለቡድኑ መፈጠር መሰረታዊ ምክንያት የሆኑትን ፖለቲካዊ እርምጃ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች መርምሮ ተገቢውን መልስ ለመስጠት አለመሞከሩ ብቻ ሳይሆን አለመታሰቡም ነው። ከላይ እንደተገለፀው በሃይማኖት የተሸፈነው የቦኮ ሃራም ጥያቄ ፖለቲካዊ መልስ የሚያሻቸው የመልካም አስተዳደር እና የኢኮኖሚ ጥያቄዎችን ያረገዘ ነው። በመሆኑም ችግሩን የሚፈታው ከአህጉር እስከ አለም አቀፍ ደረጃ ወታደር አዋጥቶ የማይጨበጠውን ቦኮ ሃራምን ለመውጋት መሞከር አይደለም። ለችግሩ መፍትሄ የሚሆነው በሰሜኑ እና በደቡቡ የናይጀሪያ ግዛት ያለውን ሰፊ የእድገት ልዩነት ለማጥበብ፣ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ለማምጣት፣ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት፣ የአየር ጸባይ ለውጥ የሚያመጣውን የሰሜናዊ ናይጀሪያን ህዝብ ፍዳ ለማቃለል መስራት በዋነኛነት ከሃገሪቱ መንግስት ይጠበቃል። በተጨማሪም የሃገሪቱ መንግስትም ሆነ ቦኮ ሃራም እያስበረገጋት በቀጠናው ወታደራዊ እዝ (AFRICOM) እስከ መመስረት የደረሰችው ልዕለ ሃያሏ አሜሪካም አጥፍታ የማታጠፋውን ቦኮ ሃራምን በአፈሙዝ ነካክታ እያደር አራስ ነብር ከማድረግ ይልቅ የችግሩን ፖለቲካዊ መንስኤ በማጥናቱ እና እልባት መስጠቱ ላይ መበርታቱ ተሻይ ውጤት ያመጣል።



በዚህ መንገድ ወደ ስልጣን የመጣ አካል ስልጣኑን ለመልቀቅም የሚያወራርደው የሙት ቁስለኛ መጠን የለውምና የተሻለ ሲመጣ ስልጣን ለማስረከብ አያቅማማም፡፡

በ1998ዓ.ም በድንገት መከበር የጀመረው የብሄረሰቦች ቀን በዓል አሁን በሀገራችን በስራ ላይ ያለው ህገ-መንግስት በስራ ላይ የዋለበትን ቀን ለማሰብ ሲባል የሚደረግ ነው የሚለው ነገር የማይመልሰው እንድጥ ያቂአል፡፡

በ1987 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለውን ህገ-መንግስት ታሳቢ ለማድረግ ከ11 አመታት በኋላ በ1998 ዓ.ም እንዲከበር የተፈለገበት ምክንያት ከመንግስት በኩል በግልጽ ተነገር አያውቅም፡፡
በሀገራችን በዜጎች መብት ላይ የሚሰራ የሲቪክ ማህበራት የህጋዊነት ሽፋን በተሰጠው አፋኝ አዋጅ ከጨዋታ ውጭ በመደረጋቸው ስለዜጎች መብት መማማር፤ ግንዛቤ መፍጠር እናመከራከር አልተቻለም፡፡

ይህ አሳዛኝ እውነት ባረበበበት ሀገር ስለእንስሳት መብት መከበር የሚሰራ የሲቪክ ተቋማት ከመንግስት ይሁን ታአግኘተው እየተንቀሳቀሱ ስለመሆኑ የሚያመለክቱ የእህዮች መብት መከበር እንዳለበት የሚያስገነዝቡ መልዕክት ያዘሉ ፖስተርች እና በራሪ ጽሁፎች ያጋጥማሉ፡፡ ሁሉን ጠቅልሉ የመያዙ ነገር አቶ መለስን ከሲጡም ከወጡም እንዲሉ በማድረጉ እረፍት ማጣቱ ከህመማቸው ጋር ተደምር ሲቀራቸው ወደ ሞት ሳያማድፋቸው አልቀረም........

ይበጃል ያሉት ሀሳባቸው ሶስተኛ ወገንን አሳመነም አላሳመነም፤ አስከፋም አስደሰተ፤ ከመርህ ጋር ተጋጨም አልተጋጨ፤ ትናንት ራሳቸው በአንደበታቸው ከተናገሩት ጋር ገጠመም አልገጠመ ባሬ ያመኑበትን ብቸኛው መንገድ አድርገው ለማስረዳት አይሰንፉም፡፡ በእምባ ገነንና ሙሰኛ መሪዎች መዳፍ ውስጥ በሁለንተናዊ ጉስቁልና የሚሳጋውን አብዛኛውን የአፍሪካ ህዝብ ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ወጣ ከማለት ይልቅ የሰው ሀገሩን ሽኝቶ በሀገሩ ጅብ እየተበላ ነው ማለቱ ገላጭ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ከመጽሀፉ የተወሰደ

ዋጋ ብር 57.65